# በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል

በ
ጌታቸው ለገሠ

ግንቦት 1992 ዓ.ም.

# በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
በቋንቋዎች ጥናት ተቋም የኢትዮጵያ ቋንቋዎቸና ሥነ ጽሁፍ ክፍል

የአማርኛ ቋንቋ በማስተማር /TEAM/ ለሁለተኛ ዲግሪ (M.A.) በከፊል ማሟያነት
የቀረበ ጥናት

ጌታቸው ለገሠ

ግንቦት 1992 ዓ.ም.

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋጽኦ


በ

ጌታቸው ለገሠ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም


የፈተና ቦርድ አባላት

ዶ/ር ደጀኔ ለታ
አማካሪ
_______________ ፊርማ

ዶ/ር ገረመው ለሙ
ፈታኝ
_______________ ፊርማ

ዶ/ር አበበ ገብረ ፃዲቅ
ፈታኝ
_______________ ፊርማ

# ምስጋና

አማካሪዬ ዶ/ር ደጀኔ ለታ በማገኛቸው ጊዜና ቦታ ሁሉ ለምጠይቃቸው ምክርና ሙያዊ እገዛ ሳይታክቱና የጥናቴን የመጀመሪያ ረቂቅ/draft / ደጋግመው በማንበብ በሚለግሱኝ አስተያየት፥ ምክርና የሞራል ድጋፍ ባልታገዝ ኖሮ፥ ይህን ጥናት በግሌ ጥረት ብቻ እዚህ ደረጃ ላይ ማድረስ መቻሌ አጠራጣሪ ይሆን ነበር፡፡ ስለሆነም ለእኚህ እንደ አባት ለማከብራቸውና እንደወንድም ለምቀርባቸው አማካሪዬ ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይደረሳቸው፡፡

ትኩረቴን በዚህ ጥናት ላይ ካደረግኩበት ጊዜ ጀምሮ የጥናቴን ንድፍ /proposal / እና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎቼን በማንበብና በማስተካከል፥ ሙያዊ ምክር በመለገስ፥ ከጥናቱ ጋር አግባብነት ያላቸውን መጻህፍት በመስጠትና በመጠቆም እርዳታቸው ላልተለየኝ ዶ/ር ተሾመ ነቅአጥበብ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በእረፍት ምክንያት እስከተለዩኝና የዚህን ጥናት ሁለተኛ ሴሚናር እስከማቀርብበት ጊዜ ድረስ አማካሪዬ ሆነው ገንቢ ምክርና አስተያየት ለለገሱኝ ለዶ/ር ዮናስ አድማሱ ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ ይህ የጥናት ውጤት በታሰበለት ጊዜ እንዳጠናቅቅ ያላትን ጊዜና አቅም ሁሉ ተጠቅማ በጥንቃቄ በመጻፍ ትብብሯ ላልተለየኝ ወ/ሮ ዘነበች ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት የሚረዱኝን የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት ትብብራቸው ላልተለየኝ ለ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅ ለአቶ ተስፋዬ ገብረመስቀል፥ ለትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት ቤተ መጻህፍት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣ ለዚህ ጥናት የሚረዱኝን መጻህፍት በማቅረብና በተለያየ መንገድ እርዳታቸው ላልተለየኝ የትመዘድ መስሪያ ቤት ባልደረቦች ለወሮ ካሰች በቀለ፥ ለወ/ሮ ህኪም ይስህቅ፥ ለአቶ ተስፋዬ ጌሴሞ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ባለፉት ሁለት የትምህርት አመታት ቤተሰባችንን የማስተዳደሩን ኃላፊነት በግሏ ለተወጣችው ባለቤቴ ወ/ሮ ሠርካለም አሰፋና ከእኔ ከአባታቸው ማግኘት የሚገባቸውን ፍቅርና እንክብካቤ መስዋእት ላደረጉት ልጆቼ ማህሌትና እፀህይወት ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

ላለፉት ሁለት ዓመታት ትምህርቴን ስማርም ሆነ ይህን ጥናት ሳካሂድ የሞራል፥ የማቴሪያልና የሙያ እገዛቸው ላልተለየኝ ለእህቶቼ ለዶ/ር ሙሉብርሃን ዓለሜ፥ ለወ/ሮ ፀኃይ ይረዳው፥ ለወሪት. አባይነሽ በቀለ፣ ለወንድሞቼ ለዶ/ር ቦጋለ ሰለሞን፥ ለአቶ ሽመልስ አያሌው፥ ለአቶ አዱኛ ፍቀሬና ለአቶ ዮናስ ሸዋዬ፥ እንዲሁም እኔንም ሆነ ልጆቼን በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ እርዳታቸውና እንክብካቤያቸው ላልተለየን ለወሪት ብርሃኔ አርጋውና ፋንታነሽ በእውቀቱ ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ

ገፅ

ምሥጋና.......................................................................
የይዘት ማውጫ..................................................................
የሠንጠረዥ ማውጫ...............................................................
የአባሪዎች ማውጫ...............................................................
አኀጽሮተ ጥናት..................................................................
ማስታወሻ.........................................................................

ምዕራፍ አንድ

1.1. የጥናቱ ዳራ.................................................... 1
1.2. የጥናቱ አላማ...................................................... 3
1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት.................................................. 4
1.4. የጥናቱ ወሰን...................................................... 4

ምዕራፍ ሁለት

የድርሳናት ቅኝት

2.1. ሬዲዮ በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና............. 6
2.1.1. ትምህርትን ለማስፋፋት.................................... 6
2.1.2. የትምህርትን ጥራት ልዩነት ለማጥበብ................ 7
2.1.3. የትምህርት ወጪን ለመቀነስ.............................. 7
2.1.4. የትመህርትን ጥራት ለማሻሻል.......................... 8
2.2. ለመደበኛ ተማሪዎች የሚተላለፍ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም.. 9
2.2.1. የማጠናከሪያ ትምህርት በሬዲዮ............................ 9
2.2.2. ርቱእ ትምህርት በሬዲዮ.................................... 10
2.2.3. አጋዥ ትምህርት በሬዲዮ.................................... 12
2.2.3.1. አጋዥ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ............. 14
2.2.3.2. የቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶች... 15
2.3. የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ........................................ 20
2.4. የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ........................ 23
2.5. በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸው ሁኔታዎች............................................ 26
2.5.1. የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች አደረጃጀትና አመራር....... 26
2.5.2. ሥነ ትምህርታዊ አደረጃጀትና አቀራረብ.................. 27
2.5.3. የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች አጠቃቀም............... 27
2.5.4. የፕሮግራም ስርጭት ጥራት .................................. 27
2.5.5. ተማሪው ........................................................ 28
2.6. የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ታሪክ በኢትዮጵያ አጭር ቅኝት.. 29

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ

3.1. የጥናቱ መረጃ ምንጮች............................................ 33
3.2. የትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች፣ የመምህራንና የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘቶች ናሙና አመራረጥ........................ 33
3.2.1. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ......................... 33
3.2.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ................................ 35

3.2.3. የመምህራን አመራረጥ........................................ 37

3.2.4. ከ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ውስጥ ለትንታኔ የቀረቡ ይዘቶች ናሙና አመራረጥ........................................ 37
3.3. የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች........................................ 38
3.3.1. የክፍል ውስጥ ምለከታ........................................ 38
3.3.2. የጽሁፍ መጠይቅ........................................ 39
3.3.3. ቃለ መጠይቅ........................................ 40
3.3.4. የይዘት ትንተና........................................ 40
3.4. የመረጃዎች አተናተን ዘዴ........................................ 41

ምዕራፍ አራት
የመረጃዎች ትንተና
4.1. በክፍል ውስጥ ምልከታ የተደረሰባቸው መረጃዎች ትንተና.......... 43
4.2. በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት ከተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎቸ ትንተና........................................ 51
4.3. ለመምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና........ 68
4.4. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም............ 71
ይዘት ትንተና
4.5. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ትንተና........................................ 74

ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና የመፍትሄ ህሳብ........................................ 77
5.1. ማጠቃለያ........................................ 77
5.2. የመፍትሄ ህሳብ........................................ 79
ዋቢ ምንጮች (Bibliography) ........................................ 82

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ገፅ


ሠንጠረዥ 1:- በጥናቱ የተሸፈኑ ትምህርት ቤቶች ስርጭት መግለጫ.......... 34
ሠንጠረዥ 2:- መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ስርጭትና ብዛት መግለጫ........ 36
ሠንጠረዥ 3:-ቃለ መጠይቅ ስለተደረገላቸው መምህራን የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች ትንተና ................................................ 37
ሠንጠረዥ 4:-የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ በተማሪዎች ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ደረጃ ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ.................... 51
ሠንጠረዥ 5:-የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ከተማሪው ደረጃ አኳያ ያለውን የአቀራረብ ብቃት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ................... 53
ሠንጠረዥ 6:-የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያለውን ብቃት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ................................ 57
ሠንጠረዥ 7:-የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የክፍል መምህራንን ለማሳተፍ ያለውን ብቃት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጡአቸው መልሶች መግለጫ................................................ 59
ሠንጠረዥ 8:-ተማሪዎች ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶችን መግለጫ................................................ 61
ሠንጠረዥ 9:-ተማሪዎች በመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርትና በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አቀራረብ በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ................................................ 62
ሠንጠረዥ 10:-የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ................................ 64
ሠንጠረዥ 11:-ተማሪዎች ምን ያህል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት ተገኝተው ፕሮግራሙን እንደሚከታተሉ ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጡ መልሶች መግለጫ............. 67
ሠንጠረዥ 12:-የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በተመለከተ ለተማሪዎች ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ መግለጫ ................................ 68
ሠንጠረዥ 13:-የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት መግለጫ................................ 71
ሠንጠረዥ 14:-በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በመደበኛው የመምህሩ መምርያ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያሳይ................................ 72
ሠንጠረዥ 15: የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ መግለጫ................................ 74-75

# የአባሪዎች ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| አባሪ 1 | የክፍል ውስጥ ምለከታና ግመገማ መመርያ ቅፅ | 87 |
| አባሪ 2 | ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ | 90 |
| አባሪ 3 | ለተማሪዎች ከቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት መግለጫ | 94 |
| አባሪ 4 | ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ | 95 |
| አባሪ 5 | መምህራን ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት መልስ | 96 |
| አባሪ 6 | የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ንድፍ ናሙናዎች | 118 |
| አባሪ 7 | የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ ናሙናዎች | 135 |
| አባሪ 8 | የትምህርት በሬዲዮ ስርጭት የጊዜ ሰሌዳ | 141 |
| አባሪ 9 | በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ብዛት በየዞኑ | 142 |

# አኅጽሮተ ጥናት(Abstract)


እይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሞ÷ አጋዥ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም÷ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ረገድ ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ማወቅ የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት ነው፡፡

ሶስት የትመህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች በሚተላለፉባቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜያት የተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች÷ በተማሪዎች የተሞላ የጽሁፍ መጠይቅ÷ ለ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅና ሲተላለፉ የክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገባቸው ሶስቱ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራሞች ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና ለጥናቱ የሚበጁ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች ናቸው፡፡

የጥናቱ ውጤትም እንዳመለከተው፡ የትምህርት በሬዲዮውና የክፍል ውስጥ ትምህርት ፕሮግራሞች አለመቀናጀት÷ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ተማሪዎችንና የክፍል መምህራንን የማሳተፍ ብቃት ዝቅተኛ መሆን÷ ከትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ስርጭት በኋላ ለተማሪዎች የሚቀርቡ የመለማመጃ ጥያቄዎች ውሱን መሆን÷ የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ የክፍል መምህሩን አስቀድሞ ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለማዘጋጀት ያለው ብቃት ዝቅተኛ መሆን÷ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት በሬዲዮ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና ሁኔታዎች አለመሟላት÷ አለመመቻቸትና የክፍል መምህራን ስለ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አላማና አጠቃቀም ያላቸው ግንዛቤ ውሱን መሆን÷ ትምህርት በሬዲዮው ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ዝቅተኛ አድርገውታል፡፡

በተደረጉት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች÷ በተማሪዎች ከተሞላው የጽሁፍ መጠይቅና ለመምህራኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ አማካይነት በተገኙ መረጃዎች÷ ተማሪዎች ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህ ተማሪዎች ለትምህርት በሬዲዮው ያላቸው በጎ አመለካከት÷ ለወደፊቱ ቀደም ብለው የተጠቀሱትን ድክመቶች(ችግሮች) ለማቃለል ከተሞከረ÷ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለቋንቋው ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አወንታዊ አስተዋፅኦ ሊኖር እንደሚችል የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል፡፡ እነዚህን ድክመቶች (ችግሮች) ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ ሀሳቦችም በጥናቱ መጨረሻ ላይ ቀርበዋል፡፡

# ማስታወሻ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱና ስማቸው በእንግሊዝኛ ፊደላት የተጻፉ ደራስያን መጻህፍት የታተሙበት በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሲሆን፥ ስማቸው በአማርኛ የተጻፉ ደራስያን መጻህፍት የታተሙበት በኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ነው።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሬዲዮ በትምህርት መገናኛ ዘዴነት በአገልግሎት ላይ ከዋለ፥ በዓለም ስድስት አሥርት አመታት ሲሆነው፥ (Tilson, 1994; Mohntey, 1994; Bates, 1984) በኢትዮጵያም ሦሥት አሠርት አመታት ሆኖታል፥ (የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት፥ 1990፤ Endale, 1988; Tesfyie,1990)::

ሬዲዮ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በትምህርት መገናኛ ዘዴነት አገልግሎት መስጠት የጀመረው የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በማሰራጨት ነው፥ (Endale, 1988)::

ሬዲዮ በኢትዮጵያ የትምህርት መገናኛ ዘዴ ሆኖ አገልግሎት ላይ በዋለባቸው ባለፉት ሠላሳ አመታት ውስጥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞችን አስመልክቶ፥ በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት አማካይነት የተለያዩ አሳሽ ጥናቶች ተካሂደዋል፥ (ትመዘድ፥ 1987፤ 1990):: የእነዚህ ጥናቶች ትኩረትም የነበረው ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መደበኛ የትምህርት አይነቶችን ለማገዝና ለመደበኛ የርቀት ትምህርት ተማሪዎች በሚተላለፉ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች ይዘት፥ አቀራረብ ፥ አተገባበርና ተማሪዎችና መምህራን በፕሮግራሞቹ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመመዘን ነው::

ከእነዚህ ጥናቶች በተጨማሪ የተወሰኑ ምሁራን በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት በተወሰኑ አጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች ላይ ጥናቶችን አካሂደዋል:: ከእነዚህም ውስጥ Teshome (1998) በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞችና አስተዋፅኦ፥ Tesfye (1990) በአጋዥ የትምህርት በሬዲዮ /ቴሌቪዥን የአቀራረብ ዘዴ በመጀመሪያ ደረጃ የሳይንስ ትምህርቶች ላይ የይዘት ትንተና፥ Awel(1987) በመጀመሪያ ደረጃ (ከ3-6ኛ ክፍል) በእንግሊዝኛ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች ይዘትና ውጤታማነት ላይ፥ Almaze (1989)

በመጀመሪያ ደረጃ (ከ3-6ኛ ክፍል) በእንግሊዝኛ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች አቀራረብና ውጤታማነት ላይ፥ Endale(1988) የትምህርት በሬዲዮ ታሪክ በኢትዮጵያ … የመሳሰሉት ለአብነት ይጠቀሳሉ።

ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለተማሪዎችና ለመምህራን በየትምህርት አይነቶች አዳዲስ የፅንሰ ሀሳብ እወቀቶችን /ግኝቶችን ክሂሎችን በማስተላለፍና አዳዲስ የመማር/ማስተማር ዘዴዎችን በማስተዋወቅ፥ የመርህ ትምህርትንና የመምህራን የስልጠና ክፈተት ይሞላል፤ ለትምህርት ቤቶች ወቅታዊ የትምህርት መረጃዎችን በተመሳሳይ ፍጥነትና ጊዜ ለማሰራጨት ይረዳል፤ አጋዥና የማጠናከሪያ ትምህርት ፕሮግራሞችን በማስተላለፍ የትምህርትን ጥራት ያሻሽላል፤ መደበኛ የትምህርት አይነቶችን በቀጥታ ለተማሪው በማሰራጨት ትምህርትን በስፋት ለማዳረስና የትምህርትንም ወጪ ለመቀነስ… ይረዳል፥ Bates, (1984; Teshome,1998; Tilson, 1994; Mohnty,1994;Tesfaye,1990)

የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም እነዚህን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ውጤቶችን ማስገኘት አለማስገኘቱን ለማወቅና የፕሮግራሞችን ይዘትና አቀራረብ በማሻሻል ለተሻለ ውጤት ለመብቃት በፕሮግራሞቹ ላይ ተከታታይ ጥናቶች መደረግ እንዳለባቸው (Hwkridge; and Robinson, 1982; Tilson, 1994) ያስገነዝባሉ።

ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ በመደበኛው ትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራሞች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ውሱን፥ ሲሆኑ ፥ በተለይም በኢትዮጵያ ትምህርት በሬዲዮ ታሪክ ውስጥ ፋና ወጊ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ላይ እራሱን ችሎ የተደረገ ጥናት የለም። በፕሮግራሙ ላይ የተደረገ ጥናት ባለመኖሩም፥ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮገራም ለትምህርቱ ጥራት መሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ በውል ለማወቅ አልተቻለም።

በመሆኑም የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ ለሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚተላለፈውን አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ለቋንቋው ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ በጥናቱ ላይ ተመስርቶ ማወቅ ነው።

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በአዲስ አበባ መስተዳድር ለሰባተኛ ክፍል የሚተላለፈውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የክፍሉን ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማገዝ ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ለማወቅ ነው።

ጥናቱ በዚህ አጠቃላይ ዓላማ ላይ ተመስርቶ ከዚህ ለሚከተሉት የጥናቱ ጥያቄዎች መልስ ለመሻት ይሞከራል፡፡

ሀ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው የመማርያና የማስተማሪያ መጽሀፍ ጋር ያለው የይዘት ግንኙነት ምን ይመስላል"

ለ. ከትምህርት በሬዲዮ ንድፍ /script/ እና የመምህር መምርያ አዘገጃጀት መርህ አኳያ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ንድፍና የመምህሩ መምርያ እንዴት ተዘጋጅተዋል?

ጠ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው?

መ. የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ያላቸው ፍላጎትና ተሳትፎ ምን ይመስላል?

የእነዚህ ጥያቄዎች በጥናት ላይ የተመሰረተ መልስ ማግኘት የትምህርት በሬዲዮውን ፕሮግራም አስተዋጽኦ ደረጃ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ጥናቱ በአጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ዓላማ÷ የይዘት አመራረጥና የመምህር መምርያ አዘገጃጀት /አቀራረብ ላይ በቀረቡ ድርሳናትና በተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች በመታገዝ ከዚህ በላይ ለቀረቡ የጥናቱ ጥያቄዎች መልስ ለመሻት ይሞከራል÷ ጥናቱ የደረሰባቸውን የፕሮራሙን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ይጠቁማል፡፡ ለፕሮግራሙ የይዘት አመራረጥና መሻሻል ሊበጁ የሚችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ይጠቁማል፡፡

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

ከዚህ የሚከተሉት ምክንያቶች ይህን ጥናት አስፈላጊ ያደርጉታል፡፡

ሀ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የክፍሉን ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማገዝ፥ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ ለማወቅ ይረዳል፤

ለ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ንድፍና የመምህሩ መምሪያ ይዘት ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው የትምህርት ይዘት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማወቅ ይረዳል፤

ጠ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ንድፍና የመምህሩ መምርያ አቀራረብ፥ የትምህርት በሬዲዮ ንድፍና የመምህር መምሪያ አቀራረብ መርሆዎችን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ይረዳል፤

መ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል ለመረዳት ያስችላል፤

ሠ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ፕሮግራሙ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ይረዳል፤

ረ. ለቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ንድፍና የመምህር መምሪያ አዘጋጆች፥ ክለሳ ድርሳናትን መሰረት ያደረጉ የቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አዘገጃጀት/አቀራረብ መርሆዎችን ይጠቁማል፤

ሰ. በአማርኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች ዙርያ የሚታዩ ችግሮች ቢኖሩና በእነዚህ ችግሮች ላይ ጥናት ማድረግ ለሚሹ አጥኚዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ መስተዳድር ለሰባተኛ ክፍል በሚተላለፈው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ መሰረት ያደረገ ሆኖ ትኩረቱም ፕሮግራሙ ለሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት በሚችለው አስተዋጽኦ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ለሰባተኛ ክፍል የሚተላለፈውን የአማርኛ ቋንቋ የርቀት ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አይመለከትም፡፡

አጥኚውን ከገጠመው የጊዜ እጥረት የተነሳ ጥናቱ በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ በሚገኙ ሶስት የመንግስትና ሶስት የህዝብ በጠቅላላው ስድስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## የድርሳናት ቅኝት

### 2.1. ሬዲዮ በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና

በሰለጠኑትም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥን ለትምህርት እድገትና መስፋፋት ታስቦ የሚቋቋምበት አጋጣሚ ውሱን ነው፤ ቢሆንም ለምንም አገልግሎት ታስቦ ይሁን አንድ ጊዜ የተቋቋመ ሬዲዮ/ቴሌቪዥን ለትምህርት እድገትና መስፋፋት እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው (Bates, 1984,15)::

በዓለም ደረጃ ሬዲዮ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመደበኛ ትምህርት አገልግሎት የዋለው እ.ኤ.አ በ1926 በእንግሊዝ ሀገር ሲሆን÷ Tilson,(1994,20)Bates, (1984,16) በሀገራችንም ከ1952 ዓ.ም. ጀምሮ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ (ትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት÷1990 ዓ.ም)::

ሬዲዮ በኢመደበኛም ሆነ መደበኛ የትምህርት መገናኛነት የሚያገለግል ቢሆንም÷ የዚህ ጥናት ትኩረት በመደበኛው ትምህርት በሬዲዮ ላይ ብቻ ስለሆነ÷ ሬዲዮ ኢመደበኛ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ድርሻ በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተተም::

ሬዲዮ ለመደበኛ ትምህርት እንዲውል የሚደረግባቸው የተወሰኑ አላማዎች አሉት:: እነዚህም:- ትምህርትን በስፋት ለማዳረስ÷ የትምህርትን ጥራት ልዩነት ለማጥበብ÷ የትምህርትን ወጪ ለመቀነስና የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ናቸው::

#### 2.1.1. ትምህርትን ለማስፋፋት

በ Das,(1993 )Mohanty, (1994 ) Teshome, (1998 ) ጥናት መሰረት በሬዲዮ የመደበኛ ስርጭት አማካይነት በተወሰኑ ግን የስልጠና ብቃት ባላቸው የየትምህርት አይነቱ ባለሙያዎች የተዘጋጁ የትምህርት አይነቶችን በተወሰነ ጊዜና ፍጥነት የአንድን ሀገር አብዛኛውን ወይም ሁሉንም ክፍል ማዳረስ ይቻላል:: በዚህ የትምህርት መገናኛ ዘዴ አማካይነት የሚተላለፈውን/የሚሰራጭን ትምህርት ለመማር ፍላጎተና ችሎታው ያላቸው የአንድ አገር ዜጎች ሁሉ በአንድ የትምህርት ማዕከል (ትምህርት ቤት÷ ኮሌጁ) መሰባሰብ ሳያስፈልጋቸው በሚያመቻቸው ቦታ ሆነው መማር ይቻላሉ::

በተለይ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች በኢኮኖሚያቸው ኋላቀርነት የተነሳ፣ ትምህርት ቤቶችን በሚፈለገው መጠንና አይነት ገንብተው፥፣ መምህራንን በብዛትና በጥራት አሰልጥነውና የትምህርት መሳሪያዎችን አቅርበው መደበኛ ትምህርትን ለዜጎቻቸው ማዳረስ በማይችሉበት ሁኔታ ትምህርት በሬዲዮ ለዚህ ችግር ሁነኛ መፍትሄ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሱት የመስኩ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ::

### 2.1.2. የትምህርትን ጥራት ልዩነት ለማጥበብ

በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በአብዛኛው ተጠቃሚ የሚሆኑት:- ድሀው የኅብረተሰብ ክፍል፥ ተበታትኖ የሚኖረው የገጠሩ ኅብረተሰብ፥ በራሳቸው አፍመፍቻ ቋንቋ ለመማር እድል የማያገኙ የአናሳ ብሄረሰብ ህፃናት፥ በኅብረተሰቡ የባህልና በሌላም ምክንያት ተፅዕኖ የሚደረግባቸው የህብረተሰብ አካላትና የመሳሰሉት ናቸው Teshome, (1998,12)::

ከአንድ የተወሰነ ማዕከል የስልጠና ብቃት ባላቸው የትምህርት ባለሙያዎች የተዘጋጀን ትምህርት ወጥ በሆነ መንገድ በማዳረስ በትምህርት ጥራትና አቅርቦት ሊፈጠር የሚችለውን ልዩነት ለማጥበብ ትምህርቱ በሬዲዮ ሁነኛ መፍትሄ እንደሆነም በተለያዩ ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ በተለያዩ ምሁራን የተደረጉ ጥናቶችን በአብነት በመጥቀስ፥ Teshome, (1998,12) ይገልፃሉ::

### 2.1.3. የትምህርት ወጪን ለመቀነስ

በተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅትና የዓለም ባንክ በተለይ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ሬዲዮን በትምህርት መገናኛ ዘዴነት እንዲጠቀሙ ያበረታታሉ፥ (Btes, 1984, 59; Hawkridg and Robinson, 1982; 38):: እነዚህ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ታዳጊ ሀገሮች ትምህርት በሬዲዮን በስፋት እንዲጠቀሙ የሚያበረታቱት፥ መደበኛ ትምህርት በሬዲዮን መጠቀም ከተለመደው የፊት ለፊት /Face-to Face/ የማስተማር ዘዴ ጋር ሲነፃፀር የሚጠይቀው የገንዘብ ወጪ በጣም አነስተኛ ስለሆነ ነው::

ትምህርት በሬዲዮን ለመደበኛ ትምህርት መገናኛነት መጠቀም፥ የትምህርትን ጥራት በተሻለ ጠብቆ የገንዘብ ወጪን መቀነስ እንደሚያስችል፥ Bates,(1984, 239) Schramm, (1977,64)

ይገልጻሉ:: Teshome (1998,14) የ Fuller, (1986) እና የ Nettleton, (1991) ጥናቶች መሰረት አድርገው እንዳቀረቡት በሬዲዮ የሚተላለፍ ትምህርት ከተለመደው የክፍል ውስጥ ትምህርት አሰጣጥ ጋር ሲነፃፀር ለትምህርት የሚወጣን የገንዘብ ወጪ ከ35%-50% እንደሚቀንስ አመልክተዋል:: ሬዲዮ ከሌሎች የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች (ቴሌቪዥንና የመማርያ መጽሀፍ) ጋር ሲወዳደር ከሚጠይቀው አነስተኛ ወጪ በተጨማሪ ብዙ ቦታን መሸፈን የሚችልና ለተማሪውም አጠቃቀም በተሻለ የሚያመች መሆኑን Teshome (1998,14) የ Bosch, (1977) Nettleton, (1991); Schramm, (1977) ጥናቶችን ጠቅሰው አቅረበዋል::

### 2.1.4. የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል

ሬዲዮን ለመደበኛ ትምህርት መገናኛነት አስፈላጊ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ያለው አቅም ነው (Bates, 1984, Mohanty, 1994):: Bates(1984,15) እንደሚገልፁት መደበኛ ትምህርት በሬዲዮ ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ ቀዳሚ እየሆነ ያለው በስራ ላይ ያለውን የመርሀ ትምህርትና የመምህራን የስልጠና ክፍተት በመሙላት የመማር ማስተማርን ጥራት ማሻሻል ነው:: የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ታስቦ የሚተላለፍ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ባለሁለት ፈርጅ ነው:: የመምህራንን የትምህርት አይነት እውቀትና ሙያዊ ብቃትን ለማዳበር እንዲያስችል ታስቦ በቀጥታ ለመምህራን የሚተላለፈው ፕሮግራም አንዱ ሲሆን÷ ሁለተኛው በየመደበኛው የትምህርት አይነት ለተማሪዎች የሚተላለፈው የስርጭት ፕሮግራም ነው::

የመምህራን የስልጠና ብቃት ማደግ ለትምህርት ጥራት መሻሻል የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው÷ (Ur÷ 1996÷241):: በመደበኛ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አማካይነት መምህራን በመደበኛ ስራቸው ላይ እያሉ ÷ የትምህርት አይነቶችን÷ ሙያዊ ስለጠናዎችንና ለየትምህርት አይነቱ የሚረዱ የማስተማር ዘዴዎችን እንዲማሩና አጠቃላይ ሙያዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ይረዳቸዋል፤ ይህም የመምህራንን የስልጠና ክፍተት በመሙላት÷ የማስተማር ብቃታቸውን ወደላቀ ደረጃ ያሳድጋል፤ የተማሪውን የመማር ፍላጎትም ያጎለብታል (Bates, 1984, 27; Mohanty, 1994, 89)::

የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የመምህራንን ሙያዊ ብቃት በማሳደግ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል የሚኖረው አስተዋጽኦ የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት ስላልሆነ፥ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ብዙ ማለት አልተፈለገም፡፡ ይልቁንም የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት በሆነውና የመደበኛውን ትምህርት ጥራት ለማሻሻል ታስቦ በቀጥታ ለተማሪው በሚተላለፈው ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ያተኩራል፡፡

## 2.2. ለመደበኛ ተማሪዎች የሚተላለፍ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም

በቀጥታ ለተማሪዎች የሚተላለፍ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የትምህርት ጥራት ማሻሻያ አንዱ አካል ነው፡፡ (Bates, 1984,15) ፡፡ ሰዎች ትምህርትን የሚማሩባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ፤ በማዳመጥ፥ በማየት፥ በማንበብ፥ በመስራት... እውቀትንና ክሂልን መቅሰም ይቻላል፡፡ በማዳመጥ ትምህርትን ለመቅሰም ከሚያገለግሉ የመገናኛ ዘዴዎች አንዱና ውጤታማው ሬዲዮ እንደሆነ Das, (1993, 78) ይገልጻሉ፡፡ ለተማሪዎች በቀጥታ የሚተላለፉ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች በሶስት አይነት ይፈረጃሉ፡- እነሱም የማጠናከሪያ ትምህርት በሬዲዮ፥ ርቱእ ትምህርት በሬዲዮና አጋዥ ትምህርት በሬዲዮ ናቸው፡፡

### 2.2.1. የማጠናከሪያ ትምህርት በሬዲዮ

እ.ኤ.አ. በ1989 መደበኛ ትምህርትን በሬዲዮ በሚያሰራጩ 48 ሀገሮች ውስጥ በ91 የመደበኛ ትምህርት ተቋማት ላይ በተደረገ ጥናት፥ ተቋማቱ ትምህርት በሬዲዮን ከሚጠቀሙባቸው ዓላማዎች አንዱ ለመደበኛ የትምህርት አይነቶች ማጠናከርያነት /enrichment) ነው፤ (Tilson, 1994,4)፡፡

የማጠናከርያ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የተወሰኑ የመርሀ ትምህርት ይዘቶችን በተጨማሪ ሀሳብና በተሻለ አቀራረብ በማጠናከር የትምህርቱን ይዘትና አቀራረብ ጥራት ከፍ ለማድረግ ታስቦ የሚዘጋጅ ፕሮግራም ነው (Bates, 1984,18) የማጠናከሪያ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የመርሃ ትምህርቱን ይዘት በቀጥታና በቅደም ተከተል አያቀርብም፤ ይልቁንም በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡ ይዘቶች ውስጥ የይዘትና የአቀራረብ ጉድለት ይታይባቸዋል

ተብለው የሚታሰቡ ይዘቶችን ይመርጣል:: የማጠናከርያ ትምህርት በሬዲዮ በመርሃ ትምህርቱ የሰፈረው የትምህርት ዓላማ በተሻለ ስኬታማ ማድረግ ነው:: የማጠናከርያ ትምህርት በሬዲዮ በመርሃ ትምህርቱ ዓላማ ላይ እንጂ በዝርዝር የመርሃ ትምህርቱ ይዘት ላይ ስለማያተኩር በአንድ የትምህርት አይነት ዙርያ እንዳቀረበ የጠቅላላ እውቀት መጽሀፍ እንደሚመስል፥ (Tesfayie, 1990,46) ያብራራሉ:: Bates (1984,18) የማጠናከርያ ትምህርት በሬዲዮን ፕሮግራም አስመልክተው እንዳቀረቡትም:-

> "የማጠናከርያ ትምህርት በሬዲዮ የክፍል መምህሩ እንዲያስተምረው ለቀረበለት ትምህርት ተጨማሪ ወይም ማጠናከርያ ነው:: በመሆኑም የማጠናከርያ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለመደበኛው ትምህርት ወሳኝና የግድ አስፈላጊ አይደለም:: ዓላማውም የክፍል መምህሩ ለተማሪዎቹ እንዲያስተምር የተዘጋጀለትን የትምህርት ይዘት (እወቀት፥ሙያ፥፥ አመለካከት) በተለየ አቀራረብ ማዳበር ነው:: ይህም የመደበኛ ትምህርት ይዘቶችን በተለየ አቀራረብ የማጠናከር ተግባር የትምህርቱን ይዘት የተሻለ ማራኪ፥ ግነኙነት (relevance) ያለው አውዳዊ በማድረግና በማስፋት የተማሪውን የመማር ፍላጎት ለማዳበር ይረዳል:: (ትርጉም በጥናቱ አቅራቢ )

የማጠናከሪያ ተጨማሪ ትምህርት በሬዲዮ የመርህ ትምህርቱን ክፈተት ከመሙላት በተጨማሪ፥ ለመምህራንም አዳዲስ የማስተማር ዘዴዎችን በማሳየት የየትምህርት አይነት መምህራን የስልጠና ክፍተት ለመሙላት አስተዋጽኦ አለው፥ (Mohanty, 1994, 94)::

### 2.2.2. ርቱእ ትምህርት በሬዲዮ

Tesfayie (1990); Bates (1984) በርቱእ የትምህርት በሬዲዮ የማስተማር /direct teaching/ ፕሮግራም በመርሃ ትምህርቱ የቀረበው የትምህርት ይዘት በሙሉ በሬዲዮ ይተላለፋል:: በርቱእ የመደበኛ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መርህ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ/radio script/ ይዘጋጃል:: የተዘጋጀው የትምህርት በሬዲዮ ንድፍም፥ አስቀድሞ ተማሪው እንዲያውቀው በተደረገ መደበኛ የፕሮግራም ስርጭት ሰሌዳ መሰረት ይተላለፋል:: የእይታ ትምህርት መርጃ መሳሪያ /ስዕል ፥ ፎቶ ግራፍ ፥ ቻርተና የተለያዩ ምልክቶች/ የሚያስፈልጋቸውን የተወሰኑ የመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለተማሪው በማዳረስ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይታገዛል:: ለትምህርት በሬዲዮ ተማሪዎች የሚታደል

የትምህርት በሬዲዮ የጽሁፍ መመርያም ሌላው የርቱእ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አጋዥ የትምህርቱ መርጃ ነው።

በርቱእ የመማር/ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዳስፈላጊነቱና አመቺነቱ በተወሰኑ ወራት ወይም በየወሰነ ትምህርቱ አንድ ጊዜ ለተማሪዎቹ ማዕከል በሆነ ቦታ የፊት ለፊት የማጠናከሪያ /tutorial/ ፕሮግራም የሚዘጋጅበት ሁኔታ አለ።

ርቱእ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በተለይ በታዳጊ ሀገሮች መሰረታዊ ትምህርትን በስፋት ለማዳረስ የትምህርትን ጥራት ወጥ በሆነ መንገድ ለመጠበቅና የትምህርትን ወጪ ለመቀነስ አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ያስገነዝባሉ፥ /Hawkridge and Robinson, 1982; Bates, 1984; Scramm, 1977)። በሌላ በኩል ርቱእ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የትምህርት አቀራረብ ስርዓት ከሰው ልጅ የመማር ባህርይ ጋር መኖር የሚገባውን ትምህርታዊ መስተጋብር /interaction/ የሚገታ ደካማ አማራጭ መሆኑንም አጠንክረው የሚገልፁ የመስኩ ባለሙያዎችም ብዙ ናቸው (Bates, 1984,61) ። Bates ይህን ሀሳባቸውን በማጠናከር ርቱእ የትምህርት በሬዲዮ የተማሪውን ቅፅበታዊ ፍላጎትና አዝማሚያ ተከትሎ የመለዋወጥና የማይመርጥ ሜካኒካዊ ስለሆነ፥ አመቺነቱ ለሰው ከመዋል ይልቅ ግዑዝ ለሆነ አሻንጉሊት /robot/ እንደሆነ ይገልፃሉ።

በሀገራችን ለመደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያለክፍል ውስጥ መምህር እርዳታ እንዲማሩ የሚተላለፍ ርቱእ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የለም። የዚህ አይነቱ ፕሮግራም የሚተላለፈው በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ተሰራጭተው የሚገኙና መደበኛ ትምህርታቸውን በርቀት ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለሚከታተሉ ተማሪዎች ብቻ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት መደበኛ የርቀት ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምን አስተዋፅኦ እንደማይመለከት በዚህ ጥናት መግቢያ ላይ ተገልጿል። ቢሆንም ይህ ከዚህ በላይ የርቱእ ትምህርት በሬዲዮን ፕሮግራም ዓላማና አጠቃቀም አስመልክቶ የቀረበው ሀሳብ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሌላ የአገልግሎት አድማስ ጠቁሞ ለማለፍ ነው።

### 2.2.3. አጋዥ ትምህርት በሬዲዮ

አጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ የተዘጋጀ መርሃ ትምህርት የተወሰነ አካል ነው። በሬዲዮ ለማቅረብ የሚያመቹ የትምህርት ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቱ ተመርጠው ለዚህ አይነቱ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘጋጃሉ። ለአጋዥ የትምህርት በሬዲዮ የሚሆኑ የትምህርት ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የሚመረጡባቸው የተወሰኑ መስፈርቶች አሉ። እነዚህም:-

ሀ. በመማርያ/ማስተማርያ መጽሀፍ ውስጥ በይዞታቸው ተሟልተው ያልቀረቡ ይዘቶች

ለ. መርሃ ትምህርቱ ከተቀረፀና የመማርያ/ማስተማሪያ መጽሀፉ ከተዘጋጀ በኋላ አዲስ ይዘት የታከለባቸው ወይም ለውጥ የተደረገባቸው ይዘቶች፥

ጠ. በድምጽ ተቀርፀው ቢቀርቡ የተሻለ ውጤታማ ይሆናሉ ተብለው የሚታመንባቸው ይዘቶች ለምሳሌ:- በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለተማሪዎች የቋንቋውን ትክክለኛ ንበት (pronunciation) ለማስደለመጥ፥ በትምህርቱ ይዘት ላይ ከፍተኛ የሙያ ስልጠናና ልምድ ያላቸውን (በህይወት ያሉም ሆነ የሌሉ) ሰዎች የሰጡትን የቃለ መጠይቅ መልስ፥ ገለፃ፥ ውይይት በማቅረብ ይዘቱን በተሻለ ለማዳበር፥ በሞዴልነት የተመረጡ ውይይቶችን ክርክሮችን፥ ቃለ መጠይቆችን የስብሰባ አመራር ስነ ስርዓቶችን... በማቅረብ የቋንቋውን አጠቃቀም ስርዓት ለማስተማር፥ የትምህርቱን ይዘት አውዳዊና ተጨባጭ ለማድረግ በእውነተኛ ድምፅ (በእንስሳት፥ በአእዋፍት፥ በተሽከርካሪዎች፥ በነጎድጓድ፥ በገበያ ውስጥ ሁካታ ወይም በተማሪዎች የእረፍት ጊዜ ጫጫታ...) ማጀብ/ማገዝ ሲያስፈልግ፥

መ. ብዙም በእይታ የሚቀርቡ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ሳያስፈልጋቸው በድምፅ ብቻ ቢቀርቡ ተማሪውን ያስደስታሉ፥ የትምህርት ተነሳስኦቱንም ያሳድጋሉ ተብለው የሚታመንባቸውና የመስሉት ይዘቶች ናቸው፥ (Das, 1993, 84; Bates, 1984,20;Scramm, 1977,97)።

በእነዚህ መስፈርቶች መሰረት በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ተመርጦ የሚዘጋጅ የመደበኛ ትምህርቱ አጋዥ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም፥ ለተወሰነው የክፍል ደረጃ ለትምህርት አይነቱ የታቀደውን የትምህርት መርሃ ግብር እንዳያዛባና

የታሰበለትንም ውጤት እንዲያስገኝ ከተቀረው የክፍል ውስጥ ትምህርት ጋር መቀናጀት አለበት (Bates, 1984,21):: የትኞቹ የመርሃ ትምህርት ይዘቶች በክፍል መምህሩ መቅረብ እንዳለባቸውና የትኞቹ የመርሃ ትምህርት ይዘቶች በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም መቅረብ እንዳለባቸው አስቀድሞ መወሰን የሚያስፈልገው አላስፈላጊ የትምህርት ይዘቶችን የአቅርቦት መደጋግምና የክፍለ ጊዜያትን ብክነት ለማስወገድ/ለመቀነስ ነው::

ይህ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለተማሪዎች የሚተላለፈው በመደበኛ የትምህርት ክፈለ ጊዜ ነው:: ለአንድ የክፍል ደረጃ የሚቀረፅ መርሃ ትምህርት በአንድ የትምህርት አመት፥ በወሰነ-ትምህርቶች በወር፥ በሳምንት፥ በቀንና በክፍለ ጊዜ ተመጥኖ ነው የሚዘጋጀው:: ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ተመርጠው የተዘጋጁት ይዘቶችም ለተማሪው የሚቀርቡት በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የያዙትን ቅደም ተከተል ጠብቀው በተወሰነላቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ነው:: ለምሳሌ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፥ በአንድ የትምህርት አመት ውስጥ በሳምንት ለአምስት ክፍለ ጊዜያት እንዲሰጥ ተመጥኖ ነው የተቀረፀው:: ከእነዚህ በሳምንት ለዚሁ ትምህርት ከተወሰኑት አምስት ክፍለ ጊዜያት ውስጥ አንዱ ክፍለ ጊዜ ለአጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የተመደበ ነው (ይህ የክፍለ ጊዜያት ድልድል በአዲስ አበባ መስተዳድር ለሰባተኛ ክፍል የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ብቻ የሚመለከት ነው::)

በዚህ መሰረት የክፍል ውስጥ ትምህርቱና የትምህርት በሬዲዮው በአግባቡ ተቀናጅተው ካልሄዱ አግባብነት የሌለው የይዘት መደጋገምና የክፍለ ጊዜ ብክነት ይከሰታል፤ የክፍለ ጊዜያት ብክነት ከተከሰተም፥ ለክፍል ደረጃው የተመደበው የትምህርት ይዘት በታቀደለት የትምህርት ጊዜ እንዳይጠናቀቅ ምክንያት ይሆናል:: የዚህ አይነቱ ችግር እንዳይከሰት ከላይ በተገለፀው ምሳሌ ምሰረት ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የተመደበው የመርሃ ትምህርቱ አንድ አምስተኛ ይዘት መቼ እንደሚተላለፍ አስቀድሞ በክፍል መምህሩ መታወቅ አለበት (Das,1993)::

የመደበኛውን የክፍል ውስጥ ትምህርትና የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም በአግባቡ አቀናጅቶ የመጠቀም ችግር የሚፈጠረው፥ መርሃ ትምህርቱ ሲዘጋጅ ለመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት ብቻ ታስቦ ስለሚዘጋጅ እንደሆነ፥ Bates, (1984,21) ያስገነዝባሉ:: Tesfaye (1990,43) Gorden (1969) ን በመጥቀስ እንዳቀረቡት የመደበኛው ትምህርት አጋዥ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምና የመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት አቀነጃጀት ከሞላ ጎደል በቡድን ከማስተማር ስልት /team teching) ጋር የተመሳሰለ ነው:: በመሆኑም የሁለቱም የስራ ድርሻ ግልፅና ተለይቶ የተወሰነ ነው:: ለእንደዚህ ዓይነቱ የሰመረ ቅንጅታዊ አሰራርም የመማር/ማስተማሪያ መጽሀፉ ፥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሙ፥ በክፍል መምህሩ በቀጥታ የሚቀርበው የክፍል ውስጥ ትምህርትና ተማሪው በመማር ማስተማሩ ሂደት ማከናወን የሚገባቸው ተግባራት ሁሉ አስቀድመው በጋራ መቀናጀት አለባቸው (Bates, 1984,21)::

### 2.2.3.1. አጋዥ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ

መደበኛውን ትምህርት ለማገዝ የሚዘጋጅ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ከዚህ በፊት ካየናቸው ከማጠናከሪያና ርቱእ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች የተለየና መስተጋብራዊ የሆነ የአቀራረብ ስርዓትን ይከተላል:: በዚህ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ትምህርታዊ መስተጋብሩ የሚከናወነው:- በትምህርት በሬዲዮ መምህሩ፥ በተማሪውና በክፍል መምህሩ መካከል ነው:: የእነዚህም ሶስቱ አካላት የተቀናጀ መስተጋብር ለፕሮግራሙ ውጤታማነት ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው፥ Fuller, (1994,56) ይገልጻሉ:: ሬዲዮ ከሌሎች የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች:- ለምሳሌ ከመጽሀፍ፥ ከቴሌቪዥንና ከሌሎች ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴዎች ጋር ሲነፃፀር በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታን በመሸፈን፥ በዋጋው ቅለት፥ በቴክኒካዊ አጠቃቀም ቅለት፥ የአድማጭ ተማሪን ስሜት/ትኩረት የመሳብ /stimulus/ ኃይሉ ወዘተ. የተሻለ የትምህርት መገናኛ ዘዴ ቢሆንም፥ በባህርይው ብዙ ደካማ ጎኖች እንዳሉትም Mohantey, (1994, 11;) Almz, (1989,8)

ይገልጻሉ። እነዚሁ የመስኩ ባለሙያዎችም እንደሚያስገነዝቡት ሬዲዮን በትምህርት መገናኛ ዘዴነት ለመጠቀም ያሉበት ችግሮች:-

ሀ. የድምፅ መገናኛ ዘዴ ብቻ መሆኑ፥

ለ. ለሰው ልጅ ከባድ የሆነውን በተከታታይና በተመስጦ ማዳመጥን የሚጠይቅ መሆኑ፥

ጠ. የተማሪውን ቅፅበታዊ ፍላጎተና አዝማሚያ መከተል አለመቻሉ፥

መ. በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን (የፀጥታ መጓደልንና ሌሎች በድንገት የሚፈጠሩ ችገሮችን) ቆም ብሎ ማሳለፍ አለመቻሉ ( ይህን ችግር ትምህርቱን በቴፕ ክር መዝግቦ በማቅረብ ማቃለል ይቻላል)

ሠ. የሬዲዮ መምህሩና ተማሪዎች ባለመተያየታቸው አንዱ የሌላውን ስሜት ከፊቱ አንብቦ የመረዳትን እድል መገደቡና

ረ. በመምህሩና በተማሪው መካከል መኖር የሚገባውን ቀጥተኛ መስተጋብር መገደቡ ናቸው።

እነዚህ ሬዲዮን በትምህርት መገናኛ ዘዴነት ለመጠቀም የሚታዩ የመገናኛ ዘዴው ደካማ ባህርያት መገለጫዎች ናቸው። እነዚህ ሬዲዮን በትምህርት መገናኛ ዘዴነት ለመጠቀም እንከን የሆኑ ድክመቶችን ከሞላ ጎደል አስወግዶ ያሉትን ጠንካራ ጎኖች ለመጠቀም መፍትሄው መስተጋብራዊ ትምህርት በሬዲዮ (Interactive Radio Instrucltion) መሆኑን Tilson (1994,8) ያስገነዝባሉ።

አጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብን መስተጋብራዊ ለማድረግ:- ለትምህርቱ ዓላማና ይዘት ተስማሚ የሆኑ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልት /radio lesson format/ ምርጫ፥ የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ /script/ እና የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ አዘገጃጀት ከፍተኛ አስተዋጽ አላቸው።

### 2.2.3.2. የቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶች

Laflin, (1990) ዘጠኝ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶችን ይዘረዝራሉ። ከእነዚህ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶች ውስጥ ከትምህርቱ አላማና ይዘት፥ ከተማሪው

የትምህርት ደረጃና እድሜ ወዘተ. እኳያ ተገናዝበው ይመረጣሉ:: በመሆኑም እነዚህ ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርቡ የአቀራረብ ስልቶች ለሁሉም የትምህርት ዓይነት ÷ አላማ ይዘት÷ የተማሪው ደረጃ÷ እድሜ÷ ፍላጎት ወዘተ. በተመሳሳይ ሁኔታ ተስማሚ አይሆኑም:: በመሆኑም አንድ የአቀራረብ ስልት ለአንድ የትምህርት ይዘት÷ ዓላማ... ተስማሚ ሊሆን የሚችለውን ያህል ለሌላው የትምህርት ይዘት ዓላማ÷ የተማሪው ደረጃ÷ ፍላጎት... ተስማሚ ላይሆን ይችላል:: እያንዳንዱ የአቀራረብ ስልት ለምን አይነት የትምህርት ይዘት ዓላማና የተማሪው ደረጃ... በተሻለ እንደሚስማማና የተሻለ ውጤት ለማስገኘት እንደሚረዳ ማወቅ÷ እነዚህን የአቀራረብ ስልቶች ለተገቢው የትምህርት ይዘት ዓላማ÷ የክፍል ደረጃ... ለመጠቀም ያስችላል::

ሀ. ተጨባጭ÷ የአቀራረብ ስልት (actulility)

በአንድ ወቅት በድምፅ አማካይነት የተከናወነንና የተከሰተን ሁኔታ በመቅረፀ ድምፅ መዝግቦ በማቆየት አንድን የትምህርት ይዘት በሬዲዮ ለማስተማር የሚረዳ የአቀራረብ ስልት ነው:: ድምፁ ተማሪዎች ከሚማሩት የትምህርት ይዘት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሆኖ ተማሪዎቹ ይዘቱን ተጨባጭና አውዳዊ በሆነ ሁኔታ እንዲረዱት የሚያስችል/የሚረዳ መሆኑ ሊታመንበት ይገባል:: ይህ እወነተኛ የሰው ወይም የነገሮችና የክስተቶች ድምፅ በተመሳሳይ ጊዜና በተለያየ ቦታ ትምህርቱን የሚከታተሉ ተማሪዎች ተመሳሳይና ወጥ በሆነ ሁኔታ እንዲያዳምጡት/እንዲማሩበት ያስችላል:: ለምሳሌ የአንድን ቋንቋ ትክክለኛ ንበት ወይም የአነጋገር ዘዬ ለማስደመጥ ወይም ለማለማመድ÷ የአንድን ባለሙያ ገለፃ÷ ትችት÷ አስተያየት÷ የቃለ መጠይቅ አቀራረብ ስርዓት÷ ወይም የአራዊት÷ የእንስሳት÷ የአእዋፍ÷ የነፋስ ንውፅውፅታ÷ የወንዝ ፏፏቴ÷ የሰዎች ሁካታ÷ የሰማይ ነጎድጓድ... ለተማሪዎች ማስደመጡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህ ተጨባጭ የአቀራረብ ስልት ይመረጣል::

ለ. ድራማዊ የአቀራረብ ስልት

ድራማዊ የአቀራረብ ስልት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በተወሰነ የትምህርት ይዘት ላይ እየተነጋገሩ÷ እየተወያዩ፡ እየተከራከሩ ወይም በሚሰማ እንቅስቃሴ/ተግባር እያከናወኑ እያለ ተማሪዎች እንዲያዳምጡት የሚረዳ የአቀራረብ ስልት ነው። ይህ የአቀራረብ ስልት ትምህርቱ በአድማጭ ተማሪዎች አይነህሊና ተቀርፆ ሳይረሳ እንዲቆይ ይረዳል።

ጠ. የልምምድ ስልት

የሬዲዮ መምህሩ የሚናገረውን ተማሪዎች በቡድን እንዲለማመዱ የሚያግዝ የአቀራረብ ስልት ነው። የሬዲዮ መምህሩ ደጋግሞ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ተማሪዎቹም እየደጋገሙ በሚሰጡት መልስ የሚከናወነው ልምምድም የዚሁ አቀራረብ ስልት አካል ነው። በዚህ የልምምድ ሂደት የተማሪዎችን አነጋገርም ሆነ መልስ የሚከታተለውና የሚያርመው የክፍል መምህሩ ነው።

መ. የቃለ መጠይቅ ስልት

በቃለ መጠይቅ የትምህርት በሬዲዮ የአቀራረብ ስልት በሬዲዮ መምህሩና በሬዲዮ መምህሩ ተጋባዥ እንግዳ መካከል በትምህርቱ ይዘት ላይ የጥያቄና መልስ ውይይት ይካሄዳል። በዚህ የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች በትምህርቱ ይዘት ላይ ጠለቅ ያለ የንድፈ ሀሳብ ትንተና እንዲደረግላቸውና የፅንሰ ሀሳብ እውቀት እንዲጨብጡ ይረዳቸዋል፤ በቃለ መጠይቅ የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች በውይይቱ የቀረበውን ይዘት እንዲገነዘቡ ከመርዳት በተጨማሪ÷ የቃለ መጠይቅ አቀራረብንና የውይይት ስርዓትን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

በቃለ መጠይቁ/ ውይይት ሂደት የሚቀርቡ ጥያቄዎችም ሆነ የሚመለሱ መልሶች ይዘትና አቀራረብ የአድማጭ ተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥኑ መሆናቸውን አስቀድሞ ማጤን ያስፈልጋል። በውይይቱ የሚነሱ ሀሳቦችም የትምህርቱን ይዘትና ተማሪዎች ከውይይቱ በኋላ እንዲያዳብሩት በታሰበው እወቀት ወይም ክሂል ላይ እንዲያተኩር ማድረግም ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ (Laflin) ያሳስባሉ።

ሠ. የገለፃ /Lecture/ አቀራረብ ስልት

ገለፃ በተለመደው የክፍል ውስጥ የፊት ለፊትም ሆነ በትምህርት በሬዲዮ የመማር/ማስተማር ሂደት ተዘውትሮ የሚሰራበት የአቀራረብ ስልት ነው። አቀራረቡ በሬዲዮ መምህሩ ገለፃ ላይ ብቻ የሚያተኩር (የተወሰነ) ከሆነ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪውን የማይስብ ፍዝ(Dull) ይሆናል። አቀራረቡ የተማሪውን ስሜት የሚስብና መስተጋብራዊ እንዲሆን በገለፃው ጣልቃና ከትምህርት በሬዲዮው ስርጭት ቀጥሎ ከገለፃው ርዕስ ጋር የሚሄዱ ቀልዶችን፥ ተረቶችን፥ ምሳሌያዊ አነጋገሮችንና ጥያቄዎችን ማቅረብ የገለፃውን ተደማጭነት ከፍ ያደርገዋል። የገለፃ አቀራረብ ስልት በመካከለኛና በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የፅንሰ ሀሳብ እውቀትን ለማስተማር ይረዳል።

ረ. የተግባራዊ ምላሽ ስልት /physical responce/

የተግባራዊ ምላሽ የአቀራረብ ስልት ከሬዲዮ መምህሩ በሚቀርቡ ትዕዛዛትና ተማሪዎች ትዕዛዛቱን በማዳመጥ በሚፈፅሟቸው አካላዊ ተግባራት ይከናወናል። ተማሪዎች ከሬዲዮ መምህሩ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ በጥሞና እያዳመጡ፥ የታዘዙትን ተግባር በትክክል ማከናወናቸውን የሚከታተለው የክፍል መምህሩ ነው። ይህ የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች ቀደም ብለው የተማሩት ክሂል ምን ያህል እንደገባቸው ለመመዘን ከመርዳቱም በተጨማሪ፥ በቃል የተማሩትን በተግባር እንዲለማመዱት ይረዳል፥ የማዳመጥ ክሂልንም ያዳብርላቸዋል። በትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ፥ መምርያ በሚጠቆመው መሠረት በተግባራዊ ምላሽ የተጀመረው የመማር/ማስተማር ሂደት ከትምህርት በሬዲዮው ስርጭት በኋላም በክፍል መምህሩና በተማሪው መካከል በሚደረግ መስተጋብር ሊቀጥል ይችላል። በዚህ የአቀራረብ ስልት በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ የሚገኙ የቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋው እንዲጠቀሙ ለመርዳት ያስችላል።

ሰ. የተከታታይ ትረካ ስልት /narration/

ተከታታይነትና ተያያዥነት ያለው ታሪክ በድራማ ወይም በትረካ መልክ የሚቀርብበት የአቀራረብ ስልት ነው። በዚህ ስልት የሚቀርብ ታሪክ በአንድ የትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ እንዲቋረጥ አይፈለግም። ታሪኩ ተማሪዎችን በሚያጓጓና ልብ በሚሰቅል የታሪኩ አንጓ ላይ ተቋርጦ ለሚቀጥለው የትምህርት በሬዲዮ ወይም ለሚቀጥለው መደበኛ የክፍል ውስጥ ትምህርት

ክፍለ ጊዜ ይተላለፋል፡፡ በዚህም የተማሪውን የትምህርት ፍላጎት ያነቃቃል የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራምና መደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት በአግባቡ ከተቀናጁም፥ በተወሰነ የታሪክ አንጓ ላይ የተቋረጠውን ትረካ ተማሪዎች ከትምህርት በሬዲዮው ክፍል ጊዜ በኋላ በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን የተቋረጠውን ታሪክ በራሳቸው እንዲቋጩት ከተደረገ የተማሪዎችን የፈጠራ ምናብ ያሰፋል፥ ስለታሪኩ ሂደትና ፍፃሜ የሚያደርጉት ውይይትና ክርክር የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፤ የውይይት ስረዓትን ይማሩበታል፤ ታሪኩን በየግላቸው እንዲቋጪት ከተደረገም የጽሁፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፡፡

ለዚህ አይነት የአቀራረብ ስልት የሚያመችና እነዚህን ከላይ የተጠቀሱ ክሂሎች ለማዳበር የሚረዳ ታሪክ ለማዘጋጀት የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ አዘጋጁን ከፍተኛ ችሎታና ጥንቃቄ ይጠይቃል፡፡ ከተማሪው ፍላጎተና ደረጃ ጋር የሚስማማ ታሪክን ማዘጋጀት ወይም መምረጥ፥ በድምፃቸው በታሪኩ ውስጥ የቀረቡ ገጸ ባህርያትን በትክክል የሚወክሉ ሰዎችን መምረጥና ማለማመድ፥ የተለያዩ ክሂሎችን ለማዳበር የሚረዱ ክንውኖችን/tasks/ ማዘጋጀት ከፍተኛ ችሎታንና ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው፡፡

ሸ. በአጭር ልቦለድ የአቀራረብ ስልት

በአጭር ልቦለድ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልት የፈጠራ ድርሰት አፃፃፍ ስልትን ለማስተማርና በተማሪዎች ዘንድ የአመለካከት ለውጥን ለማምጣት ይረዳል፡፡ የልቦለዱ ገፀ ባህርያት ከሁለትና ከሶስት ባይበልጡና የፆታ ስርጭታቸውም ወንድና ሴት ቢሆኑ ተማሪው ድምፃቸውን በቀላሉ ለመለየትና መልዕክቱን በተሻለና ግልፅ በሆነ መንገድ ለመረዳት ያስችለዋል፡፡

እንደትረካ የአቀራረብ ስልት ሁሉ በአጭር ልቦለድ የአቀራረብ ስልትም የልቦለዱ ታሪክ ሳይቋጭ ተማሪው የልቦለዱን ታሪክ በሚፈልገው መንገድ እንዲያቀርብ ቢበረታታ የፈጠራ ጽሁፍ ክሂሉን እንዲያዳብር ይረዳዋል፤ የራሱን የታሪክ አጨራረስ ከጓደኞቹ የታሪኩ አጨራረስ ጋርም እያወዳደረ ከራሱም ስህተትና ከጓደኞቹም እንዲማር ይረዳዋል፡፡ በክፍል መምህሩ

አማካይነት ስለታሪኩ ሂደትና አጨራረስ ላይ የውይይት መድረክ በመክፈትና ተማሪዎችን በማወያየት የተማሪዎችን የማዳመጥ የውይይት(የንግግር) ክሂል ለማዳበር ይረዳል፡፡ በዚህ የአቀራረብ ስልት አብዛኛው የትምህርቱ ሂደት የሚከናወነው ከትምህርት በሬዲዮው ስርጭት ክፍለ ጊዜ በኋላ ነው የሚሆነው፡፡ ለዚህም የትምህርት በሬዲዮውን ፕሮግራምና መደበኛውን የክፍል ውስጥ ትምህርት አስቀድሞ ማቀናጀት ያስፈልጋል፡፡

ቀ. በሙዚቃ /በመዝሙር አቀራረብ ስልት

በሙዚቃ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልት ለጀማሪ ህፃናት የድመፆችን ንበትና የቃላትን ሰዋሰዋዊ አገባብ በቃል እንዲያጠኑት ከመርዳት አልፎ፤ ቋንቋው አፍ መፍቻቸው ለሆኑ ህፃናትና በመካከለኛም ሆነ በከፍተኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር የሚያደርገው እገዛ እምብዛም ነው፡፡ በተለይም የዚህ ጥናት ትኩረት ለሆነው ለሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮን በሙዚቃ/መዝሙር የማስተማርያ ስልትነት መጠቀም ከደረጃ በታች ይሆናል፡፡

Lflin(1994) አበክረው እንደሚያስገነዝቡት እነዚህን የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶች ተጠቅሞ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የታሰበለትን ውጤት ማስገኘት የሚችለው ስልቱ ለይዘቱ ያለው አግባብነትና በትምህርቱ ሂደት የሬዲዮ መምህሩ÷ የክፍል መምህሩና የተማሪው ተሳትፎ ተቀናጅቶ ሲቀርብ ነው፡፡

## 2.3. የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ

Laflin(1994,59) ስለትምህርት በሬዲዮ ንድፍ ሲገልፁ

> የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ በሬዲዮ እንዲተላለፉ የተመረጡ የትምህርት ፕሮግራሞችን የያዘ ሰነድ ነው፡፡ ንድፉ የፕሮግራሞችን ይዘት÷ የአቀራረብ ስልት÷ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ መኖር የሚገባቸውን መስተጋብሮችና ተማሪው በትምህርቱ ላይ ተነሳስአ እንዲያድርበት የሚረዱ አላባዎችን ያካተተ ጽሁፍ ነው፡፡
> ብለዋል፡፡ (ትርጉም በጥናቱ አቅራቢ)

የትምህርት በሬዲዮንን ዓላማ ማወቅ፥ የትኛው የመርሀ ትምህርቱ ይዘት ይበልጥ ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም እንደሚያመች፥ እያንዳንዱን የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ካለፈውና ከሚቀጥለው የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት እንዲኖረው ማድረግና በአንድ ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ይዘቶችም ተገቢውን ቅደም ተከተል ይዘው እንዲደራጁ ማድረግ፥ ትምህርቱ ሲቀርብ በምን አይነት ድምፅ መታጀብ እንዳለበት ማጤን፥ መምረጥና ለትምህርቱ ይዘት አቀራረብ የሚያመችን የአቀራረብ ስልት መምረጥ የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ ከመፃፉ በፊት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው (Das, 1993)::

ቀደም ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከተው በትምህርት በሬዲዮ የመማር/ማስተማር ሂደት በድምፅ ላይ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ምክንያት በሬዲዮ መምህሩና በተማሪው መካከል ያለውን የግንኙነት ክፍተት ቀንሶ ግንኙነቱን በተሻለ ቀና ለማድረግ የንድፉ አቀራረብ ግልፅ መሆን አለበት። የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ የሚፃፈው ለአይን ንባብ ሳይሆን ለጆሮ እንዲደመጥ መሆኑ እየታሰበ መፃፍ እንዳለበት Mohanty, (1994,73) ይገልፃሉ። በጽሁፍ የቀረበን የትምህርት ይዘት ተማሪው እስከሚገባው ደጋግሞ የማንበብ እድሉ አለው፥ ይዘቱ በክፍል መምህሩ የሚቀርብ ከሆነ፥ ተማሪው መምህሩን እስኪገባው ድረስ ጠይቆ የመረዳት እድል አለው፤ በሬዲዮ የሚተላለፍን ትምህርት ግን እነዚህን አማራጮች ተጠቅሞ ያልገባውን መረዳት አይችልም።

ይህን የትምህርት በሬዲዮኑን ተማሪ ችግር ለመቀነስ የሚረዱ መፍትሄዎች ብለው Mohnty, (1994,74) የሚዘረዝሯቸው ነጥቦች፥ የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ በጽሁፍ የሚቀርብ ቢሆንም ቋንቋው የጽሁፍ ሳይሆን የንግግር፥ መደበኛ የጠነነ ሳይሆን፥ ተራ ቀላልና ኢመደበኛ መሆን አለበት። ፀሀፊው ለማያውቃቸው ተማሪዎች እየጣፈላቸው ሳይሆን፥ ማሰብ ያለበት አጠገቡ ላሉ ተማሪዎች እየነገራቸው እንዳለ እያሰበ መሆን አለበት፥ ትምህርቱ በአጫጭር አረፍተ ነገር ወይም ተዋስኦ የተገነባ መሆንና ትምህርቱ የቀረበው በቃለ ምልልስ ከሆነም የውይይቱ ተሳታፊዎች በድምፃቸው ተለይተው የሚታወቁ፥ በውይይቱም ወቅት ተወያዮቹ በስም እየተጠሩ የሚነጋገሩ ሊሆን ይገባል.. የተሰኙት ናቸው።

የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ ሲዘጋጅ ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች አስቀድሞ ያገናዘበ መሆን እንዳለበት (Laflin, 1990,61) ይጠቁማሉ::

ሀ. ሬዲዮ ለትምህርት መገናኛነት ያሉበትን ችግሮች ያገናዘበ

ለ. ለትምህርቱ ይዘት አቀራረብ የሚረዱ በዖታ፥ በእድሜና በደረጃ የሚመጥኑ አቅራቢዎችን/ገፀ-ባህርያትን የሚጠቀም፥

ጠ. በቁጥራቸው የተወሰኑ አቅራቢዎችን/ገፀ ባህርያትን የሚጠቀም፥

መ. በአንድ ፕሮግራም ውስጥ ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና ለሚሰጡ መልሶች የተለያዩ አቅራቢዎችን የሚጠቀም፥

ሠ. ለፕሮግራሙ ይዘት፥ ጠቃሚ የሚሆኑ አጃቢ ድምጾችን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ የሚጠቀም፥

ረ. በአንድ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ አቅራቢዎች አንዱ ከሌላው ተለይተው የሚታወቁ፥

ሰ. ትምህርታዊ መስተጋብር የሚታይበት፥

ሸ. ለአንድ ፕሮግራም ወጥ የአቀራረብ ስልትን የሚጠቀም፥

ቀ. በቋንቋ አቀራረቡ ግልፅ የሆነ

በ. ለተማሪዎች ተሳትፎ በቂና ተስማሚ የጊዜ ፋታ የሚሰጥ

ተ. በፕሮግራሙ ለቀረቡ ጥያቄዎች በየዕለቱ ትክክለኛና የማጠናከሪያ መልስ የሚሰጥና፡

ቸ. ተማሪዎች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልሶቻቸውን በቃል ለክፍል መምህራቸው የሚሰጡበትን ጊዜ ለይተው እንዲያውቁ የሚያደርግ

የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ንድፍ፥ የተዋጣለትና የታሰበለትን ዓላማ በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲያሳካ በንድፉ ዝግጅት ወቅት በቂ የሙያ ስልጠናና ልምድ ካለው የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ አዘጋጅ ጋር የመርሀ ትምህርት አዘጋጆች፥ የትምህርት አይነት መምህራን፥ ተማሪዎች፥ የሬዲዮ ፕሮግራም አቅራቢ፥ የትምህርት ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች እንዲሳተፉ Das(1993,84) Laflin, (1994) ያስገነዝባሉ::

## 2.4. የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ

የትኛው የመርሀ ትምህርት ክፍል/ይዘት በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም እንደሚሸፈንና የትኛው የመርሀ ትምህርቱ ክፍል ደግሞ በክፍል መምህሩ እንደሚቀርብ ለይቶ ለማወቅ የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ ወሳኝ ድርሻ አለው:: በትምህርት በሬዲዮ ክፈለ ጊዜ የክፍል መምህሩ የሚኖረውን የስራ ድርሻ ቀድሞ እንዲያውቅና በተግባርም እንዲተረጉመው የሚመራው የመምህሩ መምሪያው ነው:: (Das, 1993,89)

Das(1993) አክለው እንደሚገልፁት ብዙ ጊዜ መምህራን ከግንዛቤ ጉድለት የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ሙሉ በሙሉ መምህሩን የሚተካ እየመሰላቸው በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ክፍለ ጊዜ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ አይወጡም:: በትምህርት በሬዲዮው መምህርና በክፍል መምህሩ ትግግዝ እንዲቀርብ ታስቦ በተዘጋጀው ፕሮግራም ውስጥ የክፍል መምህሩ ተሳትፎ ከሌለ ፕሮግራሙ ህያውነት አይኖረውም፥ ትምህርቱም የታሰበለትን ውጤት ያስገኛል ተብሎ አይታሰብም:: የክፍል መምህሩ በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ሊኖረው የሚችለውን የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲያስወግድና በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ተገቢውን ተሳትፎ እንዲያደርግ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ከመጀመሩ አስቀድሞ የክፍል መምህሩ ስለ ፕሮግራሙ ዓላማ፥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አጠቃቀም በፕሮግራሙ አቅርበት ውስጥ ስለሚኖረው ድርሻ ትክክለኛውን ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ለፕሮግራሙ ስመረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው:: በተጨማሪ የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርት በሬዲዮውን ይዘት አቀራረብና በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቅበትን ተግባር አስቀድሞ ለማሳየት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው::

የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ ለክፍል መምህሩ ስለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አጠቃላይ ግንዛቤ ከማስጨበጥና በፕሮግራሙ አቅርቦት ሂደት ውስጥ የሚጠበቅበትን ድርሻ ለይቶ ከማመልከት በተጨማሪ፥ የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም ከክፍል ትምህርቱ ጋር ለማቀናጀት የሚያደርግለት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው:: በክፍል መምህሩ የሚቀርበው የመርሃ ትምህርቱ ይዘት ከትምህርት በሬዲዮው ይዘት ጋር ተከታታይነትና ተያያዥነት እንዲኖረው ለማድረግ የመምህሩ መምሪያ ለክፍል መምህሩ ዋነኛ መሳሪያ ነው:: የክፍል መምህሩ

የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም ከክፍል ትምህርቱ ጋር ለማቀናጀት እንዲያመቸው የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምርያ ቀደም ብሎ ሊደርሰው ይገባል (Das, 1993,84)::

የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስርጭት መተላለፍ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ለክፍል መምህሩ ከደረሰው ለፕሮግራሙ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የትምህርት መርጃ መስርያዎች ቢኖሩ፥ መስሪያዎችን ለማዘጋጀት ለማቅረብና ለመጠቀም ያስችለዋል፤ ተማሪዎች በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘት ላይ ቀደም ብለው ፍንጭ እንዲኖራቸው ለማስቻል ይረዳዋል፤ ቅደመ ጊዜና ድህረ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ወቅት በእሱም ሆነ በተማሪዎች መከናወን ያለባቸውን ትምህርታዊ ክንውኖች ለይቶ ለማወቅ ያስችለዋል:: ለዚህም ነው የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርት በሬዲዮኑን መምህር፥ የክፍሉን መምህርና ተማሪዎችን የሚያገናኝ ድልድይ ነው የሚባለው (የትመዘድ፥ 1990፡48)::

ከትምህርት በሬዲዮ ንድፍ ጋር ጎን ለጎን የሚዘጋጀው የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ በየወሰነ ትምህርቱ ወይም በትምህርት አመቱ የሚተላለፉ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞችን የያዘና እያንዳንዱ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራምም በሶስት ክፈሎች የተከፋፈለ ነው:: ክፍሎቹም ቅደመ ትምህርት በሬዲዮ፥ ስርጭት፥ በትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ጊዜና ድህረ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ናቸው:: ዳስ የእነዚህን ሶስት የትምህርት በሬዲዮ የመምህር መምርያ አካላት ሲያብራሩ፡-

ሀ. ቅደመ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት፡- ይህ ክፍል የትምህርት በፌዲዮው ፕሮግራም ከመሰራጨቱ ቀደም ብሎ በክፍል መምህሩና በተማሪው መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት የሚያመለክት ክፍል ነው:: በዚህ ክፍል የክፍል መምህሩ ስላለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ይዘት ለተማሪዎቹ በክለሳ መልክ እንዲያስታውሳቸውና በዕለቱ ስለሚቀርበው ፕሮግራም ይዘት/ርዕስ ፍንጭ እንዲሰጣቸው ይረዳዋል:: ስለ አለፈው የትምህርት ይዘት ለመከለስም ሆነ በዕለቱ ስለሚቀርበው የትምህርት ይዘት ፍንጭ ለመስጠት የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ መምህሩን ብቻ ማዕከል ያደረገ ሳይሆን፥ ስላለፈው ይዘት ተማሪዎችን የሚያሳትፉ ጥያቄዎችን በማቅረብና በማወያየት፥ ላይ ያተኮረ መሆን አለበት:: በእለቱ ስለሚቀርበው ይዘትም ፍንጭ ለመስጠት

ይዘቱን የሚጠቀሙ ቃላትንና ሀረጎችን በስሌዳ ላይ በመፃፍ ይዘቱን በግልም ሆነ በውይይት እንዲተነብዩ በማበረታታት ለክፍል መምህሩ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ይረዳዋል፡፡

ለ. የትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ጊዜ፡- ይህ ክፍል ዋናው የትምህርት በሬዲዮ ይዘት በሚሰራጭበት 15 ደቂቃ ውስጥ በክፍል መምህሩና በተማሪዎች መከናወን ያለባቸውን ተግባራት የሚጠቁም ክፍል ነው፡፡ በዚህ የስርጭት ጊዜ ውስጥ የመምህሩ ተግባር የክፍሉን ፀጥታ መቆጣጠርና ከሬዲዮ መምህሩ የሚጠየቀውን ተግባር በማከናወን ተማሪዎችን መርዳት ይሆናል፡፡ ማዳመጥ ግላዊ በመሆኑ የትምህርት በሬዲዮው በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪው ለየግሉ ፀጥ ብሎ ያዳምጣል፥ ከሬዲዮ መምህሩ የሚሰጡ ተግባራት ካሉም እያዳመጠ ያከናውናል ማስታወሻ ይይዛል፡፡ በስርጭቱ ጣልቃ ከሬዲዮ መምህሩ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪው መልሱን ለክፍል መምህሩ ይሰጣል፡፡ እንደ ትምህርት በሬዲዮው ይዘትና አቀራረብ በስርጭቱ ወቅት በተማሪውም ሆነ በመምህሩ መከናወን የሚገባቸው ተግባራት በመምህሩ መምሪያ ይጠቆማሉ፡፡

ጠ. ድህረ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት፡- ይህ የመምህሩ መምርያ ክፍል የፕሮግራሙ ስርጭት ካበቃ በኋላ በተማሪዎችና በክፍል መምህሩ መከናወን ያለባቸውን ክንውኖች /tasks/ ያመለክታል፡፡ በድህረ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ጊዜ ውስጥ ትምህርታዊ ክንውኖቹ በተማሪው የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ክንውኖቹም በዚያ የትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ ብቻ የሚከናወኑ ሳይሆኑ፥ ቀጣይነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የክፍል መምህሩ በትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ እየተመራ/እየታገዘ ተማሪዎችን በጥንድ ወይም በቡድን በማቀናጀት ትምህርታዊ ክንውኖችን እንዲያከናውኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፥ ያበረታታል፥ ይከታተላል እንደሁኔታውም ይሳተፋል፡፡ የመምህሩ መምሪያ በእያንዳንዱ የትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ በክፍል መምህሩና በተማሪዎች መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ከማመልከት/ከመጠቆም በተጨማሪ፥ ለፕሮግራሙ ተጨማሪ የትምህርት መርጃ የሚሆኑ ጽሁፎችን ርዕስና ምንጫቸውን፥ ከትምህርት በሬዲዮው ስርጭት በፊት ጊዜና በኋላ ለተማሪዎች ለእይታ መቅረብ ያለባቸውን ፎቶግራፎች፥ ስዕሎች፥ ሠንጠረዦች... ሊይዝ ይችላል (Das, 1993, 89)፡፡

## 2.5. በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸው ሁኔታዎች

### 2.5.1. የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች አደረጃጀትና አመራር

የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች /ሬዲዮ÷ ቴሌቪዥን/ አደረጃጀትና አመራር እንደየሀገሮቹ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ይለያያል(Tesfayie, 1990; Hawkridge and Robinson, 1982):: የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች አደረጃጀትና አመራር የትምህርት መገናኛ ዘዴዎችን ባለቤትነት÷ የባለሙያዎችን ደረጃጀትና አመራር÷ የትምህርት ፕሮግራሞችን እቅድ÷ ዝግጅት÷ ስርጭት አጠቃቀምና ግመገማ ጉዳዮችን ይመለከታል:: በአብዛኛው በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ አህጉራት ውስጥ በሚገኙ ሀገሮች የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ተቋማትና ባለሙያዎች ባለቤትነትና አመራር በግል ወይም በድርጅት የትምህርት ተቋማት ስር ይሆናል(Hawkridge and Robinson,1982) :: እንደ ኢትዮጵያ ባሉ (በብሄራዊ/ማዕከላዊ የትምህርት ስረዓት በሚመሩ) ታዳጊ ሀገሮች የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች በየሀገሮቹ የመገናኛ ዘዴዎች ባለስልጣን መስሪያ ቤት ወይም በትምህርት ጉዳዮች ባለስልጣን (ትምህርት ሚኒስቴር) ባለቤትነት ስር ይመራሉ (ለምሳሌም ኢትዮጵያ) (Tesfaye ,1990)::

በኢትዮጵያ ሁኔታ የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች አደረጃጀትና አመራር በትምህርት ሚኒስቴር ስር እራሱን ችሎ በተቋቋመው የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት ስር ነው:: ይህም የትምህርት በሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እቅድ÷ ዝግጅት ለየትምህርት አይነቱ መስጠት ስለሚገባው የጊዜ መጠን÷ የስርጭት ጊዜና ሌሎችም ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ የመወሰንና የመምራት ስልጣን ያለው አንድ ድርጅት መሆኑ ለፕሮግራሙ ስምረት አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው Das, (1993,89) ያስገነዝባሉ:: የዚህ አይነቱ አደረጃጀትና አመራርም÷ ለፕሮግራሞች ቅንጅት ያግዛል፤ በባለሙያዎች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን የቅንጅታዊ አሰራር ክፍተት ያጠባል:: ሆኖም የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች በትምህርት ሚኒስቴር ስር በሚደራጁበት ሁኔታ የፕሮግራም አቅራቢዎችና የቴክኒክ ባለሙያዎች የስልጠና ብቃት ማነስና

በዚህም ምክንያት የስርጭት ጥራትና ማራኪነት ማነስ ሊከሰት እንደሚችል (Das, 1993,93) ያስገነዝባሉ።

### 2.5.2. ሥነ ትምህርታዊ አቀራረብ አደረጃጀት /The Pedgogical Approach/

Tesfayie (1990) Jmison (1978) ን ጠቅሰው እንዳቀረቡት የመገናኛ ዘዴውን በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ ተማሪዎች ከማናቸውም የመገናኛ ዘዴ መማር ይችላሉ። በመሆኑም ለትምህርቱ ውጤት መለያየት ምክንያት የሚሆኑት፥ ትምህርቱ ከቀረበባቸው መስሪያዎች ይልቅ ትምህርቱ ራሱ የተደራጀበትና የቀረበበት መንገድ ነው። እውቀት በተለያዩ ምልክቶች /symbols/ ማለትም በቃላትና በስዕል፥ አማካይነት ሊቀርብና ሊቀሰም ይችላል። ተማሪው በየትኛውም ምልክት ይሁን የቀረበለትን የትምህርት ይዘት እንዲማር የይዘቱ አደረጃጀትና አቀራረብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። ለዚህ ደግሞ ትምህርቱ ከሚቀርብበት መሳሪያ /መገናኛ/ ይልቅ የፕሮግራሙ አዘጋጆችና አቅራቢዎች የትምህርቱን ይዘት ያደራጁበት መንገድና ያቀረቡበት ስልት ለትምህርቱ ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው (Tesfaye, 1990) ያስገነዝባሉ።

### 2.5.3. የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች አጠቃቀም

የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች የተሻለ ተቋማዊ አደረጃጀት ቢኖራቸውና በተሻለ አመራር ስር ቢሆኑም፥ የትምህርቱ ፕሮግራም ሥነ ትምህርታዊ መርህን ተከትሎ ቢደራጅና ቢቀርብም በትምህርት ቤት ደረጃ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ካልዋለ የታሰበለትን ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ከምን አይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጋር አብሮ መቀናጀት እንዳለበት መወሰን ያለበት ከዋናው የመገናኛ ዘዴ/ሬዲዮው/ ጉድለት/ድክመት በመነሳት/የጉድለቱን ክፍተት ለመሙላት ታስቦ መሆን አለበት። የትምህርቱ ርዕስ፥ የትምህርት ቤቱ አውድ፥ የተማሪው ሁኔታ /ደረጃ የሚመረጠውን የትምህርት መርጃ መሳሪያ አይነት ይወስኑታል (Das, 1993, Tesfayie, 1990) ። እነዚህ ሁኔታዎች በትምህርት ቤት ደረጃ ከሞላ

ጎደልም ቢሆን ተሟልተውና ተጣጥመው ሲገኙ ነው ትምህርቱ የታሰበለትን ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው::

### 2.5.4. የፕሮግራም ስርጭት ጥራት

የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በቴክኒካዊ አቀራረብ ጥራቱ ግልፅ ሆኖ መስማትና ማራኪነት የፕሮግራሙን ተደማጭነትና ተቀባይነት ከፍ ያደርገዋል÷ የተማሪውንም የመማር ተነሳስኦ/motivation/ ይጨምራል:: የእነዚህ ሁኔታዎች መሟላት ፕሮገራሙ የታሰበለትን ውጤት እንዲያስገኝ የሚኖረው÷ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው (Das, 19993, 87)::

### 2.5.5. ተማሪው

የትምህርት በሬዲዮ ዋነኛው ተጠቃሚ ተማሪው ነው:: የትምህርቱ ፕሮግራም ውጤታማነት የሚለካውም ፕሮገራሙ በተማሪው ላይ ባስከተለው የባህርይና የአሰራር ለውጥ ነው:: የፕሮግራሙ ብቃተና አስተዋፅኦ ደረጃ መለኪያውም ተማሪው ነው:: ተማሪዎች ለመማር የሚመርጧቸው የመማር ስተራቴጅዎች /Learning strategies/ አሏቸው:: የተወሰኑ ተማሪዎች በግል በማንበብ ሌሎች ደግሞ የሌሎችን ገለፃ ወይም ከሬዲዮ በማዳመጥ ወዘተ. መማርን ይመርጣሉ:: አንድ የትምህርት አቀራረብ ስልት የተዋጣለት የአቀራረብ ስልት /ዘዴ ነው የማይባለውም የሁሉንም ተማሪዎች የመማር ስተራቴጂና የትምህርት አውድ ማሟላት ስለማይቻለው ነው:: Laflin, 1990,97)::የተለያዩ የትምህርት አቀራረብ ስልቶች የየራሳቸው የማስተማር ችሎታ አቅም/campacity/ እና ችግሮች /constraints/ የሚገለፀውም ተማሪዎች ትምህርቱን ከሚማሩበት÷ ከሚመርጡት/ከለመዱት የመማር ስትራቴጂ ከትምህርቱ ርዕስ/ይዘት ልዩነት አንፃር ነው::

እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች የሚያሟላና ለሁሉም ተማሪ የመማር ስትራቴጂ የሚስማማ የትምህርት አቀራረብ ስልት መምረጥ የማይቻል ቢሆንም÷ የአብዛኛውን ተማሪ ፍላጎትና

የመማር ስትራቴጂ ለማጥናትና ለማወቅ መሞከርና ለዚያም የሚስማማ ስልት ለመምረጥ መጣር ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ስኬታማነት የሚኖረው አስተዋፅኦ አወንታዊ ነው /Tesfaye, 1990 )::

የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጆችና አቅራቢዎች ከትምህርቱ ዝግጅትና አቅርቦት በፊት የትምህርቱ ፕሮግራም የሚቀርብላቸውን ተማሪዎች አስመልክቶ ማጤን የሚገባቸው:-

ሀ. የትምህርት ፕሮግራሙ የሚቀርበው ለማን ነው?

ለ. ተማሪዎቹ ትምህርቱን የሚማሩት ለምን አገልግሎት ሊያውሉት ነው?(ዓላማው)

ጠ. የተማሪዎቹ የትምህርት ዳራ ምንድን ነው?

መ. ተማሪውን የሚያስደስቱት የትምህርት ተግባራት የትኞቹ ናቸው?

ሠ. አብዛኛው ተማሪ የሚመርጣቸው የመማር ስተራቴጂዎች የትኞቹ ናቸው? ለተሰኙት ጥያቄዎች መልስ ለመሻት መሞከር ነው:: ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ማለትም የትምህርቱ ፕሮግራም የሚዘጋጅላቸውን ተማሪዎች ማወቅ ማለት ነው:: የትምህርት በሬዲዮኑን ዋነኛ ተጠቃሚ አውቆ፥ የትምህርት ፕሮግራሙንም ከእሱ አኳያ ለማዘጋጀትና ለማቅረብ መሞከር ፕሮግራሙ የታሰበለትን ውጤት እንዲገኝ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን Tesfaye (1990, ) Brown (1977) ን በመጥቀስ አስገንዝበዋል::

## 2.6. የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ታሪክ በኢትዮጵያ አጭር ቅኝት

የሬዲዮ ስርጭት አገልግሎት ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የተጀመረው በኢጣልያን ወረራ ዋዜማ አካባቢ በ1928 ዓ.ም. ቢሆንም፥ መደበኛ በሆነ መልክ ስርጭቱ የተጀመረው ከኢጣልያ ወረራ ማግስት በ1934 ዓ.ም. ነው (ትመዘድ፥ 1990):: ሆኖም የሬዲዮ ፕሮግራሞች የስርጭት ሽፋን እየሰፋና እየተጣናከረ የመጣው ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ ነው:: የኢትዮጵያ ሬዲዮ የአጠቃላይ አገልግሎት የስርጭት ፕሮግራምና የጊዜ ሽፋን ከተጠናከረ በኋላ፥ ይህ የመገናኛ ዘዴ ለትምህርት ስርጭት መስፋፋት ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ትኩረት እያገኘ መጣ::

ሬዲዮ ትምህርትን ለማስፋፋት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለማወቅም የሙከራ/አሳሽ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከ1957-1958ዓ.ም. የተለያዩ በኦዲዮ ካሴት የተቀረፁ የትምህርት ፕሮግራሞች ለሙከራ ጥናቶች ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው (ትመዘድ፡1990)፡፡ በዚህ መሰረት ከመጋቢት እስከ ሰኔ 1957 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ አማርኛን ማንበብና መፃፍ ለማይችሉ ተማሪዎች ሊያገለግል የሚችል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኦዲዮ ካሴት ተዘጋጅቶ በዳግማዊ ሚኒሊክ ትምህርት ቤትና በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ውስጥ የሙከራ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ከዚህ የሙከራ ጥናት ውጤት በመነሳት ከህዳር 7 ቀን 1958 ዓ.ም. ጀምሮ አዲስ አበባ ገፈርሳ በሚገኘው ፊውታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ተማሪዎች ለአስር ወራት ከሃያ አራት ቀናት የዘለቀ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቴፕ ካሴት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

በዚያው አመት ማለትም ከመጋቢት 22 ቀን 1958 ዓ.ም. ጀምሮ በሌላ ተመሳሳይ ትምህርት ቤት እንዲሁ የሙከራ ጥናት ለማድረግ ለሰባት ወር ከአስራ አንድ ቀን የዘለቀ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቴፕ ክር ተዘጋጅቶ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ዝግጅት የሙያ ዘርፍ በቂ የሰለጠነ ሰው አለመኖር፥ ሬዲዮ በትምህርት ዘርፍ ስለሚሰጠው ባለብዙ ፈርጅ ጠቀሜታ ገና በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ባለማግኘቱና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት የትምህርት ፕሮግራሙ ለአምስት አመታት ያህል ከነአካቴው ተቋርጦ እንደነበር የትመዘድ (1990) እና የ Endale, (1988) ጥናታዊ ዘገባዎች ያመለክታሉ፡፡

ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የህብረተሰቡ የትምህርት ፍላጎት ማደግ፥ የተማሪ ቁጥር መጨመርና ሀገሪቱ እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት የነበራት የሰለጠነ የሰው ኃይል ብዛትና የማቴርያል ውሱንነት የትምህርት በሬዲዮን ፕሮግራም ተፈላጊነት እየጨመረው እንደመጣ  የተጠቀሱት ጥናታዊ ዘገባዎች ያመለክታሉ፡፡

በትምህርት ቤቶች የተማሪ ቁጥር ማደግ ምክንያት ትምህርት ቤቶች በፈረቃ ማስተማር መጀመራቸው፥ በትብብር መልክ ከተለያዩ ሀገሮች ተልከው ሲያስተምሩ የነበሩ መምህራን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣትና አዳዲስ የትምህርት አይነቶች እየተጨመሩ መምጣት የትምህርቱን አቅርቦት አስቸጋሪ አድርገውት ነበር፡፡ በወቅቱ ተሻሽለው የቀረቡ የትምህርት አይነቶችን ለምሳሌ (Entebe Mathemtics እና  New English for Ethiopian) የተሰኙ የትምህርት

አይነቶችን ማስተማር የሚችሉና የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን በተፈለገው መጠን አለመኖር ችግሩን ይበልጥ እንዳባባሰው EMMA(1967) ይገልጻል:: የእነዚህ ችግሮች እየተባባሰ መምጣት የትምህርት በሬዲዮኑን አስፈላጊነት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ሳይሆን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም እንዲሆን አደረገው::

የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በትምህርቱ መስክ እየተከሰቱ የመጡ ችግሮችን ለማቃለል የሚኖረውን አስተዋፅኦ ለማረጋገጥ÷ ቀደም ሲል በ1957 እና በ1958 ም. የተደረጉ የሙከራ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ ሌላ ሰፋ ያለ ጥናት ለማድረግ ተወሰነ:: ጥናቱን ያበረታታውና ያካሄደውም EDO(Center for Educationl Development Overseas) የተሰኘው የእንግሊዝ ሀገር የጥናት ቡድን ነው:: ቡድኑ ከ(UNESCO) ባለሙያዎች ጋር ባካሄደው ሰፋ ያለ ጥናት ኢትዮጵያ በዚያን ወቅት በትምህርቱ ዘርፍ በኩል ያለባትን የሰለጠነ የሰው ኃይልና የማቴርያል እጥረት ችግር ለመቅረፍ ሬዲዮን በትምህርት መገናኛ ዘዴነት መጠቀም ሁነኛ መፍትሄ መሆኑን ጠቁሟል::

በዚህ የጥናት ውጤት መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1962 ዓ.ም. የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስርጭት እንደተጀመረ የትመዘድ (1990-) እና የ (Endale,1988) ጥናታዊ ዘገባዎች ያመለክታሉ:: የትምህርት ፕሮግራሞቹም ይተላለፉ የነበሩት በወቅቱ የመናገሻ አውራጃ እየተባለ በሚጠራው ክልል ውስጥ ለነበሩ ሃምሳ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበር:: በዚያ ዓመተ-ምህረት ከህዳር ወር ጀምሮ በዚህ ክልል ውስጥ ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም የአማርኛ÷ የእንግሊዝኛ ÷ የታሪክ÷ የጂኦግራፊና የሳይንስ ትምህርቶች መሰራጨት ጀምረው እንደነበር እነዚህ የጥናት ዘገባዎች ያመለክታሉ::

እነዚህ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቀጥታ ይተላለፉ የነበሩት የትምህርት አይነቶች ፕሮግራም ቢቋረጥም÷ መደበኛውን ትምህርት በግላቸው በርቀት ትምህርት ፕሮግራም ለሚከታተሉ የሁለተኛ ደረጃ የርቀት ትምህርት ተማሪዎች ሲተላለፍ ቆይቷል::

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይተላለፉ የነበሩ እነዚሁኑ መደበኛ የትምህርት አይነቶችን የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስርጭት እንደገና ለመጀመር÷ በትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት አማካኝነት በ1989 ዓ.ም. የሙከራ ጥናቶች ከተደረጉ በኋላ በዚህ አመት

(በ1992) የትምህርት አይነቶቹ ስርጭት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በማስተላለፍ የተጀመረ ሲሆን በሚቀጥለውም ዓመት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች እንደሚጀምር የዚህ ጥናት አቅራቢ ከድርጅቱ የምርምርና ዶክመንቴሽን ክፍል ጠይቆ ባገኘው መረጃ ለማወቅ ችሏል::

በ1962 ዓ.ም. የማስታወቂያ ሚኒስቴርን ሬዲዮ ጣቢያ በመጠቀም የተጀመረው የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም፥ በአሁኑ ጊዜ ትምህርት ሚኒስቴር ባስተከላቸው አስራ አንድ የትምህርት ሬዲዮ ጣቢያዎች በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት አይነቶች ለመደበኛ ትምህርት ቤቶች በመተላለፍ ላይ ይገኛሉ (ትመዘድ፥ 1990፥ Tesfaye, 1990::

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚጠቀም ሲሆን፥ በዚህ የጥናቱ ክፍልም :- የጥናቱ የመረጃ ምንጮች፥ የመረጃ ምንጮች ናሙና አወሳሰድ፥ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችና የመረጃ አተናተን ዘዴዎች ይቀርባሉ::

### 3.1. የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ የዋሉት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. የ7ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በሚተላለፍባቸው ክፍለ ጊዜያት የተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች፥-

ለ. በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የተሞላ የጽሁፍ መጠይቅ፥

ጠ. ለ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅና

መ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ንድፍና የመምህሩ መምሪያ ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና

### 3.2. የትምህርት ቤቶች፥ የተማሪዎች፥ የመምህራንና የትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም ይዘቶች ናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት አይነተኛ አላማ ለአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የክፍል ደረጃውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት ለማሻሻል እያደረገ ያለውን አስተዋፅኦ ለማወቅ እንደመሆኑ መጠን፥ በመስተዳድሩ ውስጥ ከሚገኙና የ7ኛ ክፍል ደረጃን ከሚያካትቱ 224 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስድስት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል:: ቁጥራቸው ከዚህ በላይ ከተጠቀሱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምን እንደማይጠቀሙ የታወቁ 46 የግልና የማህበረሰብ (community) ትምህርት ቤቶች አስቀድመው ከእጣ ውጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል::

ሠንጠረዥ 1 በጥናቱ የተሸፈኑ ትምህርት ቤቶች ስርጭት መግለጫ

| ዞን | የትምህርት ቤቶች አይነትና ብዛት | | የተመረጡ ትምህርት ቤቶች | የትምህርት ቤቱ አይነት | ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ወረዳ/ቀ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የህዝብ | የመንግስት | | | |
| 1 | 20 | 5 | ዳግማዊ ብረሃን | ህዝብ | 6/01 |
| 2 | 25 | 12 | እድገት በህብረት | የመንግስት | 21/01 |
| 3 | 16 | 12 | ፍሬ ህይወት ቁ.2 | የህዝብ | 19/55 |
| 4 | 30 | 24 | እንጦጦ አምባ | የመንግስት | 11/01 |
| 5 | 21 | 6 | አፍሪካ አንድነት ቁጥር 1 | የህዝብ | 2/11 |
| 6 | 2 | 6 | ገላን ቁጥር ቁ.1 | የመንግስት | 27/08 |
| ድምር | 114 | 65 | 6 | | |

በጥናቱ ውስጥ የተጠኚዎችን አካባቢያዊ ስርጭት ሚዛናዊ ለማድረግ ሲባል÷ በመስተዳድሩ ውስጥ ከሚገኙ ዞኖች ውስጥ አንድ አንድ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። በመስተዳድሩ ውስጥ በሚገኙ 6 ዞኖች ውስጥ 114 የህዝብና 65 (አባሪ 8ን ይመልከቱ) የመንግስት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ (በየዞኑ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን አይነትና ብዛት በአባሪ-ይመልከቱ)። በመስተዳድሩ ውስጥ ከሚገኙ 224 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስድስት ትምህርት ቤቶች በቀጥታ በተራ ዕጣ ናሙና እንዲመረጡ ቢደረግ÷ ምናልባት ዕጣው በተወሰኑ ዞኖች ውስጥ ብቻ ያሉ÷ የመንግስት ወይም የህዝብ ትምህርት ቤቶችን ብቻ ሊሸፍን የሚችልበት አጋጣሚ ከተፈጠረ በጥናቱ መካተት የሚገባቸውን ተጠኚዎች አካባቢያዊና የትምህርት ቤት አይነቶችን ስርጭት ሚዛናዊ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል። የተጠኚ ትምህርት ቤቶች አይነትና አካባቢያዊ ስርጭት ሚዛናዊ ሳይሆን ቀርቶ በአብዛኛው ወይም በሙሉ በጥናቱ የሚሸፈኑ ትምህርት ቤቶች የመንግስት ወይም የህዝብ ብቻ ሊሆኑ ከቻሉ ከትምህርት ቤቶች አይነት የተለየ ባህሪይ ምክንያት በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አስተዋፅኦ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን ለማወቅ አያስችልም።

ይህ እንዳይሆንና የጥናቱን ሽፋን ለሁሉም ዞኖችና በጥናቱ መሸፈን ለሚገባቸው ለሁለቱም የትምህርት ቤት አይነቶች (የህዝብና የመንግስት) ለማዳረስ ሶስት የህዝብና ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በጥናቱ የሚሸፈኑ ትምህርት ቤቶችን አካባቢያዊ ስርጭትና የትምህርት ቤት አይነቶችን ሽፋን ሚዛናዊ ለማድረግ፥ በመጀመሪያ ዞኖችን በጎደሉና በሙሉ ቁጥር በመለየት፥ ለሁለቱ የትምህርት ቤት አይነቶች የጎደሎና የሙሉ ቁጥሮች ዕጣ ተጥሏል፡፡ በወጣው ዕጣ መሰረት ለህዝብ ትምህርት ቤቶች ባለ ጎደሎ ቁጥር ዞኖች ሲደርሱ፥ ለመንግስት ትምህርት ቤቶች በአንፃሩ ባለ ሙሉ ቁጥር ዞኖች ደርሰዋል፡፡ በዚህ መሰረት በዞን 1፥3 እና 5 ውስጥ ከሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ትምህርት ቤት በተራ ዕጣ ናሙና (Random Sampling ) ሲመረጥ በዞን 2፥4 ና 6 ውስጥ ከሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥም በተመሳሳይ መንገድ አንድ ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ፓናልና ከየዞኑ ትምህርት መምርያ ሱፐርቪዥን ክፍል በተገኙ መረጃዎች መሰረት የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምን በአግባቡ የማይጠቀሙና ቀደም ብሎ የአሰሳ ጥናት የተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች ከእጣ ውጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

### 3.2.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ ከተመረጡ ስድስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ 240 የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በተራ ዕጣ ናሙና ተመርጠው የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ካሉት የመጀመሪያ ደረጃ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡባቸው ሁለት አበይት ምክንያቶች አሉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ረዘም ላሉ አመታት (ቢያንስ ከስድስት አመታት በላይ) የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮን የመማር ልምድ ስላላቸውና

ለ. የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች አንፃራዊ በሆነ መልኩ በእድሜያቸውም ሆነ በትምህርት ደረጃቸው ከ7ኛ ክፍል በታች ባሉ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ካሉ ተማሪዎች የተሻለ ብስለት ስለሚኖራቸው የሚሰጡትም መረጃ የተሻለ አስተማማኝ ይሆናል ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ያልተመረጡት፥ ተማሪዎቹ ብሄራዊ ፈተና የሚወስዱ ስለሆኑና፥ በተለይም ይህ ጥናት በሚካሄድበት ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ወቅት የተማሪዎችም ሆነ የመምህራን ትኩረት ባለፉት የትምህርት ይዘቶች ክለሳ ላይ ስለሚሆን ለትምህርቱ በሬዲዮው ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ውሱን መሆኑን፥ የጥናቱ አቅራቢ ከመምህራኑ ባገኘው መረጃ መረዳት ስለቻለ ነው::

ለጥናቱ ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች መጠይቁን የሚሞሉ ተማሪዎች ብዛት የተወሰነው በየትምህርት ቤቱ ከሚማሩ አጠቃላይ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት አንፃር በተሰራ የሬሽዮ ቀመር መሰረት ነው:: በሬሽዮው ቀመር መሰረት ለየትምህርት ቤቱ የደረሰው የጽሁፍ መጠይቅ በስድስቱ ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ የ7ኛ ክፍል ምድቦች (ሴክሽኖች) ተከፋፍሎአል:: ከየምድብ ክፍሉ ተማሪዎች በተራ ዕጣ ናሙና ተመርጠው መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል::

ሠንጠረዥ 2፡- መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ስርጭት መግለጫ

| ዞን | የትምህርት ቤቱ ስም | ጠቅላላ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት | መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ዳግማዊ ብረሃን | 103 | 10 | 9.7 |
| 2 | እድገት በኅብረት | ·705 | 72 | 102 |
| 3 | ፍሬህይወት ቁጥር 2 | 354 | 36 | 10.17 |
| 4 | እንጦጦ አምባ | 527 | 53 | 10.1 |
| 5 | አፍሪካ አንድነት ቁጥር 1 | 371 | 38 | 10.24 |
| 6 | ገላን ቁጥር 1 | 304 | 31 | 10.20 |
| ድምር | 6 | 2364 | 240 | 10.15 |

የየክፍል ምድቡን የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በመጠየቅ በተገኘው መረጃ መሰረት የመስማት ችግር ያለባቸው፥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምን አዘውትረው በመገኘት የማይከታተሉና የዚህ አመት ትምህርት ከተጀመረ በኋላ ዘግይተው ከአዲስ አበባ መስተዳድር ክልል ውጭ የመጡ አዲስ ገቢ ተማሪዎች ከእጣ ውጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል::

### 3.2.3. የመምህራን አመራረጥ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የሰለጠኑና ለጥናቱ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሰባተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ አንድ አይነት ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው፥ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ሁሉ የመሰላቸውን ነፃ አስተያየት ሰጥተዋል። መምህራኑ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶችም በጽሁፍ ተመዝግቦ በአባሪ 5 ስር ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 3፡ ስለ መምህራን የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች ትንተና

| ፆታ | የትምህርት ደረጃ | | ስለትምህርት በሬዲዮ ስለጠና የወሰደ(ች) | የአገልግሎት ዘመን በአማካይ | 7ኛ ክፍል ያስተማሩበት አመት በአማካይ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዲፕሎማ | 12 + 1 | | | |
| ሴት | 1 | - | - | 20 | 8 |
| ወንድ | 3 | 3 | 1 | 21 | 11 |
| ድምር | 4 | 3 | 1 | 20 | 10 |

### 3.2.4. ከ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ውስጥ ለትንታኔ የቀረቡ ይዘቶች ናሙና አመራረጥ

ከ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘቶች ውስጥ የይዘት ትንተና የተደረገባቸው ይዘቶች የክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት የቀረቡት ፕሮግራም 18፥20 ና 21 የትምህርት ይዘቶች ናቸው። ፕሮግራም 19 የተዘለለው ይህ ፕሮግራም የተላለፈው መጋቢት 22 ቀን 1992 ዓ.ም. ሲሆን፥ ይህ ቀን ደግሞ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሄራዊ ፈተና ሳምንት ውስጥ ነው የዋለው። በተጠቀሰው ሳምንት (ከመጋቢት 18 -22 በነበሩት ቀናት ውስጥ) ደግሞ ትምህርት ቤቶች ዝግ በመሆናቸው ፕሮግራሙ ቢሰራጭም በጥቅም ላይ ባለመዋሉና ፕሮግራሙ ሲሰራጭም የክፍል ውስጥ ምልከታ ሊደረግበት ባለመቻሉ እንዲዘለል ተደርጓል።

## 3.3. የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች

በትምህርት በሬዲዮ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ ለሚደረግ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች፡- የክፍል ውስጥ ምልከታ ለጥናቱ በማብራሪያ የተደገፉ መረጃዎችን ይሰጣሉ ተብለው ለሚታመንባቸው የመስኩ ባለሙያዎች፥ መምህራን ተማሪዎች፥ ለፕሮግራም አዘጋጆች፥ ለርዕሳነ መምህራን በሚቀርብ የቃልና የጽሁፍ መጠይቅና በፕሮግራሞች ላይ በሚደረግ የይዘት ትንተና መሆናቸውን (Mohanety, 1994, 120; Prist, 1996,184) ይጠቁማሉ:: በዚህም መሰረት የዚህ ጥናት አቅራቢ የእነዚህን የመስኩን ባለሙያዎች አስተያየትና የዚህን ጥናት ዓላማና የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች በማገናዘብ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች ተጠቅሟል::

### 3.3.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በሳምንት አንድ ቀን አርብ ለከሰዓት በፊት ፈረቃ በ4ኛው ክፍል ጊዜ (ከ4:15-4.55) እና ለከሰዓት በኋላው ፈረቃ በ7ኛው ክፍለ ጊዜ (ከ8:45 - 9:25 ሰዓት ) ይተላለፋል:: ፕሮግራሙ በእነዚህ ክፍለ ጊዜያትና ሰዓታት ለ15 ደቂቃ ይሰራጫል:: ለክፍለ ጊዜው ከተመደበው 40 ደቂቃ ውስጥ 10 ደቂቃ ለቅድመ ትምህርት በሬዲዮ ተግባራትና 15 ደቂቃ ለድህረ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት በኋላ ተግባራት የሚውል ነው::

ለክፍል ውስጥ ምልከታ በተመረጡ ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ የ7ኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ በአንድ አንድ የክፍል ምድቦች (ሴክሺን) ውስጥ ለሶስት ክፍለ ጊዜያት የክፍል ውስጥ ምልከታው ተካሂዷል:: የክፍል ውስጥ ምለከታው የተካሄደባቸው ክፍሎች ከላይ በተጠቀሰው ዕለትና ሰዓት (ክፍለ ጊዜያት) የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ምድቦች ናቸው:: በዚህም መሰረት በጥዋቱ ፈረቃ በእንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 7ኛ "ሀ" ና "ለ" ምድቦች በአንድነት ሆነው የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም በሚከታተሉበት ክፍል ውስጥ ምልከታው ሲደረግ፥ በከሰዓት በኋላው ፈረቃ ደግሞ በአፍሪካ አንድነት ቁጥር 1 የመጀመሪያ ደረጃ የህዝብ ትምህርት ቤት በ7ኛ ክፍል ምድብ "ሠ"

ተካሂዷል። በእነዚህ ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ከዋናው አጥኚ ጋር ሁለት ረዳት አጥኚዎች አብረው በመሆን የክፍል ውስጥ ምልከታውን አካሂደዋል። በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት ሶስቱም ረዳት አጥኚዎች የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ ሞልተዋል። ረዳት አጥኚዎቹ ቀደም ሲል በመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከአስር አመታት በላይ በማስተማር በሥራ ላይ የቆዩ ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ ብአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመርያ ዲግሪ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ናቸው። የክፍል ውስጥ ምልከታው ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ስለ ጥናቱ ዓላማ በተለይም ስለ ክፍል ውስጥ ምልከታ ቅፁ አሞላል በጥናቱ አቀራቢ በቂ ገለፃ ተደርጎላቸዋል።

የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ ቀደም ብሎ በባለሙያዎች ታርሞና ተስተካክሎ በሁለት ትምህርት ቤቶች ለአንድ አንድ ክፍለ ጊዜያት የአሰሳ ጥናት ተካሂዶበታል። እንደገናም በአሰሳው ጥናት ካጋጠሙ ሁኔታዎች በመነሳት ደግሞ እንዲታረምና እንዲሻሻል ተደርጓል። ከዚያ በኋላ ቅፁ ለዋናው ጥናት የታሰቡ መረጃዎችን ሊያስገኝ እንደሚችል ከታመነበት በኋላ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይህ የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ ከ (Teshome, 1998,217) ሞዴል የተወሰደ ነው።

### 3.3.2. የጽሁፍ መጠይቅ

ብዙ ተጠኝዎችን ለመሸፈን የሚረዳው የጽሁፍ መጠይቅ ሌላው የዚህ ጥናት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ ነበር። ለጥናቱ በተመረጡ ስድስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 240 ተማሪዎች ተመርጠው መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል።

ከዋናው ጥናት ቀደም ካሉ የአሰሳ ጥናት በተደረገባቸው ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ 48 ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል። ቀደም ብሎ በተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡ 22 ዝግና 3 ክፍት ጥያቄዎች የአሰሳ ጥናቱ ከተደረገባቸውና በአራት የዩኒቨርሲቲው የቋንቋ መምህራን፥ በአንድ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ባለሙያና በሁለት የስነ-ልቦና የሁለተኛ አመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች እንዲገመገምና እንዲሻሻል ተደርጓል። በዚህ ሂደትም ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ጋር አግባብነት የሌላቸው ጥያቄዎች ተወግደዋል፤ ለጥናቱ ተገቢ መረጃዎችን ያስገኛሉ ተብለው የታመነባቸው ጥያቄዎች ታክለዋል፤ ግልፅነት

## 3.4. የመረጃዎች አተናተን ዘዴ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይህ ጥናት በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ደረጃ ለማወቅ የሚረዱ አራት የመረጃ ምንጮች የተጠቀመ ሲሆን ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች የተሰባሰቡ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል::

1. በአንድ የህዝብና በአንድ የመንግስት ትምህርት ቤት በተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በሚከተለው ሁኔታ ለመተንተን ተሞክሯል::

   ዋናው አጥኚና ሁለት ረዳት አጥኚዎች በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ለሶስት ለሶስት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት በተካሄዱ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች ወቅት በተሞሉ ቅፆች ውስጥ ለሰፈሩ 23 የመመዘኛ ነጥቦች የተሰጡ የምዘና ዋጋዎች ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል::

2. በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ ለተካተቱ ጥያቄዎች የቀረቡትን ምርጫዎች በመምረጥ የተሰጡ መልሶች ከከተሰባሰቡና በቁጥርም ከተወከሉ በኋላ÷ ወደ መቶኛ እንዲለወጡ ተደርጓል:: በዚህ ስሌት መሰረት ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎችን ውጤት በሌሎች የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶች አማካይነት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር በማዋሀድ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል::

3. ለጥናቱ በተመረጡ ስድስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አማርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩ መምህራን በቃለ መጠይቅ አማካይነት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተሞክሯል:: በቃለ መጠይቁ አማካይነት መረጃ እንዲሰጡ የተመረጡ መምህራንን በአንድ የተወሰነ ጊዜና ቦታ በአንድነት ማግኘት ስላለተቻለ÷ እያንዳንዱ መምህር በተመቸው ጊዜና ቦታ ቃለ መጠይቁ እንዲቀርብለት ተደርጓል:: እያንዳንዱ መምህር ለቀረቡለት ጥያቄዎች የሰጣቸው መልሶች በጽሁፍ ተመዝግበው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል::

4. በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ቁጥር 18÷20 እና 21 የቀረቡ ይዘቶች ለክፍሉ ደረጃ ከተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ/ማስተማሪያ መፃህፍት ጋር

ያላቸውን የይዘት ግንኙነት ለማየት ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በተጠቀሱት የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራሞች ውስጥ የቀረቡ ዝርዝር ይዘቶችን፥ በመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡ ተመሳሳይ ዝርዝር ይዘቶች ጋር በማወዳደር በይዘቶቹ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ለመተንተን ተሞክሯል።

በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ፥ የአቀራረብ ስልቶችም፥ ለቀረቡ ይዘቶች ያላቸውን ተስማሚነት ከተማሪዎችና ከመምህራን ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የክፍል መምህሩን ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ቀደም ብሎ ለማዘጋጀትና የክፍል መምህሩንና ተማሪውን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ለማሳተፍ ያለው ብቃት፥ ከክፍል መምህራንና ከተማሪዎች ከተገኘው መረጃ ጋር በማገናዘብ ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ለጥናቱ በተመረጡ መሳሪያዎች አማካይነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን በምዕራፍ አንድ ለተጠቀሱት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

### 4.1. በክፍል ውስጥ በምልከታ የተደረሰባቸው መረጃዎች ትንተና

በክፍል ምልከታው ወቅት ትኩረት የተደረገባቸው አራት አበትይ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ሀ. የመምህሩ ተግባር በቅድመ ትምህርት በሬዲዮ፥ የትምህርቱ ፕሮግራም በሚተላለፍበት ጊዜና ከትምህርት ፕሮግራም ስርጭት በኋላ፥

ለ. በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ፥

ጠ. የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብና

መ. የመማርያ ክፍሉና የትምህርቱ መቀበያ ሬዲዮ ሁኔታ ናቸው፡፡

የክፍል ውስጥ ምልከታው ክትትል የተደረገበት ቅፅ (Observation checklist) በጠቅላላው 23 የመመዘኛ/መገምገሚያ ነጥቦችን አካቷል፡፡ ክፍል ውስጥ ምልከታው መረጃ የተሰበሰበባቸው ሁለት ትምህርት ቤቶች አንድ የመንግስትና አንድ የህዝብ ትምህርት ቤት መሆናቸው በምዕራፍ ሶስት መገለፁ ይታወሳል፡፡ እነዚህም፡- ከመንግስት ትምህርት ቤቶች እነጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፥ ከህዝብ ትምህርት ቤቶች ደግሞ አፍሪካ አንድነት ቁጥር 1 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው የተመረጡት፡፡

## ሀ. እንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በምልከታ የተደረሰባቸው መረጃዎች ትንተና

ይህ ጥናት በተከናወነበት ጊዜ ትምህርት ቤቱ ከ1-8ኛ ክፍል በጠቅላላው 4454 ተማሪዎች ሲኖሩት፥ ከዚህ ውስጥም 527 ተማሪዎች ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርግባቸው የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በስምንት ምድብ/ሴክሽን ተመድበው የሚማሩ ሲሆን፥ አራት ምደቦች ትምህርታቸውን በጥዋቱ ፈረቃ ይከታተላሉ፤ የተቀሩት አራቱ ምደቦች ደግሞ ከሰዓት በኋላው ፈረቃ ይማራሉ። በሁለቱም ፈረቃ የሁለት ምድብ ተማሪዎች ናቸው ተጻብለው በአንድነት የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም የሚከታተሉት። የአንድ ምድብ የተማሪዎች አማካይ ቁጥር 69 ሲሆን በአንድ አዳራሽ ውስጥ የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም የሚከታተሉት ተማሪዎች ቁጥር በአማካይ 138 ናቸው።

በዚህ ትምህርት ቤት የክፍል ውስጥ ምልከታው የተካሄደው በጥዋቱ ፈረቃ ምድብ “ሀ” ና “ለ” በአንድ ላይ ሆነው ፕሮግራሙን በሚከታተሉበት አዳራሽ ውስጥ ነው። በእንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ የጥዋቱ ፈረቃ የተመረጠው፥ ያለ ዕጣ ነው። ምክንያቱም ሌላኛው የክፍል ውስጥ ምልከታ ሊደረግበት የተመረጠው አፍሪካ አንድነት ቁጥር 1 የህዝብ ትምህርት ቤት ፕሮግራምና ለጥዋት ፈረቃ የሚተላለፈው የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስለማይጣጣም፥ በዚህ ትምህርት ቤት (በአፍሪካ አንድነት ቁጥር 1) የክፍል ውስጥ ምልከታ ማካሄድ የሚቻለው ለከሰዓት በኋላው ፈረቃ በሚተላለፈው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ ብቻ በመሆኑ ነው።

ምልከታው በተካሄደበት በእንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፥ የመማርያ ክፍል/አዳራሽ ውስጥ፦ ጥቁር ሰሌዳ፥ የኤሌክትሪክ ሶኬት፥ ተማሪዎቹ የሚቀመጡበትና የሚፅፉበት ወንበርና ጠረጴዛ/ዴስክ፥ መምህሩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎቻቸውን የሚያስቀምጡበት ጠረጴዛ የለም። አምስት ከእንጨት የተሰሩ አግዳሚ ወንበሮች ብቻ የግድግዳውን ጥግ ይዘው ተቀምጠዋል። እነዚህም ወንበሮች ቀድመው የገቡ ተማሪዎች ለአምስት እየሆኑ ተጣበው ተቀምጠውባቸዋል። የክፍሉ ወለል አፈር ነው። አብዛኛው ተማሪ ደብተሩ ላይ

ተቀምጦ ትምህርቱን ይከታተላል:: ሌሎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ውጭ በመስኮት አካባቢ ቆመው ፕሮግራሙን ሲያዳምጡ፥ የተወሰኑ ተማሪዎች መቀመጫም ሆነ መቆሚያ በማጣታቸው ተመልሰው ሲሄዱ ይታያሉ:: በባትሪ ድንጋይ የሚሰራው ሬዲዮ ድምፅ በጥራት ይሰማል:: ሬዲዮኑ ከተማሪዎች ፊት ለፊት ካለው ግድግዳ ላይ ተደግፎ በቆመው ወንበር ላይ ነው የተቀመጠው:: የሬዲዮው አቀማመጥም ሆነ ጥራት ፕሮግራሙን ለመከታተል አመቺ ነው::

ይሁንና በክፍሉ ውስጥ ጥቁር ሰሌዳ ባለመኖሩ፥ በዕለቱ የሚተላለፈው የትምህርቱ ፕሮግራም ርዕስ እንኳን ልተፃፈም:: በትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ ውስጥ በክፍል መምህሩ እንዲከናወኑ የተጠቆሙት ተግባራትም በጥቁር ሰሌዳው አለመኖር አልተከናወኑም:: ለምሳሌ የመጀመሪያው የክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገበት መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. የተላለፈው 18ኛ ፕሮግራም ግጥም ነው:: በትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ ላይ ባለ አስራ ሁለት ስንኞች ግጥም በክፍል መምህሩ፥ ጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲጻፉ ቢጠቆምም አልተፃፉም::

የተማሪው ብዛትና የመማርያ ክፍሉ ሁኔታ ለትምህርት በሬዲዮው ምቹ ባለመሆናቸው ይመስለል ምልከታው በተካሄደባቸው ሶስቱም ቀናት (መጋቢት 15፥29 እና ሚያዝያ 6 ቀን 1992 ዓ.ም.) በትምህርት በሬዲዮው ስርጭት ወቅት የመምህሩ ተግባር ርዕሱን በቃል በመንገር፥ ሰዓት ጠብቆ ሬዲዮኑን በመክፈትና በማስተካከል፥ አልፎ ልፎ የክፍሉን ፀጥታ በመቆጣጠርና ተማሪዎች ፕሮግራሙን እንዲያዳምጡ በማበረታታት ላይ የተወሰነ ሆኖ ነው የታየው:: ይህም በመሆኑ በዚህ ጥናት በምዕራፍ ሁለት ውስጥ በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ በክፍል መምህሩ መከናወን የሚገባቸው ሰፋ ያሉ ተግባራትም ሆኑ፥ በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምርያ ውስጥ የተጠቀሱ የተወሰኑ ተግባራት ምልከታው በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት አልታዩም::

ለተማሪው የመቀመጫ ወንበር፥ አስደግፎ የሚፅፍበት ጠረጴዛና ጥቁር ሰሌዳ በክፍል ውስጥ ከሞላ ጎደልም እንኳን ተሟልተው አለመገኘታቸው በትምህርት በሬዲዮ የመማር/ማስተማር ሂደት ውስጥ በተማሪው ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አስከትሎ ታይቷል:: የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሙን ይከታተላሉ ተብለው ከታሰቡት 138 ተማሪዎች ውስጥ

ፕሮግራሙን እያዳመጡ ማስታወሻ የሚፅፉ ተማሪዎች ቁጥር በጣም ጥቂት ሆኖ ታይቷል፡፡ ቁጥራቸው በአማካይ ከ50 የማይበልጡ ተማሪዎች አግዳሚ ወንበር ላይና መሬት የተቀመጡት ታፋቸው ላይ አስደግፈው ሲጽፉ የቆሙትም ደብተራቸውን አንድ እጃቸው ላይ አስደግፈው ሲፅፉ ነው የተስተዋሉት፡፡ ከትምህርት በሬዲዮ ስርጭት በኋላ ከሬዲዮ መምህሩ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ለመመለስ አብዛኛው ተማሪ እጁን ያወጣል፡፡ ለተማሪዎች መልስ መስጫ ጊዜ ከሬዲዮ መምህሩ የሚሰጠው የጊዜ ፋታ አጭር ስለሆነ ለአንድ ጥያቄ ከሁለት ተማሪ መልስ በላይ ለመቀበል እንደማያስችል በምልከታው ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ያም ሆኖ አብዛኛው የክፍሉ ተማሪ ከክፍል መምህሩ ፈቃድ ሳይጠብቅ በአንድነት ድምፁን ከፍ አድርጎ ለጥያቄዎቹ ትክክኛ መልስ ሲሰጥ በምልከታው ወቅት ተመልክቷል፡፡

ተማሪዎች ከትምህርት በሬዲዮው መምህር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ያለ ክፍል መምህሩ ድጋፍ ፈጣንና ትክክለኛ መልስ የሚሰጡት በሁለት ምክንያቶች መሆኑን የጥናቱ አቅራቢ ለመረዳት ችሏል፡፡ አንደኛው ምክንያት የክፍል ምልከታው በተደረገባቸው የትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት የተላለፉ (በተለይ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ) የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘቶች ቀደም ብለው በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት በክፍል መምህሩ የቀረቡ በመሆናቸው ሲሆን ይህንንም ለክፍሉ ደረጃ የተዘጋጀውን የመማርያ/ማስተማሪያ መጽሀፍት በማመሳከር፥ የተማሪዎችን የማስታወሻ ደብተር በማየትና ከክፍል መምህሩ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለማወቅ ሲቻል ሁለተኛውም ምክንያት የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ከተማሪው ደረጃ በታች መሆኑን ከ7ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በእንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘው መረጃ ጠቅለል ባለ መልክ ሲታይ፦ የክፍል መምህሩ ተሳትፎ በትምህርት በሬዲዮ ቅድመ፥ጊዜና ድህረ ስርጭት ወቅት ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የተማሪው ተሳትፎም ከትምህርት በሬዲዮው መምህር የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በአብዛኛው ድምፅን በአንድነት ከፍ አድርጎ ከመመለስ ያለፈ አይደለም፡፡ በትምህርት በሬዲዮው ፕሮገራም ለተማሪው ተሳትፎ ማነስም፦ የመማርያ ክፍሉ ምቹ አለመሆን፥ የፕሮግራሙ አቀራረብ ከተማሪው ደረጃ በታች መሆንና በተለይም በመማርያ ክፍሉ ውስጥ የጥቁር ሰሌዳ ባለመኖሩ

ምክንያት የክፍል መምህሩ ተሳትፎ ውሱን ሆኖ መታየት እንደሆነ በተደረጉት የክፍል ምልከታዎች ለመረዳት ተችሏል።

ለ. በአፍሪካ አንድነት ቁጥር 1፥ የመጀመሪያ ደረጃ የህዝብ ትምህርት ቤት በምልከታ የተደረሰባቸው መረጃዎች ትንተና

በአፍሪካ አንድነት ቁጥር 1 የመጀመሪያ ደረጃ የህዝብ ትምህርት ቤት የክፍል ምልከታው በተካሄደበት ጊዜ በትምህርት ቤቱ ከ1-8ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ 2067 ተማሪዎች አሉ። ከተጠቀሰው የተማሪ ቁጥር ውስጥም 391ዱ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በአምስት ምድብ (ሴክሽን) የተመደቡ ሲሆን በእያንዳንዱ ምድብም በአማካይ 78 ተማሪዎች ትምህርታቸውን ይከታተላሉ። እያንዳንዱ ምድብም የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሙን የሚከታተለው በመደበኛው የመማርያ ክፍል ውስጥ ነው። ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያከናውነው በአንድ የትምህርት ፈረቃ ሲሆን፥-ትምህርት ቤቱ መደበኛው የመማር ማስተማር ሥራውን የሚጀምረውም ጥዋት በ2:15 ነው።

መደበኛው የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስርጭት ጥዋት በ2:00 ሰዓት የሚጀምር በመሆኑ፥ መደበኛውን የመማር ማስተማር ሂደት ከሁለት ሰዓት በኋላ ዘግይተው የሚጀምሩ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከሰዓት በፊት የሚተላለፈውን የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በቀጥታ መጠቀም አይችሉም። የአፍሪካ አንድነት ቁጥር አንድ የመጀመሪያ ደረጃ የህዝብ ትምህርት ቤት ለዚህ ችግር እንደ መፍትሄ እድርጎ የሚጠቀመው ከሰዓት በፊት የሚተላለፉ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞችን በቴፕ ክር መዝግቦ በማቆየት በመደበኛው የትምህርት ክፍለ ጊዜ መጠቀም ነው። ከሰዓት በኋላ የሚተላለፈውን የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ግን በቀጥታ መጠቀም የሚያስችል የፕሮግራም ቅንጅት ነው ያለው። ይህም በመሆኑ በዚህ ትምህርት ቤት የክፍል ምልከታው የተካሄደው ከሰዓት በኋላ ከ8:45-9:25 ሰዓት ባለው 7ኛ ክፍለ ጊዜ ነው። በትምህርት ቤቱ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ስርጭት መሰረት በዚህ (7ኛው) ክፍለ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የ7ኛ "ሠ" ምድብ ክፍል ተማሪዎች ብቻ በመሆናቸው፥ የክፍል ውስጥ ምልከታውም ያለ አማራጭ የተካሄደው በዚሁ ክፍል ውስጥ ነው።

በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥ ጥቁር ሰሌዳ፥ ሶኬት፥ የክፍል መምህሩ ወንበርና ጠረጴዛ፥ የተማሪዎች ዴስክና የክፍሉ ንፅህና በተለይም ከእንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር ሲነፃፀር የተሟላ ነው። በአንድ ዴስክ ላይ ሦስት ተማሪዎች ናቸው የሚቀመጡት። አሁንም አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ተማሪዎቹ ብዙም ሳይጨናነቁና ሳይጣበቡ ነው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበረው።

በእንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደተደረገው በአፍሪካ አንድነት የህዝብ ትምህርት ቤትም የክፍል ውስጥ ምልከታው የተካሄደው በዚህ ጥናት አቅራቢና ከሁለቱ ረዳት አጥኚዎች ጋር በመሆን ነው። ምልከታው በተደረገባቸው ሶስቱም ክፍለ ጊዜያት የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም መቀበያ አቀማመጥና ጥራት የተዋጣላት ሆኖ ታይቷል። ምልከታው የተደረገባቸው ቀናትና ፕሮግራሞች በእንጦጦ አምባ ምልከታ ከተካሄደባቸው ቀናትና ፕሮግራሞች ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

መጋቢት 15 እና ሚያዚያ 6 ቀን አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ተደርጎና የትምህርቱ መቀበያ ሬዲዮም ተዘጋጅቶና ተከፍቶ ፕሮገራሙ ተላልፏል። መጋቢት 29 ቀን የተላለፈው ፕሮግራም ግን ሬዲዮ ጣቢያውን አስቀድሞ ባለማስተካከል ምክንያት በተፈጠረ ችግር ለአማራ ክልል የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚተላለፈው የአማርኛ ቋንቋ ፕሮግራም መደመጥ ከተጀመረ በኋላ እንዲቋረጥ ተደርጓል። ከዚያ በኋላ የሬዲዮ ጣቢያው እስኪስተካከል ድረስ አብዛኛው የዕለቱ ትምህርት ስርጭት ስለተገባደደ፥ ለሌሎች ምድብ ክፍሎች ታስቦ ከሰዓት በፊት ከተላለፈው ፕሮግራም የተቀዳውን የቴፕ ካሴት እንዲደመጥ በማድረግ የተፈጠረውን ችግር ማቃለል ተችሏል።

ምልከታው በተካሄደባቸው ሶስቱም የትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት የክፍል መምህሩ ሲያከናውኗቸው የነበሩት ተግባራት ተመሳሳይ ሆነው ታይተዋል። ከትምህርት በሬዲዮው ስርጭት በፊት የፕሮግራሙን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመፃፍ ያለፈውን የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ርዕስም በቃል ለተማሪዎቹ ለማስታወስ ሞክረዋል። ከዚህ አልፎ በክፍል መምህሩ ስለአለፈው የትምህርት ይዘት የተደረገ ክለሳም ሆነ፥ ስለ እለቱ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት መግቢያ የሚሆን ገለፃ ሲሰጥ አልታየም። በትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምርያ ከትምህርት በሬዲዮ በፊት በክፍል መምህሩ መከናወን (በጥቁር ሠሌዳው ላይ መፃፍ) ያለባቸው

የተወሰኑ ተግባራት ቢጠቀሙም አልተተገበሩም፡፡ የክፍል መምህሩ ተማሪዎች በፀጥታ የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም እንዲያዳምጡና ማስታወሻም እንዲፅፉ ማሳሰቢያ ቢሰጡም ክፌሉ ውስጥ በመዘዋወር ያደረጉት ክትትልና ቁጥጥር ባለመኖሩ የተወሰኑ ተማሪዎች የሌላ ትምህርት ደብተር ሲዋዋሱ ሲገለብጡና የቤት ስራ ሲሰሩ ይታያሉ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛው የክፍሉ ተማሪ የትምህርት በሬዲዮ ማስታወሻ ደብተሩን አውጥቶ÷ ያዳመጠውን ያህል ሲፅፍ ይታያል፡፡

በአማርኛው ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ወቅት የክፍል መምህሩ ከሬዲዮ መምህሩ ለተማሪዎቹ በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲፅፉላቸው የተጠየቁትን በመፃፍና ከሬዲዮ መምህሩ ለተማሪዎች ለቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመቀበል የተጠቀሙትን ተግባር ሲያከናውኑ ታይተዋል፡፡

ከትምህርት በሬዲዮው ስርጭት በኋላ ባለው ጊዜ የክፍል መምህሩ ሲያከናውኑ የታዩት ተግባር በጣም ውሱን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምልከታው በተደረገባቸው በሶስቱም የትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ተበረታታዋል፡፡ ከዚያ በተረፈ በትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምርያ ላይ በክፍል መምህሩ እንዲከናወኑ የተጠቀሙ ተግባራት ሲከናወኑ አልተስተዋሉም፡፡ ከትምህርት በሬዲዮ ይዘት ስርጭት ለጥቆ በክፍል መምህሩ የፕሮግራሙ ዋና ዋና ነጥቦች÷ መከለስ÷ ተማሪዎች ትምህርቱን መከታተላቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ነጥቦችን በጥያቄ መልክ በማንሳት÷ ትምህርቱን ማጠቃለል÷ ትምህርቱን ለማዳበር የሚረዱ የተለያዩ የመልመጃ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ለተማሪዎች የክፍልም ሆነ የቤት ሥራ መስጠትና ሌሎችም በትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የተጠቀሙ ተግባራት መከናወን ሲገባቸው÷ ምልከታው በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት እነዚህ ተግባራት ከሞላ ጎደልም ቢሆን ሲተገበሩ አልታዩም፡፡ እነዚህም በትምህርት በሬዲዮው ክፍለ ጊዜ በክፍል መምህሩ መከናወን ሲገባቸው ከሞላ ጎደል እንኳን ቢሆን ባለመከናወናቸው የታዩ ድክመቶች በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አስተዋፅኦ ላይ የሚኖራቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል የጥናቱ አቅራቢ ይገምታል፡፡

አብዛኞቹ የክፍሉ ተማሪዎች ያለ ክፍል መምህሩ በቂ ክትትልና ቁጥጥር የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሙን በፀጥታ ያዳምጣሉ÷ ማስታወሻ ለመያዝ ይሞክራሉ÷ ከሬዲዮ መምህሩ

ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሽቀዳደማሉ (ብዙውን ጊዜም ለመመለስ እደሉ ሳይሰጣቸው መልሱን በአንድ ላይ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይመልሳሉ) ፥ እነዚህ በትምህርት በሬዲዮው ክፍለ ጊዜ በተማሪዎች የሚታዩ ተሳትፎዎች ተማሪዎች ለፕሮግራሙ ፍላጎት እንዳላቸው ይጠቁማሉ።

የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ተማሪዎችን እያዝናና የማስተማር (በትምህርቱ ሂደት ጣልቃ አዝናኝ ቀልዶችንና አባባሎችን የመጠቀም) አዝማሚያ እንደሌለ ከሬዲዮ ትምህርቱም ሆነ ከትምህርት በሬዲዮው ንድፍ ለመረዳት ተችሏል። የሬዲዮ መምህሩ ድምፅ ፈጠን ማለትና ለተማሪው ተሳትፎ (መልስ ለመስጠት) የሚሰጠው የጊዜ ፋታ መጥበብ በተማሪው የማስታወሻ አወሳሰድና ሌላም ተሳትፎው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሲያስከትል ታይቷል።

በትምህርት በሬዲዮው ስርጭት ወቅት የሬዲዮ መምህሩ መግለፅ የጀመረውን ሀሳብ ሳይጨርስ ተማሪዎቹ ከአፉ ቀልበው፥ ሀሳቡን ቀድመው በትክክል ሲቋጩትና የሚያቀርበውንም ጥያቄ እንዲሁ ሳይጨርስ ቀድመው ሲመልሱ ተስተውለዋል። ይህ ሁኔታ በዚህ ክፍል ጎላ ብሎ ቢታይም በእንጦጦ አምባ የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤትም ታይቶ እንደነበር ተገልጿል። ተማሪዎቹ የትምህርት በሬዲዮኑን ይዘቶች እንዴት እንደዚህ ቀድመው ለማወቅ እንደቻሉ ለክፍል መምህሩ ለአቶ ዓለሙ መተኪያ ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር። እሳቸውም እንደገለፁልኝ በመማርያ/ማስተመአርያ መጻህፍቱ ውስጥ በቀረቡት ይዘቶች ቅደም ተከተል መሰረት እነዚህን በትምህርት በሬዲዮ የቀረቡ ይዘቶች በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርቱ እንዳስተማሯቸው፥ በይዘቶችም ላይ ጥያቄዎችን በማውጣት እንደፈተኗቸው ገልፀውልኛል። መምህሩ በተጨማሪም የመማርያ/ማስተማሪያ መጻህፍቱም ሆኑ የትምህርት በሬዲዮ ይዘትና አቀራረብ ከተማሪዎች ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ እንደሆነ፥ በተለይም አራተኛና አምስተኛ ክፍል እያሉ ከተማሩት ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይህ የ7 ክፍል እንደሚቀል አመልክተዋል። የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ ከተማሪዎቹ ደረጃ በታች መሆን አለመሆኑ እራሱን የቻለ ጥናት የሚያሻው ቢሆንም፥ በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት በክፍል መምህሩ የቀረበን ይዘት እንደገና እንደ አዲስ ይዘት በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ማቅረቡ ግን በመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርትና በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ላይ ተገቢ ቅደመ ዝግጅትና ቅንጅታዊ አሰራር እንዳልነበር

ይጠቁማል:: ይህ ደግሞ በተማሪው የትምህርት በሬዲዮ ፍላጎት ላይና በትምህርት ክፍለ ጊዜያት ብክነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል::

## 4.2. በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት ከተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

ለጥናቱ ከተመረጡ ስድስት ትምህርት ቤቶች የተመረጡ 240 ተማሪዎች መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉት በጥናቱ አቅራቢ አማካይነት ነው:: የጥናቱ አቅራቢ የየትምህርት ቤቱን የሥራ ኃላፊዎች በማስፈቀድ መጠይቁን እንዲሞሉ የተመረጡትን ተማሪዎች ለብቻቸው አንድ ክፍል/አዳራሽ ውስጥ በማስገባትና በመጠይቁ ውስጥ ለቀረቡ ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ በመስጠት አስሞልቷል::

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ በተማሪዎች ዘንድ ያለውን ተቀባይነት/ማራኪነት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አንዱ መሆኑ ይታወቃል:: በመሆኑም የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት በሬዲዮው ፕሮገራም ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በቀረቡ ጥያቄዎች አማካይነት የተገኙ መረጃዎችን ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ ይመለከቷል::

ሠንጠረዥ 4:- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ በተማሪዎች ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ደረጃ ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ

| ተቁ | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም ከፍላጎትህ(ሽ) ጋር የመጣጣሙ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | 29 | 12.08 | 35 | 14.58 | 75 | 31.25 | 61 | 25.42 | 40 | 16.67 |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም አቀራረብ ማራኪነት ደረጃ ምን ያህል ነው? | 38 | 15.83 | 30 | 12.50 | 62 | 25.83 | 76 | 31.67 | 34 | 14.17 |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም አቀራረብ የማዳመጥ ትኩረትህ(ሽን) የመሳብ(የመመሰጥ) ደረጃው ምን ያህል ነው? | 36 | 15 | 32 | 13.33 | 57 | 23.75 | 75 | 31.25 | 40 | 16.67 |
| 15 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም አቀራረብ ተማሪዎችን አያያዝና የማስተመአር ብቃቱ ምን ያህል ነው? | 27 | 11.25 | 24 | 10 | 58 | 24.17 | 67 | 27.92 | 64 | 26.67 |

በሠንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም በተማሪዎች ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ለማወቅ አራት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከመጠይቁ በተገኘው መረጃ መሰረትም ፕሮግራሙ በተማሪዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነት ጎልቶ እንዳልታየ ይጠቁማል፡፡ በዚህ መሰረት "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ከፍላጎትህ(ሽ) ጋር የመጣጣሙ ሁኔታ ምን ል ነው?" ተብሎ የቀረበውን ጥያቄ ከመለሱት 240 ተማሪዎች ውስጥ 75(31.25) ተማሪዎች ፕሮግራሙ ከፍላጎታቸው ጋር የመጣጣሙ ሁኔታ መካከለኛ መሆኑን ሲጠቁሙ 61(25.42) ተማሪዎች ዝቅተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ለጥያቄው ከቀረቡት አምስት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪ መካከለኛና ዝቅተኛ ነው የሚል አመለካከት ሲኖረው፥ ከዚያ ቀጥሎ 40(16.67) ተማሪ በጣም ዝቅተኛ ነው፤ 35(14.58) ተማሪ ከፍተኛ ነው 29(12.08) ተማሪ በጣም ከፍተኛ ነው የሚል አመለካከት እንዳለው ተጠቁሟል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ነጥብ ላይ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የመጣጣሙ ሁኔታ ከአማካይ በታች እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም አቀራረብ ማራኪነት ደረጃ በተመለከተ በተራ ቁጥር 4 ላይ በቀረበው ጥያቄ አማካይነት ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም፥ በተራ ቁጥር 3 ላይ በቀረበው ጥያቄ አማካይነት ከተገኘው መረጃ ጋር ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የፕሮግራሙን አቀራረብ ማራኪነት ደረጃ በተመለከተ 76(31.67) ተማሪዎች ዝቅተኛ ነው፤ 62(25.83) ተማሪዎች መካከለኛ ነው፥ 38(15.83) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ ነው፥ 34(14.17) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ ነው፥ 30(12.50) ከፍተኛ ነው በማለት ያላቸውን አመለካከት ጠቁመዋል፡፡ መጠይቁን ከሞሉት ጠቅላላ ተማሪዎች አብላጫ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች የትምህርት በሬዲዮው ማራኪነት ደረጃ መካከለኛና ዝቅተኛ ነው የሚለውን ሀሳብ ማመልከታቸው የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ በተማሪዎቹ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እምብዛም እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

የትምህርት በሬዲሮው ፕሮግራም አቀራረብ የተማሪዎችን የማዳመጥ ትኩረት የመሳብ(የመመስጥ) ኃይሉ ከፕሮግራሙ አቀራረብ ማራኪነት ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎችም ይህንኑ ነጥብ በተመለከተ ያላቸው አመለካከት ቀደም ብሎ

ከተተነተነውና በተራ ቁጥር 4 ላይ ከቀረበው ነጥብ ጋር ተቀራራቢ መሆኑን ለ8ንተኛው ጥያቄ የሰጡት መልስ ያመለክታል፡፡

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ተማሪዎችን እያዝናና የማስተማር ብቃቱ ከዚህ በላይ በቁጥር 3፥4 እና 8 ከቀረቡት ነጥቦች ይበልጥ ዝቀተኛ መሆኑን፥ በሠንጠረዡ ተራ ቁጥር 15 ስር ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት መልስ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት ፕሮገራሙ ተማሪዎችን እያዝናና የማስተማር ብቃቱን በተመለከተ የተማሪዎች አመለካከት በቅደም ተከተል 67(27.92) ተማሪዎች ዝቅተኛ ነው፥ 64(26.67) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ ነው፥ 58 (24.17) ተማሪዎች መካከለኛ ነው፥ 27(11.25) በጣም ከፍተኛ ነው እና 24(10%) ተማሪዎች ከፍተኛ ነው የሚል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ በተማሪዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ታስቦ ለቀረቡ ጥያቄዎች አንፃራዊ በሆነ መልኩ የአብዛኛው ተማሪ አመለካከት "ዝቅተኛ" ና "መካከለኛ" በተሰኙት አማራጮች ላይ ማመዘኑ የፕሮግራሙ አቀራረብ በተማሪዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነት ዝቅተኛ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

**ሠንጠረዥ 5፡- የ7ኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ከተማሪው ደረጃ አኳያ ያለውን የአቀራረብ ብቃት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቀተኛ ነው | | በጣም ዝቀተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ደረጃህን(ሽን) የመመጠኑ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | 23 | 9.58 | 29 | 12.08 | 96 | 40 | 48 | 20 | 44 | 18.33 |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ግልፅነት ደረጃ ምን ያህል ነው? | 74 | 30.83 | 54 | 22.50 | 76 | 31.67 | 25 | 10.42 | 11 | 4.58 |
| 12 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መምህር(መምህራን) ድምፅ አግካይ ፍጠነት ተስማሚነት ደረአ ምን ያህል ነው? | 73 | 30.42 | 68 | 28.33 | 37 | 18.50 | 49 | 20.42 | 13 | 5.42 |
| 13 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ወቅት ለተሳትፎ(መልስ ለመስጠት፥ ጥያቄ ለመጠየቅና አስተያየት ለመስጠት የሚሰጣችሁ የጊዜ ሩታ ተስማሚነት ደረጃ ምን ያህል ነው? | 13 | 5.42 | 21 | 8.75 | 56 | 23.33 | 62 | 25.83 | 88 | 356.67 |
| 17 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ በውይይት ሲተርብ የአንደኛው ተወያይ ከሌላኛው ተወያይ በግልፅ ተለይቶ የመታወቅ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | 76 | 31.67 | 76 | 31.67 | 69 | 28.75 | 13 | 5.42 | 6 | 2.50 |

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ በአቀራረቡ የተማሪውን ደረጃ ምን ያህል እንደሚመጥን ለማወቅ ከቀረበው ጥያቄ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ከተሰጡት አምስት የአማራጭ መልሶች ቁጥራቸው በዛ ያለው (96(40%)ተማሪዎች መካከለኛ ነው ሲሉ፥ 48(20%) እና 44(18.33) ተማሪዎች ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት አመልክተዋል። አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ቁጥራቸው አነስ ያለ ተማሪዎች ማለትም 23(9.58) እና 29(12.08) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ በማለት አመልክተዋል። መጠይቁን ለሞሉ ተማሪዎች ይህን ጥያቄ በተመለከተ በጥናቱ አቅራቢ በተሰጣቸው ማብራሪያ መሰረት በጣም ከፍተኛ ነው ወይም ከፍተኛ ነው ካሉ የትምህርቱን አቀራረብ ክብደት ማመልከታቸው እንደሆነ፥ መካከለኛ ነው ካሉ፥ የአቀራረቡ ክብደት አማካይ መሆኑንና ዝቅተኛ ነው ወይም በጣም ዝቅተኛ ነው ካሉ ግን አቀራረቡ ቀላልና ከደረጃቸው በታች መሆኑን ማመልከቻው እንደሆነ ተነግሯቸዋል።

ከዚህ አኳያ ይህ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ ከመመጠን አኳያ ለአብዛኛው ተማሪ አማካይና ዝቅተኛ መሆኑ ተመልክቷል። ይህ መረጃ በክፍል ውስጥ ከተደረጉ ምልከታዎችና መምህራኑ ከሰጡት አስተያየት ከተገኙ መረጃዎች ጋር መጠነኛ ልዩነት ታይቶበታል። ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን በሙሉ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ከተማሪዎች ደረጃ በታች መሆኑን ሲያመለክቱ፥ በተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎችም በተገኘው መረጃ የትምህርቱ አቀራረብ ከተማሪው ደረጃ፥ በላይ ባለመሆኑ ትምህርቱን ለመረዳት ሲቸገሩ አልታዩም፥ እንዲያውም በአብዛኛዎቹ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች ተማሪዎቹ ከትምህርት በሬዲዮው መምህር ቀድመው የትምህርቱን ይዘት በአንድ ድምፅ ሲናገሩ ነበር የተስተዋሉት።

በዚህ መሰረት በተማሪዎቹ አመለካከት የትምህርት በሬዲዮው አቀራረብ ደረጃቸውን የመመጠኑ ሁኔታ መካከለኛ ነው ወደሚለው አዝማሚያ የሚያደላ ቢመስልም፥ ዝቅተኛ ነው ወይም በጣም ዝቅተኛ ነው የሚለው አመለካከት፥ በጣም ከፍተኛ ነው ወይም ከፍተኛ ነው ከሚለው አስተያየት ጎላ ያለ ልዩነት ማሳየቱ፥ ከክፍል ውስጥ ምልከታዎችና ከመምህራኑ ከተገኙ መረጃዎች ጋር ተዳምሮ የፕሮግራሙ አቀራረብ ከተማሪዎች ደረጃ በታች መሆኑን ያመላክታል።

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮውን አቀራረብ ግልፅነት ደረጃ ለማወቅ ታስቦ በተራ ቁጥር 11 ለቀረበው ጥያቄ ከተማሪዎቹ የተገኘው መረጃ የፕሮግራሙን አቀራረብ ግልፅነት ይጠቁማል:: ከቀረቡት አምስት አማራጮች ውስጥ አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ሲታይ ቁጥሩ በዛ ያለው ተማሪ አሁንም የገለልተኛነትን አመለካከት አዝማሚያ የሚያመለክተውን "መካከለኛ ነው" የተሰኘውን 76(31.67) ተማሪ ቢመርጥም፥ የፕሮግራሙ ግልፅነት በጣም ከፍተኛ ነውና ከፍተኛ ነው በማለት የመለሰው 128(53.33) ተማሪ፥ የፕሮግራሙ ግልፅነት ዝቀተኛ ነውና በጣም ዝቅተኛ ነው ብሎ ከመለሰው 36(15%) ተማሪ ጋር ሲነፃፀር፥ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ለተማሪው ግልፅ መሆኑን ያመለክታል::

የትምህርት በሬዲዮው አቀራረብ ድምፅ አማካይ ፍጥነት ተስማሚነት ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ከተማሪዎቹ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል:: በዚህም መሰረት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው 73(30.42) እና 68(28.33) ተማሪዎች የፕሮግራሙ ድምፅ አማካይ ፍጠነት ተስማሚነት ደረጀ በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ነው በማለት ሲያመለክቱ 37(18.50) ተማሪዎች መካከለኛ ነው የሚል አመለካከት እንዳላቸው ተመልክቷል:: በአንፃሩ 49(20.42) እና 13(5.42) ተማሪዎች የፕሮግራሙ የድምፅ ፍጥነት ተስማሚነት ደረጃ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት አመልክተዋል::

ይህ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ በተደረጉት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች ከተገኘው መረጃ ጋር ተማክሉ ሲታይ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቅራቢዎች አማካይ የድምፅ ፍጥነት ለተማሪዎቹ ደረጃ የሚስማማ/የሚመጥን ሆኖ ተገኝቷል::

በትምህርት በሬዲዮው ስርጭት ወቅት ለተማሪዎች ተሳትፎ የሚሰጠው የጊዜ ፋታ ዝቅተኛ ሆኖ መገኘቱን ተማሪዎቹ የሰጡት መረጃ ጠቁሟል:: 88(36.67%) እና 62(25-83%) ተማሪዎች የፕሮግራሙ አቅራረብ ለተማሪዎች ተሳትፎ የሚሰጠው የጊዜ ፋታ በጣም ዝቅተኛና ዝቀተኛ ነው የሚለውን አመልክቷል:: መጠይቁን ከሞሉ 240 ተማሪዎች ውስጥ 150(62.50%) ተማሪዎች የፕሮግራሙ አቀራረብ ለተማሪዎች ተሳትፎ የሚሰጠው የጊዜ ፋታ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ማመልከታቸው፥ 56(23.33%) ተማሪዎች የተስማሚነቱ ደረጃ አማካይ (መካከለኛ ነው ማለታቸውና 13(5.42) እና 21(8.75) ያህሉ በድምሩም 34(14.17) ተማሪዎች

ብቻ በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ነው ማለታቸው የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ለተማሪዎች ተሳትፎ የሚሰጠው የጊዜ ፋታ ዝቅተኛ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ይህ መረጃ በክፍል ውስጥ በተደረጉ ምልከታዎችና ከ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዘንድ ከተገኙት መረጃዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በአቀራረቡ ተማሪዎችን ለማሳተፍ የሚሰጠው የጊዜ ፋታ እጥረት ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ንድፍ ላይ በተደረገው የይዘት ትንተናና በተደረጉት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች በተገኘው መረጃ መሰረት ፕሮግራሙ በውይይት ሲቀርብ ተወያዮቹ መምህርና ተማሪ፥ አባትና ልጅ፥ ወንድና ሴት መሆናቸው ተመልክቷል፡፡ በዚህ አይነቱ ስብጥር የሚደረግ ውይይትም የተወያዮችን ድምፅ ለይቶ ለማወቅና የውይይቱንም ጭብጥ ለመረዳት አወንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ክለሳ ድረሳናት እንደሚያመለክቱም በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አኳያ በዚህ ነጥብ ላይ ተማሪዎች ስለ 7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በቀረበው ተራ ቁጥር 17 ላይ ለቀረበው ጥያቄ በሰጡት መልስ አብዛኞቹ ተማሪዎች የፕሮግራሙ አቀራረብ በዚህ መልክ ጉልህ ችግር እንደሌለበት አመልክተዋል፡፡ በዚህ መሰረትም 76(31.67) እና 76(31.67)ተማሪዎች የተወያዮች በግልፅ ተለይቶ የመታወቃቸው ሁኔታ በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ነው የሚል አመለካከት እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ ከ240 ተማሪዎች 156(63.33) ተማሪዎች በዚህ ነጥብ ላይ ያላቸው አመለካከት አወንታዊ መሆን፥ 69(2.75) ተማሪዎች መካከለኛ ነው የሚል አመለት መታየቱና 13(5.42) እና 6(2.50) ተማሪዎች በድምሩ 19(7.92) ተማሪዎች ብቻ አሉታዊ አመለካከት እነዳላቸው መታየቱ፥ ከላይ እንደተጠቀሰው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ በዚህ ነጥብ ዙሪያ ጉልህ ችግር እንደሌለበት አመልክቷል፡፡

ለአጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስኬታማነት የተማሪው ተሳትፎ ጉልህ ድርሻ እንዳለው በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ መጠቀሱ ይታወሳል፡፡ በዚህ መሰረት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ተማሪውን የማሳተፍ ብቃቱ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ጥቅም ላይ ከዋሉት መሳሪያዎች አንዱ የጽሁፍ መጠይቅ ነው:: በጽሁፍ መጠይቁ አማካይነት በዚህ ነጥብ ዙርያ ተማሪዎች ስላላቸው አመለካከት ፍንጭ ለማግኘት የሚረዱ ሁለት

ጥያቄዎች ቀርበው ነበር፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ተመልክተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 6:- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያለውን ብቃት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቅተኛ ነው | | በጣም ዝቅተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 5 | በትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ጊዜ የተማራችሁትን ትምህርት ከትምህርት ስርጭቱ በኋላ በግልም ሆነ በቡድን መልመጃዎችን በመስራት የመለማመዳችሁ ሁኔተአ ምን ያህል ነው? | 18 | 7.5 | 27 | 11.25 | 31 | 12.92 | 47 | 19.58 | 117 | 48.75 |
| 14 | የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ተማሪዎችን የማሳተፍ ብቃቱ ምን ያህል ነው? | 21 | 8.75 | 14 | 5.83 | 71 | 29.58 | 86 | 35.83 | 48 | 20 |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የቀረበውን የትምህርት ይዘት በግልም ሆነ በቡድን ልምምድ እንደማያዳብሩት ከተማሪዎቹ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ትምህርት 18(7.5) እና 27(11.25%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ ወይም በድምሩ 45(18.75%) ተማሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ በግልም ሆነ በቡድን እንደሚለማመዱት ሲያመለክቱ 31(12.92) ተማሪዎች መካከለኛ በሆነ ሁኔታ እንደሚለማመዱት አመልክተዋል፡፡ ከሌላው አንፃር 48(19.58%) እና 117(48.75) ያህሉ ተማሪዎች ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሆነ ሁኔታ ወይም በድምሩ 194(80.83%) ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ በልምምድ እንደሚያዳብሩት አመልክተዋል፡፡

በተደረጉት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች እንደተስተዋለው በፕሮግራሙ ስርጭት ወቅት ከሬዲዮ መምህሩ የሚሰነዘሩ የተወሰኑና ተማሪው ያዳመጠውን የትምህርት ይዘት መረዳቱን ለማወቅ ከሚቀርቡና ተማሪዎችም ያለ ብዙ ችግር ተሽቀዳድመው በአንድነት ከሚመልሷቸው ጥያቄዎች ባሻገር፥ ከትምህርት በሬዲዮው ስርጭት በኋላ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚለማመዱባቸው መልመጃዎች እንዳልነበሩ ተመልክቷል፡፡ በትምህርት ፕሮግራሙ ንድፍ ላይ

በተደረገው የይዘት ትንተና የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በላይ በዚህ ነጥብ ዙርያ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ከተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎችና ከፕሮግራሙ ንድፍ የይዘት ትንተና ከተገኙ መረጃዎች ጋር ተዳምሮ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ተማሪዎች የሚማሯቸውን የቋንቋ ክሂሎች በልምምድ እንዲያዳብሩ በሚረዱ መልመጃዎች ያልተደገፈ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ተማሪዎን ለማሳተፍ ያለውን ብቃት ለማወቅ በቀረበው ጥያቄ አማካይነት ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም የውጤቱን አሉታዊነት የሚጠቁም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎችም የተማሪዎች ተሳትፎ በትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ወቅት ከትምህርት በሬዲዮው መምህር ለሚቀርቡ የወዲያው ጥያቄዎች በአንድነት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለክፍል መምህራቸው በሚሰጡት መልስ የተወሰነ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከዚያ አልፎ በቅድመም ሆነ በድህረ ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ጊዜ የተማሪው ተሳትፎ የተገደበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ነጥብ ዙሪያ ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ መሰረትም 21(8.75%) እና 14(5.83) ተማሪዎች የፕሮግራሙ ተማሪዎችን የማሳተፍ ብቃት በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ነው ወይም ጠቅለል ባለ መልኩ 35 (14.58%) ተማሪዎች ብቻ ከፍተኛ ነው ሲሉ 71(29.58%) ተማሪዎች መካከለኛ ነው ብለዋል፡፡ በሌላ በኩል አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ማለትም 86(35.83%) እና 48(20%) ተማሪዎች ፕሮግራሙ ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያለው ብቃት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ወይም በድምሩ 134(55.83%)ቱ ተማሪዎች ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በዚህ ነጥብ ዙርያ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የማሳተፍ ብቃቱ ዝቅተኛ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡

በአጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የመማር/ማስተማር ሂደት የትምህርት ፕሮግራሙንና ተማሪውን የሚያገናኘው ሁነኛ ድልድይ የክፍል መምህሩ እንደሆነ ክለሳ ድረሳናትን በቃኘው በምዕራፍ ሁለት መጠቀሱ ይታወሳል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ተማሪዎች ከትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በመማር ካሳለፉት ሂደት በዚህ ነጥብ ዙርያ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማየት ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 7፡- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የክፍል መምህራንን ለማሳተፍ ያለውን ብቃት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጧቸው መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቅተኛ ነው | | በጣም ዝቅተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 1 | የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም በፅሞና እንድትከታተሉ በክፍል መምህራችሁ የሚደረግላችሁ እገዛ ምን ያህል ነው? | 36 | 15 | 41 | 17.08 | 58 | 24.17 | 71 | 29.58 | 34 | 14.17 |
| 10 | በሬዲዮ ፕሮግራም በተማራችኋቸው ይዘቶች ላይ መልመጃዎችን በግልም ሆነ በቡድን እንድትሰሩ በክፍል መምህራችሁ የሚደረግላችሁ እገዛ ምን ያህል ነው? | 14 | 5.83 | 23 | 9.58 | 55 | 22.92 | 72 | 30 | 76 | 31.67 |
| 16 | በሬዲዮው ፕሮግራም በተማራችኋቸው ይዘቶች ላይ መልመጃዎችን ስተሰሩ በክፍል መምህራችሁ የሚደረግላችሁ ክትትልና የሚሰጣችሁ እረማት ምን ያህል ነው? | 34 | 14.17 | 33 | 13.75 | 43 | 17.92 | 56 | 23.33 | 14 | 30.83 |
| 19 | ከትምህርት በሬዲዮ መምህር ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች የምትሰጡትን መልስ በመቀበልና እናንተም የምታቀርቧቸውን ጥያቄዎችና አስተየአየቶች በመቀበል የክፍል መምህራችሁ የሚያደርጉላችሁ እገዛ ምን ያህል ነው? | 49 | 20.42 | 36 | 15 | 59 | 24.58 | 59 | 24.58 | 37 | 15.42 |

የትምህርት በሬዲዮ በሚቀርብባቸው ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች የትምህርት ፕሮግራሙን በጥሞና እንዲከታተሉ በክፍል መምህራኑ የሚደረግላቸው እገዛ ከአማካይ በታች መሆኑን በሠንጠረዡ የሰፈረው ከተማሪዎቹ አመለካከት መለኪያ ጥያቄ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ 71(29.58%) እና 34(14.17) ያህሉ ተማሪዎች የመምህራኑ እገዛ በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ መሆኑን ሲያመለክቱ፥ 36(15%) እና 41(17.08) ያህል ተማሪዎች እገዛው በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ጠቅለል ባለ ሁኔታ 105(43.75) ተማሪዎች በዚህ ነጥብ ዙርያ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ሲሆን ፥ 77(32.08%) ተማሪዎች አወንታዊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ውጤት የመምህራኑ እገዛ መካከለኛ ነው ከሚሉት 58(24.17% ) ተማሪዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች ፕሮግራሙን እንዲከታተሉ የሚያደርጉላቸው እገዛ መሻሻል የሚገባው መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ተማሪዎች በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የተማሩትን ትምህርት በግልም ሆነ በቡድን እንዲሰሩ በክፍል መምህራኑ የሚደረግላቸው እገዛ ዘቅተኛ መሆኑን ከተማሪዎቹ የተገኘው መረጃ በጉልህ ያመለክታል። በዚህ ነጥብ ላይ የ 72(36%) እና የ76(31.67%) በድምሩ 148(61.67) ተማሪዎች አሉታዊ አመለካከት ከ 14(5.83%) እና ከ23(9.58%) በድምሩ ከ37(15.42%) ተማሪዎች አወንታዊ አመለካከት ጋር ሲነፃፀር በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የተማሩትን የትምህርት ይዘት በልምምድ እንዲያዳብሩት በክፍል መምህራኑ የሚደረግላቸው እገዛ በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ መሆኑንም በግልፅ ያመለክታል። የመምህራኑን እገዛ በአማካይ ደረጃ፥ የገለፁት 55(22.92) ተማሪዎችም አመለካከት የችግሩን መኖር የሚያመለክት ነው።

በዚህ አብይ ነጥብ ዙሪያ ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ከተለያየ አቅጣጫ ለማረጋገጥ ተማሪዎች መልመጃዎችን ሲሰሩ፥ በክፍል መምህራኑ የሚደረግላቸው ክትትልና የሚሰጣቸው እርማት፥ ከተማሪዎች የሚቀርቡ፥ ጥያቄዎችን፥ የሚሰጡ መልሶችንና የሚሰነዘሩ አስተያየቶችን በመቀበል በመምህራኑ የሚደረግላቸው እገዛ ምን እንደሚመስል በዚሁ ሠንጠረዥ 6 ውስጥ በተራ ቁጥር 16 እና 19 ላይ በቀረቡ ጥያቄዎች አማካይነት ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች በተራ ቁጥር 1 እና 10 ላይ በቀረቡ ጥያቄዎች አማካይነት የተገኙ መረጃዎችን የሚያጠናክሩ ሆነው ተገኝተዋል። ይህንንም ለእነዚህ ጥያቄዎች ለቀረቡላቸው አማራጭ መልሶች፥ መልስ የሰጡ ተማሪዎችን ብዛትና የመቶኛ ስሌቱን ውጤት በሠንጠረዡ ውስጥ በጥያቄ ተራ ቁጥር 16 ና 19 ትየዩ ይመልከቱ።

በክፍል ውስጥ በተደረጉ ምልከታዎች የተገኙና፥ በዚህ የጥናት ክፍል በሠንጠረዥ 5 በተራ ቁጥር 5 ላይ በቀረበው ጥያቄ አማካይነት የተገኙ መረጃዎችም ውጤትም ከዚህ በላይ ለማቅረብ ከተሞከሩት የመረጃዎች ውጤት ጋር ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ ጥናት ውስጥ በጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ስልትን በመጠቀም ለማወቅ የተሞከረው ሌላው ነጥብ ተማሪዎች ለዚህ የአማርኛ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ነው።

ሠንጠረዥ 8:- ተማሪዎች ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጡ መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቅተኛ ነው | | በጣም ዝቅተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 23 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ያለህ(ሽ) ፍላጎት ምን ያህል ነው? | 116 | 48.33 | 73 | 30.42 | 23 | 9.58 | 17 | 7.08 | 11 | 4.58 |

በጥናቱ ከተሸፈኑት 240 ተማሪዎች 116(48.33%) እና 73(30.42%) ተማሪዎች ለትምህርቱ በሬዲዮው ያላቸው ፍላጎት በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ወይም ጠቅለል ባለ መልኩ 189(78.75%) ያህሉ ተማሪዎች ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ላይ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው 17(7.08%) እና 11(4.58፤) በድምሩ 28(11.67፤) ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር ተማሪዎቹ ለትምህርት በሬዲዮው ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑ ጎልቶ ታይቷል፡፡ 23(9.58፤) ተማሪዎች ብቻ ለፕሮግራሙ ያላቸው ፍላጎት መካከለኛ መሆን ለፕሮግራሙ ፍላጎት ገለልተኛ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ውሱን መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደጠቆሙት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በአቀራረቡ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉበት ቢመለከትም ከላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ 7 መሠረት አብዛኛው ተማሪ ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የትምህርት ፕሮገራሙ በአቀራረቡ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉበት ጥናቱ እየጠቆመ፥ ተማሪው ለትምህርት በሬዲዮው ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ሆኖ መገኘቱ፥ የተሻለ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ማዘጋጀትና ማቅረብ ከተቻለ ተማሪው ከትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በተሻለ ሁኔታ መማር እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ለተማሪዎች በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት ተማሪዎች መደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርትና የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ያላቸው አመለካከት ለማወቅ ተሞክሮ ነበር፡፡

ሠንጠረዥ 9:- ተማሪዎች በመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርትና በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አቀራረብ በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቀተኛ ነው | | በጣም ዝቀተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 6 | በክፍል መምህራችሁ የተማራችሁትን ትምህርት በሬዲዮ ደግማችሁ የመማራችጠ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | 41 | 17.08 | 29 | 12.08 | 76 | 31.25 | 46 | 19.17 | 49 | 20.42 |
| 9 | በሬዲዮ የተማራችሁትን ትምህርት በክፍል መምህራችሁ ደግማችሁ የመማራችሁ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | 39 | 16.25 | 32 | 13.33 | 68 | 28.33 | 48 | 20 | 53 | 22.08 |

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከቀረቡ አምስት አማራጭ መልሶች አንፃራዊ በሆነ መልኩም ቢሆን ቁጥሩ በዛ ያለው ተማሪ መካከለኛ ወደሚለው አማራጭ አዘንብሎ ተገኝቷል፡፡ በተለይም በጥያቄ ተራ ቁጥር 6 ላይ በመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት የተማሩትን የትምህርት ይዘት በትምህርት በሬዲዮ ምን ያህል ደግመው እንደሚማሩ ለቀረበላቸው ጥያቄ 41(17.08፤) እና 29(12.08) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ወይም በድምሩ 70(29.17) ተማሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ደግመው እንደሚማሩ ሲያመለክቱ 46(19.17፤) እና 49(20.42፥) ያህሉ ተማሪዎች ደግመው የመማራቸው ሁኔታ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ወይም ጠቅለል ባለ መልኩ 95(39.58፤) ተማሪዎች ዝቅተኛ መሆኑን ነው የጠቆሙት፡፡ መካከለኛ ነው ያሉትም 76(31.25) ተማሪዎች ናቸው፡፡

በሬዲዮ የተማሩትን የትምህርት ይዘት በክፍል መምህራቸው ምን ያህል ደግመው እንደሚማሩ ለቀረበላቸ ጥያቄም 39(16.25፤) እና 32(13.33፤) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ ደግመው እንደሚማሩ ሲያመለክቱ፥ በአንፃሩ 48(20፤) እና 53(22.08) ያህሉ ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ በሆነ ሁኔታ ደግመው እንደሚማሩ አመልክተዋል፡፡ 68(28.33፤) ተማሪዎችም መካከለኛ በሆነ ሁኔታ ደግመው እንደሚማሩ አመልክተዋል፡፡

ከሁለቱም ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎችን በአስተማማኝ መረጃነት ለመቀበል የማያስችሉ ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም በክፍል

መምህራችሁ፥ ወይም መደበኛውን የክፍል ውስጥ ትምህርት በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ደግማችሁ የመማራችሁ ሁኔታ ምን ያህል ነው ተብለው ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች ልዩነት የተቀራረበ ነው፤ በሌላ በኩል የ7ኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ንድፍ በማየት፥ በተደረጉት የክፍል ውስጥ ምልከታዎችና ለመምህራኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ አማካይነት ከተገኙ መረጃዎች ለማወቅ እንደተሞከረው በትምህርት በሬዲዮው ክፍለ ጊዜ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ቀደም ብለው በመደበኛው የትምህርት ክፍለ ጊዜያት የቀረቡ (የሚቀርቡ) ሆነው ተገኝተዋል። በሌላም በኩል በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የቀረቡ(የሚቀርቡ) የትምህርት ይዘቶች በክፍል መምህራን ደግመው እንደማይቀርቡ ከእነዚህ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከዚህ አንፃር ይህን ነጥብ አስመልክቶ ለተማሪዎች ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ከፕሮግራሙ ንድፍ፥ ከትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ፥ ከክፍል ውስጥ ምልከታዎችና ከክፍል መምህራኑ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ጋር የማይጣጣሙ ሆነው ተገኝተዋል። በዚህ ጥናት አቅራቢ አስተያየት ለእነዚህ ልዩነቶች ምክንያት መስለው የሚታዩት ይህን ነጥብ በተመለከተ ለተማሪዎቹ የቀረቡት ጥያቄዎች በቅርብም ሆነ ራቅ ባሉ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችንና አቀራረባቸውን ሁኔታ ጊዜ ወስዶ ማሰብና ማስታወስን የሚጠይቁ መሆናቸውና ተማሪዎቹ መጠይቁን ሲሞሉ የነበራቸው ጊዜ፥ ትዕግስትና የትምህርት ደረጃ ውሱንነት ሊሆኑ ይችላሉ።

የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ መሆኑ ይታወሳል። በዚህ ጥናት ውስጥ በጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲያስገኙ ታስበው ነው። ለተማሪዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ ውስጥም እንዲሁ ተማሪዎች የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ተማሪዎች በዚህ አብይ የጥናቱ ጥያቄ ዙሪያ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስልም ከዚህ ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ ይመለከቷል።

ሠንጠረዥ 10:- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቅተኛ ነው | | በጣም ዝቅተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 7 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የሚቀርቡ ክፈለ ጊዜያት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ትምህርቱን በልምድም እንድታዳብረው (ሪው) በመርዳት የሚያደርጉልህ(ሽ) አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | 21 | 8.75 | 17 | 7.08 | 34 | 14.17 | 103 | 42.92 | 65 | 27.08 |
| 21 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለአማርኛ ቋንቋ ትመህርትህ(ሽ) የፈተና ውጤት መሻሻል የሚያደርግልህ(ሽ) አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | 68 | 28.33 | 56 | 23.33 | 48 | 20 | 35 | 14.58 | 33 | 13.75 |
| 22 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር የአማርኛ ቋንቋ ችሎታህን(ሽን) እንድታዳብር(ሪ) የሚያደርግልህ(ሽ) አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | 43 | 17.92 | 38 | 15.83 | 88 | 36.67 | 42 | 17.5 | 31 | 12.92 |
| 24 | መደበኛው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም እየታገዘ መሰጠቱ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | 34 | 14.17 | 51 | 21.25 | 83 | 34.58 | 56 | 23.33 | 16 | 6.67 |

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮው ክፍለ ጊዜያት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ትምህርቱን በልምምድ እንዲያዳብሩ የሚያደርጉላቸው አስተዋፅኦ ዝቅተኛ እንደሆነ ከተማሪዎቹ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። 103(42.92%) እና 65(27.08፣) ተማሪዎች አስተዋፅኦው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ወይም በድምሩ 168(70፣) ተማሪዎች በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የሚቀርቡ መልመጃዎች የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያደርግላቸው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል። በአንፃሩ 21(8.75፣) እና 17(7.08) ወይም በድምሩ 38(15.83፣) ተማሪዎች በዚህ ነጥብ ዙርያ የፕሮግራሙ አስተዋፅኦ በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ እንደሆነ ሲያመለክቱ 34(14.17፣) ተማሪዎችም አስተዋፅኦው መካከለኛ መሆኑን አመልክተዋል።

የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ተማሪዎች መልመጃዎችን በግልም ሆነ በቡድን እንዲሰሩ ለመርዳት ያለው አስተዋፅኦ በዝቅተኛ ከመሆኑ ጋር (ሠንጠረዥ 5፣ ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 5ን ይመለከታል) ይህ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥሩ መሻሻል ሊያበረክት በሚችለው

አስተዋፅኦ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ይጠቁማል፡፡

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር በተማሪዎች የፈተና ውጤት ላይ የሚኖረውን ተፅእኖ ለማወቅ በ21ኛው ተራ ቁጥር ላይ በቀረበው ጥያቄ አማካይነት የተገኘው መረጃም እንደሚያመለክተው፡- 68(28.33) እና 56(28.33፤) ተማሪዎች የትመህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለፈተና ውጤታቸው መሻሻል በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደረግላቸው ሲያመለክቱ፥ 35(14.58፤ ) እና 33(13.75፤) ተማሪዎች አስተዋፅኦው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ አስተዋፅኦው ከፍተኛ ነው ያሉት 124(51.17፤) ተማሪዎች አስተዋፅኦው ዝቅተኛ ነው ካሉት 68(28.33፤) ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር አስተዋፅኦው አወንታዊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ያም ሆኖ አስተዋፅኦው መካከለኛ ነው የሚሉት 40(20፤ ) ተማሪዎች አመለካከከት፥ በአስተዋፅኦው ላይ አሉታዊ አመለካከከት ካላቸው 68(28.33፤) ተማሪዎች ጋር ሲታይ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ላይ መሻሻል ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን የሚጠቁም ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ በማዳበር የሚኖረውን አስተዋፅኦ በተመለከተ ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በቀረበው ጥያቄ አማካይነት የተሰጡ መልሶች ለአወንታዊና ለአሉታዊ ምረጫዎች የተሰጡ መልሶች ተቀራራቢ ሆነው ሲገኙ፤ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የብዙ ተማሪዎች መልስ መካከለኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት 43(17.92) እና 38(15.83) ወይም በድምሩ 81(33.75፤) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ በማለት ፕሮግራሙ የቋንቋ ችሎታቸውን እንደሚያዳብርላቸው ሲያመለክቱ በሌላው አንፃር 42(17.50%) እና 31(12.92%) ተማሪዎች ፕሮግራሙ የቋንቋ ችሎታቸውን የሚያዳብርላቸው ዝቅተኛ ወይም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ መጠይቁን ከሞሉ 240 ተማሪዎች፥ የ81(33.75%) ተማሪዎች አመለካከት አወንታዊ፥ የ73(30.42%) አሉታዊ (ዝቅተኛ) እና የ88(36.67%) ተማሪዎች መካከለኛ ሆኖ መገኘት የትኛውንም መልስ በአስተማማኝ መረጃ ስጪነት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

ይህ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ላይ በተደረገው የይዘት ትንተና ከተገኘው መረጃ ጋር የተራራቀ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተደረገው የይዘት ትንተናም የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘቶች ተማሪው አበይት የቋንቋ ክሂሎችን እንዲያዳብር የሚረዱ ሳይሆኑ፥ በአመዛኙ ስለቋንቋው እንዲያውቅ የሚረዱ ሆነው ተገኝተዋል (የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ናሙና ይዘቶችን በአባሪ 6 ይመለከቷል)፡፡

መደበኛው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአጋዥ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም እየታገዘ መስጠቱ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት በሚችለው አስተዋፅኦ ላይ ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ለማወቅም ለቀረበው ጥያቄ የተሰጡ መልሶች ተቀራራቢ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በዚህም መሰረት 34(14.17) እና 51(21.25%) ተማሪዎች አስተዋፅኦው በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ነው ሲሉ፥ 56(23.33%) እና 16(6.67%) ተማሪዎች የፕሮግራሙ አስተዋፅኦ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል 83(34.58%) ተማሪዎች አስተዋፅኦው መካከለኛ እንደሆነ ያመለከቱ ናቸው፡፡ ይህ ውጤት ጠቅለል ባለ መልኩ በቅደም ተከተል ሲታይ፥ 85(35.42) ተማሪዎች የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለትምህርቱ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው ሲሉ፥ 83(34.58) ተማሪዎች መካከለኛ ነው፥ 72(30%) ዝቅተኛ ነው የሚል አመለካከት እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡

በዚህ መሰረት ለቀረቡት አማራጭ መልሶች የተሰጡት መልሶች ተቀራራቢነት ተማሪዎች በዚህ ክፍል ነጥብ ዙሪያ ያላቸው አመለካከት ይህን ይመስላል ብሎ ለመወሰን አላስቻለም፡፡ በተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች፥ ከመምህራኑ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅና በፕሮግራሙ ላይ በተደረገው የይዘት ትንተና የተገኙ መረጃዎች የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አሁን ባለበት ሁኔታ የትምህርቱን ጥራት ለማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ዝቅተኛ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ከተማሪዎቹ የተገኘው መረጃ ከሌሎቹ የመረጃ ምንጮች ከተገኙ መረጃዎች የተለየው በመጠይቁ መጨረሻ አካባቢ ጊዜ ወስደው በጥያቄው ይዘት ላይ ለማሰብ ትዕግስት ከማጣትና ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ካላቸው ፍላጎት የመነጨ ሊሆን ይቾላል የሚል የዚህ ጥናት አቅራቢ ግምት አለ፡፡

በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች የመረጃ ምንጭ እንዲሆኑ ለተፈለጉበት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ያላቸው ቅድመ እውቀት ማወቁ ከተማሪዎቹ የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ደረጃ ለመጠቀም ይቸላል ተብሎ በጥናቱ አቅራቢ ስለታመነበት ተማሪዎቹ ምን ያህል በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት ተገኝተው ፕሮግራሙን እንደሚከታተሉ ለማወቅ ተሞክሯል::

**ሠንጠረዥ 11፡- ተማሪዎች ምን ያህል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት ተገኝተው ፕሮግራሙን እንደሚከታተሉ ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጡ መልሶች መግለጫ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛአ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቅተኛ ነው | | በጣም ዝቅተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 20 | አንተ(አንቺ) በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፈለ ጊዜ ሁሉ ተገኝተህ(ሽ) ትምህርቱን የመከታተልህ/ሽ/ ሁኔታ ምን ያህል ነው | 134 | 55.83 | 61 | 25.41 | 37 | 15.42 | 6 | 2.50 | 2 | 0.83 |

በዚህ መረጃ መሰረት 195(81.25%) ተማሪዎች ፕሮግራሙን ክፍል ውስጥ ተገኝተው የመከታተላቸው ሁኔታ በጣም ከፍተኛ ወይም ከፍተኛ መሆኑ ሲመለከት፣ 37(15.42%) ተማሪዎች ደግሞ መካከለኛ በሆነ ሁኔታ እንደሚከታተሉ አመልክተዋል:: 6(2.50%) እና 2(0.83) ተማሪዎች ብቻ በሌላ በኩል ትምህርት በሬዲዮኑን የሚከታተሉት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ እንደሆነ አመልክተዋል:: ይህ መረጃም ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት ተማሪዎች ስለተጠየቁት ስለ 7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ልመዱ እንዳላቸው ሊጠቁም ይቸላል::

በመጠይቁ 18ኛ ጥያቄ ላይ "ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መማርያ የሚያገለግል ሬዲዮ በትምህርት በሬዲዮ ክፈለ ጊዜ ተማልቶ የመገኘቱ ሁኔታ ምን ያህል ነው?" ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ የአብዛኛው ተማሪ መልስ ከፍተኛ ነው የሚል ሆኖ ተገኝቷል:

በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች የመረጃ ምንጭ እንዲሆኑ ለተፈለጉበት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ያላቸው ቅድመ እውቀት ማወቁ ከተማሪዎቹ የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ደረጃ ለመጠቀም ይቾላል ተብሎ በጥናቱ አቅራቢ ስለታመነበት ተማሪዎቹ ምን ያህል በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት ተገኝተው ፕሮግራሙን እንደሚከታተሉ ለማወቅ ተሞክሯል::

ሠንጠረዥ 11:- ተማሪዎች ምን ያህል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት ተገኝተው ፕሮግራሙን እንደሚከታተሉ ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጡ መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛእ ነው | | መካከከለኛ ነው | | ዝቅተኛ ነው | | በጣም ዝቅተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 20 | አንተ(አንቺ) በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፊለ ጊዜ ሁሉ ተገኝተህ(ሽ) ትምህርቱን የመከታተልህ/ሽ/ ሁኔታ ምን ያህል ነው | 134 | 55.83 | 61 | 25.41 | 37 | 15.42 | 6 | 2.50 | 2 | 0.83 |

በዚህ መረጃ መሰረት 195(81.25፤) ተማሪዎች ፕሮግራሙን ክፍል ውስጥ ተገኝተው የመከታተላቸው ሁኔታ በጣም ከፍተኛ ወይም ከፍተኛ መሆኑ ሲመለከት፥ 37(15.42፤) ተማሪዎች ደግሞ መካከለኛ በሆነ ሁኔታ እንደሚከታተሉ አመልክተዋል:: 6(2.50፤) እና 2(0.83) ተማሪዎች ብቻ በሌላ በኩል ትምህርት በሬዲዮኑን የሚከታተሉት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ እንደሆነ አመልክተዋል:: ይህ መረጃም ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት ተማሪዎች ስለተጠየቁት ስለ 7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ልመዱ እንዳላቸው ሊጠቁም ይቾላል::

በመጠይቁ 18ኛ ጥያቄ ላይ "ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መማርያ የሚያገለግል ሬዲዮ በትምህርት በሬዲዮ ክፊለ ጊዜ ተማልቶ የመገኘቱ ሁኔታ ምን ያህል ነው?" ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ የአብዛኛው ተማሪ መልስ ከፍተኛ ነው የሚል ሆኖ ተገኝቷል:

ሠንጠረዥ 12:- የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦትን በተመለከተ ለተማሪዎች ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ ነው | | ከፍተኛ ነው | | መካከለኛ ነው | | ዝቀተኛ ነው | | በጣም ዝቀተኛ ነው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 18 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መማርያ የሚያገለግል ሬዲዮ በትምህርት በሬዲዮ ክፊለ ጊዜያት ተሟልቶ የመገኘቱ ሁኔታ ምን ያህል ነው | 102 | 42.50 | 73 | 30.42 | 47 | 19.58 | 13 | 5.42 | 5 | 2.08 |

ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ መሠረት 102(42.50) እና 73(30.42) ተማሪዎች የትምህርት መቀበያ ሬዲዮ ችግር አለመኖሩን ሲያመለክቱ የሬዲዮው አቅርቦት ዝቀተኛ ነው የሚሉት 13(5.42፤) እና 5(2.08) በድምሩ 18(7.50፤) ብቻ ሆነው ተገኝተዋል:: አቅርቦቱ መካከለኛ ነው ያሉትም 47(19.58) ተማሪዎች ናቸው:: ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው መምህራንም በተገኘው መረጃ መሰረት ከአንድ ትምህርት ቤት በቀር የሬዲዮ አቅርቦት ችግር አሳሳቢ እንዳልሆነ ነው የተጠቆመው:: ከዚህ አኳያ ከተማሪዎችም የተገኘው መረጃ ከመምህራኑ ከተገኘው መረጃ ጋር የተቀራረበ ሆኖ ተገኝቷል::

በመጠይቁ 3ኛ ክፍል "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለመደበኛው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊኖረው ስለሚችለው አስተዋፅኦ በአጭሩ ብትገልፅልኝ (ጪልኝ)?" በማለት ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን የሞሉት 181 ተማሪዎች አስተያየት ሳይሰጡ ቀርተዋል:: አስተያየታቸውን ለመስጠት የሞከሩትም 59 ተማሪዎች ከ2.1-2.24 ለቀረቡላቸው የምርጫ ጥያቄዎች ከሰጧቸው መልሶች ጋር ተመሳሳይ ሆነው ተገኝተዋል::

## 4.3. ለመምህራን ከቀረበ ቃለመጠይቅ የተገኙ መልሶች ትንተና

ለጥናቱ በተመረጡ ስድስት ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሙያ ስልጥነው 7ኛ ክፍል ቋንቋውን ለሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ ዘጠኝ ተመሳሳይ የሆኑ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል:: ከመምህራኑ የተገኙ መረጃዎችን በተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች፥ በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት ከተማሪዎች ከተገኙ መረጃዎችና በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ላይ በተደረገ የይዘት ትንተና ከተገኙ መረጃዎች ጋር ለማገናዘብ እንዲያመች፥ እያንዳንዱ መምህር ለቀረቡለት ጥያቄዎች ሰፋ ካለ ማብራሪያ ጋር የሰጣቸው መልሶች በጥናቱ መጨረሻ በአባሪ 5 ስር ቀርበዋል:

በዚህ የጥናቱ ክፍል ለማቅረብ የተሞከረው ለቃለ መጠይቁ መልስ ስለሰጡ መምህራን የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች የትምህር ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በሚሰጡት ትኩረት ሁኔታ ላይ መምህራን ያላቸው አስተያየት፥ ስለ7ክፍል የአማርኛ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጁ የመማርያ/ማስተመአሪያ መጽሀፍት ይዘት ጋር ስላላቸው ግንኙነት፥ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ብቃት፥ ስለመምህሩ መምሪያ አቅርቦትና ይዘት ሁኔታና በመጨረሻም የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋው ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥራት መጠበቅ/መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ በተመለከተ መምህራኑ ያላቸውን አስተያየት ነው።

የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የሚሰጡትን ትኩረት አስመልክቶ ለመምህራኑ ከቀረበው ቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት፡- የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለፕሮግራሙ የተሻለ ትኩረት እንደሚሰጡና ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ስኬታማነት የሚረዱ መሳሪያዎችን (ሬዲዮ፥ የቴፕ ክር፥ ሶኬት፥ የተመቻቹ የመማርያ ክፈሎች፥ ወንበርና ጠረጴዛ) አቅርቦትም ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል። በተለይ ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስኬታማነት የሚረዱ መሳሪያዎችን በተመለከተ ከመምህራኑ የተገኙ የመረጃዎችና በተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች ከተገኙ መረጃዎች ጋር ተቀራራቢ ሆነው ታይተዋል።

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጁት የመማርያና ማስተማርያ መፃህፍት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ አምስት መምህራን በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራምና በመማርያ/ማስተማሪያን መፃህፍቱ መካከል ግንኙነት አለ ሲሉ፥ ሁለት መምህራን ግን ግንኙነት እንደሌላቸውና ቢኖራቸውም በጣም ውሱን መሆኑን ገልፀዋል።

የትምህርት በሬዲዮውን ፕሮግራም አቀራረብ በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ መምህራኑ በሰጡት አስተያየት በአብዛኛው ተመሳሳይ፥ የአቀራረብ ስልትን(ውይይት) የሚጠቀም፥ ከተማሪው ደረጃ በታች ይዘትና አቀራረብ የሚታዩበት፥ ተማሪውን የማይስብ፥ የማያነጋግርና ተማሪው የተማረውን በልምምድ እንዲያዳብር የሚያግዙ መልመጃዎች ጉድለት የሚታይበት መሆኑን ገልፀዋል። ከእነዚህ ከትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ጉድለቶች የተነሳም በትምህርት

በሬዲዮው ክፍለ ጊዜያት የተማሪውና የክፍል መምህሩ ተሳትፎ ውሱን እንደሆነ መምህራኑ በተመሳሳይ ሁኔታ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ሌላው መምህራን አስተያየታቸውን በተመሳሳይ ሁኔታ የተጋሩበት ጉዳይ የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምርያ አቀራረብ ነው፡፡ በቀረበው ቃለመጠይቅ አስተያየታቸውን ከሰጡ መምህራን ውስጥ አንድም መምህር የትምህርት በሬዲዮኑን የመምህር መምሪያ በጉ ጎን የገለፀ የለም፡፡ መምህራኑ የመምህር መምርያውን አስመልክተው በሰጡት አስተያየት፡- የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ ግልፅነት የጎደለው፥ በሚቀርበው ፕሮግራም ውስጥ ላሉ ቃላትና ሀረጎች እንኳን ለመምህሩ የሚጠቁመው ፍንጭ የሌለው፥ በተማሪውም ሆነ በመምህሩ መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት በዝርዝር የማያመለክት፥ በየፕሮግራሙ ስለሚቀርቡ ዝርዝር ይዘቶች አስቀድሞ ሀሳብ ማስጨበጥ የማይችል ነው በማለት ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት ገልፀዋል፡፡ መምህራኑ በዚህ አመት የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የመምህሩ መምሪያ መድረስ በሚገባው ሰዓት ቀደም ብሎ ሲደርስ፥ ከዚያ ቀደም ግን ፕሮግራሙ መሰራጨት ከጀመረና ያለ መምሪያ ማስተማር ከጀመሩ፥ አልፎ አልፎም የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ካበቃ በኋላ እንደሚደርሳቸው ገልፀዋል፡፡

ከቅንጅት ጉድለት አብዛኛውን ጊዜ በትምህርት በሬዲዮ የሚቀርቡት የትምህርት ይዘቶች፥ ተማሪዎቹ ቀደም ብለው በመደበኛው ክፍለ ጊዜያት ከተማሩአቸው በኋላ ስለሚተላለፉና በይዘትና አቀራረባቸውም ቀላል ስለሆኑ፥ ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ ለፕሮግራሙ ያላቸውን ፍላጎት እንደሚቀንስባቸው አመልክተዋል፡፡

በመጨረሻም የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለቋንቋው ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ እንዲገልፁ ለቀረበላቸው ጥያቄ፡- ፕሮግራሙ ምንም አይነት አስተዋፅኦ እንደሌለውና ከነአካቴው ቢቀር የተሻለ እንደሚሆን አመልክተዋል፡፡ መምህራኑ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አሁን ባለበት ሁኔታ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ እንደሌለ አመልክተዋል፡፡

መምህራኑ ስለ 7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የሰጡት አስተያየት በአጭሩ ከዚህ በላይ ለማቅረብ የተሞከረውን ሲመስል፥ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው መምህራኑ የሰጡት ሰፋ ያለ ሀሳብ በጥናቱ መጨረሻ አባሪ 5 ስር ቀርቧል::

## 4.4. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ትንተና

የድርሳናትን ቅኝት ባካተተው በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ አጋዥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት በስራ ላይ ያለ መርሀ ትምህርት ይዘት የተወሰነ ክፍል መሆኑ ተጠቅሷል:: ከዚህ አኳያ በዚህ የጥናቱ ክፍል ውስጥ:- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ይዘት መርሀ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ ለክፍል ደረጃው ከቀረበው የመማርያ ማስተማሪያ መፃህፍት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማየት ይሞከራል:: የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ከመደበኛው መማርያ/ማስተማሪያ መጻህፍት ጋር ያለውን የይዘት ግንኙነት ለማወቅ በናሙናነት የተወሰዱት የክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት የተላለፉ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘቶች ናቸው::

ሠንጠረዥ 13:- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት መግለጫ

| የፕሮግራሙ ቁጥር | የትምህርቱ ርዕስ | የትምህርቱ ይዘት |
|---|---|---|
| 18 | ግጥም | - የግጥም ምንነት<br>- ቤት መምቻና ቤት መድፍያ ስንኝ<br>- ግጥም በጥቂት ፊደላት ሰፊ ሀሳብ/መልዕክት/ ማስተላለፍ የሚችል መሆኑ |
| 20 | የድርጊትን ቅደም ተከተል ማወቅ | - ድረሰት ቅደም ተከተል እንዳለው<br>- አንዱ ከሌላው ቀጥሎ እንደሚመጣ |
| 21 | የመንስኤና የውጤት ግንኙነት | - የመንስኤ ምንነት<br>- የውጤት ምንነት<br>- የመንስኤና የውጤት አንድነት<br>- ለውጤት የመንስኤ መኖር አስፈላጊነት |

ምንጭ:- ከሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ 2ኛ መንፈቀ አመት (1991) ከገፅ7-8ና ከገፅ 11-13

ሠንጠረዥ 14:- ከዚህ በላይ በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በመደበኛው የመምህሩ መምሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙበት ሁኔታ መግለጫ

| ርዕስ | የትምህርቱ ይዘት | ይዘቱ የቀረበበት ምንባብ | የሚገኝበት ገፅ |
|---|---|---|---|
| ግጥም | - ከምንባቡ ውስጥ ተገርደው የቀሩትን ስንኞች አሟልቶ መፃፍ<br>- ከምንባቡ የወጡ ስንኞች የሚያስተላልፉትን ሀሳብ በራስ አባባል መግለፅ<br>- ክፍት ቦታዎችን በልዩ ልዩ ስንኞች መሙላት | ትምህርቱ | 14 |
| | - የግጥም አነባበብ ግንዛቤና<br>- ግጥም ዜማዊ አነባበብ ያለው መሆኑ | ሰላም ይሰፈን | |
| ግጥም | - የግጥም አነባበብ ዜማ እንደየ ሀረጎችና ስንኞቹ ባህርያት የሚለያይ መሆኑ<br>- ግጥም የማንበብ ችሎታ<br>- ግጥም የመሰብሰብና የማንበብ ዝንባሌ ማግኘት<br>- የግጥም ስንኞች አይነትና ባህርያት<br>- አጫጭርና ረጃጅም ስንኞች<br>- ግጥምን ወደስድ ንባብ መለወጥ<br>- የግጥም ስንኞችን ቅደም ተከተል ማስያዝ | ነፃነት | 54 |
| | - ነገሮችን እያወዳደሩ አሳጥሮ ግጥሞችን መፃፍ | ንብና ትንኝ | 86 |
| የድርጊትን ቅደም ተከተል ማወቅ | - የድርጊቶችንና የጊዜን ቅደም ተከተል አገላለፅ በመጠቀም ሀረጎችን አረፍተ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ | ሰላም ይሰፈን | 38 |
| | - ተጠየቃዊ አስተሳሰቦችን በመጠቀም የአንድን ነገር አገልግሎት በቅደም ተከተል ማስቀመጥ | ወንዞች በሥራ ላይ ሲውሉ | 70 |
| የመንስኤና የውጤት ግንኙነት | - የቀረበላቸውን ሀረጎችና አረፍተ-ነገሮች በመንስኤና በውጤት ረድፍ ያስቀምጣሉ<br>- ከዚህ በላይ በመንስኤና በውጤት ያስቀመጧቸው አረፍተ ነገሮች በተገቢ አያያዦች እያገናኙ ረጃጅም አረፍተ ነገሮችን ይሰራሉ | የሰማይ አሞራ | 18 |
| | - የመንስኤና የውጤት ግንኙነትን ማስረዳት | አድማስ | 98 |

ምንጭ:- ከ7ኛ ክፍል አማርኛ ማስተማሪያ መጽሀፍ(የመምህሩ መምሪያ)

ግጥም በሰባተኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያም ሆነ ማስተማሪያ መፃህፍት ውስጥ በአ በየተለያዩ የምንባብ ርዕሶች ስር ቀርቧል፡፡ እነዚህን ምንባቦች ተከትለው በቀረቡ የተለያዩ መልመጃዎች ተማሪዎች ግጥምን እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል፡፡ በተለይም በመደበኛ የመምህሩ መምሪያ ላይ ነፃነት የተሰኘውን ምንባብ ተከትለው የቀረቡት የግጥም ይዘቶች፥ በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ቁጥር 18 ውስጥ ከቀረቡት የግጥም ይዘቶች በተሻለ ጥልቀትና ስፋት ቀርበው ታይተዋል፡፡ ከዚህም በላይ እነዚህ ግጥምን በተመለከተ የቀረቡ ይዘቶች ለተማሪው የቀረቡት በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት መሆኑ ከመደበኛው የመምህሩ መምሪያና ከመምህራኑ ጋር ከተደረገው ቃለመጠይቅ በተገኙ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ የእነዚህ ይዘቶች ከትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በተሻለ ስፋትና ጥልቀት ቀደም ብለው መቅረባቸው ሁለት ችግሮችን አስከትሎ ታይቷል፡፡ በመጀመሪያ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ግጥምን የተመለከቱ ይዘቶች በክፍል መምህሩ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር ተመሳሳይና እንዲያውም ከዚያ ባነሰ መልክ መቅረባቸው ከተማሪው ደረጃ በታች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ሁለተኛም ተማሪው ለትምህርት በሬዲዮው በተመደበው ክፍለ ጊዜ አዲስና የተለየ እውቀት ወይም ክሂል ስላላገኘበት የክፍለ ጊዜ ብክነትን አስከትሏል፡፡

በፕሮግራም 20 ስለ ድርጊት ቅደም ተከተል የቀረቡ ይዘቶችም እንዲሁ ተማሪዎቹ ቀደም ብለው በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት እንደተማሯቸው በክፍል ምልከታዎቹ ወቅት ከተማሪዎቹ የማስታወሻ ደብተር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ በፕሮግራም 20 ላይ የሚታዩ የይዘት ችግሮች/ድክመቶች በፕሮግራም 18 ላይ ከቀረቡት የግጥም ይዘቶች ብዙም የተለዩ ሆነው አልታዩም፡፡ በፕሮግራም 21 ስር የቀረበው የመንስኤና የውጤት ግንኙነት ይዘቶች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው በመማሪያና ማስተማሪያ መጽሃፍ ውስጥ "የሰማይ አሞራ" እና"አድማስ" በተሰኙ ምንባቦች ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ይህን ርዕስ አስመልክቶ በመደበኛው የመምህር መምሪያ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች፥ በትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከቀረቡ ይዘቶች ጋር ሲተያዩ ተመሳሳይ ግን የተሻለ ስፋትና ጥልቀት ኖሮአቸው ተገኝተዋል፡፡ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም 21 ቀደም ብለው ከቀረቡት ፕሮግራሞች(18 እና 20) ለየት የሚለው ይዘቱ በመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት ከቀረበበት ጊዜ ጋር በተቀራረበ ወቅት መቅረቡ ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታው በተደረገባቸው

ሁለት ትምህርት ቤቶች ከክፍል መምህራኑም ሆነ የተማሪዎችን የማስታወሻ ደብተር በማየት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ይህ የትምህርት ይዘት በመደበኛው የክፍል ውስጥ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከመቅረቡ ቀደብ ብሎ ቀርቧል።

የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ከመደበኛው የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሀፍት ጋር ያለውን ግንኙነት ከዚህ በላይ በቀረቡት ሶስቱ ፕሮግራሞች ናሙናነት ለማየት እንደተሞከረው፥ ይዘቶቹ ተመሳሳይ ሆነው ታይተዋል። ይሁን እንጂ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራሞች ይዘት በመደበኛው የማስተማሪያ/የመምህሩ መምሪያ መጽሀፍ ውስጥ እንደታየው ሰፋ ባለ ሁኔታ እንዳልቀረበ ማየት ተችሏል።

## 4.5. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ትንተና

በዚህ ክፍል የ7ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ስልት ምን እንደሚመስል ለማየት ይሞከራል። በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት በጠቅላላው ዘጠኝ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስለቶች (farmts) እንዳሉ የተለያዩ የክለሳ ድርሳናትን ዋቢ በማድረግ መጠቀሱ ይታወሳል። የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ የትኞቹን የአቀራረብ ስልቶች እንደሚጠቀም ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 15 የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ መግለጫ

| የፕሮግራም ቁጥር | የትምህርቱ ርዕስ | ትምህርቱ የቀረበበት ስልት |
|---|---|---|
| 1 | የምህፃረ ቃላት አመሰራረት | ቃለ ምልልስ |
| 2 | የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም | ገለፃ |
| 3 | " " " | ቃለ ምልልስ |
| 4 | የቃልንና የሀረግን ትርጉም ከአገባብ መለየት | ገለፃና ቃለምልልስ |
| 5 | ስለ ገላጮች | ገለፃ |
| 6 | የቃላት በመጥበቅና መላላት የትርጉም ለውጥ ማምጣት | ቃለ ምልልስ |
| 7 | የቃላት አመሰራረት | ቃለ ምልልስ |

| | | |
|---|---|---|
| 8 | ቅደመ ግንድ ቅጥያዎች | ገለፃ |
| 9 | ድህረ ግንድ ቅጥያዎች | ቃለ ምልልስ |
| 10 | ቃላትና ሀረጎች ያላቸውን ልዩነት ማሳየት | |
| 11 | ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት | ቃለ ምልልስ |
| 12 | ስለ ቃላት በአረፍተ ነገር ስጥ በስርዓት መደርደር | ገለፃ |
| 13 | መመርያን መከተል | ገለፃ |
| 14 | መጀመርያው ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ | ገለፃ |
| 15 | አንብቦ መረዳት | ገለፃ |
| 16 | አረፍተ ነገሮችን አገጣጥሞ አንቀፅ መፃፍ | ቃለ ምልልስ ገለፃ |
| 17 | ግጥም | ገለፃ |
| *18 | ግጥም | ገለፃ |
| 19 | ሥነ-ቃል | ቃለ-ምልልስ |
| *20 | የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተል | ቃለምልልስ |
| *21 | መንስኤና ውጤት | ገለፃ |
| 22 | ማስታወሻ መያዝ | ገለፃ |
| 23 | አንድን ሀሳብ በተለያዩ አባባሎች መግለፅ | ገለፃ |
| 24 | ጽሁፍን ማስፋፋት | ቃለ ምልልስ |
| 25 | አስተዋፅኦ መንደፍ | ገለፃ |
| 26 | የራስ የህይት ታሪክ አፃፃፍ | ገለፃ |
| 27 | ክርክር | ገለፃና ክርክር |
| 28 | የ2ኛ ሴሚስተር ማጠቃለያ | ገለፃ |

ምንጭ:- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ንድፍ (1991)

*የክፍል ውስጥ ምልከታ የተደረገባቸ ፕሮግራሞች

ተዘውትረው ይሰራባቸዋል ተብለው በክለሳ ድርሳናት(በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት) ከቀረቡት ዘጠኝ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶች ውስጥ ለ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች የተመረጡት የአቀራረብ ስልቶች ሶስት ብቻ መሆናቸውና አብዛኞቹ ፕሮግራሞች የቀረቡትም በተለመደው የክፍል ውስጥ የመማር/ማስተማር ሂደት ተዘውትሮ በሚሰራበት የገለፃ አቀራረብ ስልት መሆኑ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አቀራረብ ስልት ችግር እንዳለበት ያመለክታል፡፡

ለትምህርት በሬዲዮ የሚመረጡ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች ተስማሚ በሆኑ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶች ካልቀረቡ በተማሪው ዘንድ የሚኖራቸው ተቀባይነት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ የፕሮግራሙ አቀራረብ በተማሪ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ዝቅተኛ ከሆነም፥ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት በሚችለው አስተዋፅኦ ላይ አሉታዊ አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል፡፡

26ቱም የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች በንዑሳን የቋንቋ ክሂሎች የንድፍ ሀሳብ እውቀትና መመርያ ላይ ብቻ ከማተኮር አልፈው፥ ተማሪው በቋንቋው እንዲጠቀም ለማድረግ በሚረዱ፥ መልመጃዎች ወይም ክንውኖች /tasks/ አለመታገዛቸው በትምህርት በሬዲዮው አቀራረብ ላይ የታየ ሌላ ችግር ነው፡፡ ለዚህም አብነት ይሆኑ ዘንድ በአባሪ 6 ና 7 የቀረቡትን የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም 18፥ 20 ና 21 ንድፍና የመምህር መምሪያ ይመለከቷል፡፡ በትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምርያ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች መልመጃዎችና ለክፍል መምህሩ የቀረቡ የአሰራር መመርያዎች ውሱንነት፥ የክፍል መምህሩን ለፕሮግራሙ ለማዘጋጀት ያለው ብቃት ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ

### 5.1. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ ለመግለፅ እንደተሞከረው መደበኛ ትምህርት በሬዲዮ ከሚቀርብባቸው ዓላማዎች አንዱ፥ በሥራ ላይ ያለን መደበኛ ትምህርት ጥራት ለማሻሻል ነው። መደበኛ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የሚቀርብበት ዓላማ እንዲሁ የትምህርቱን ጥራት ለማሻሻል ነው። በዚህ ጥናት ለማቅ የተፈለገውም በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የትምህርቱን ጥራት ለማሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ለማወቅ እንደሆነ በጥናቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ተገልጿል።

የምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ መኖር አለመኖሩንም ለማወቅ የሚረዱ አራት የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች በጥቅም/ተግባር ላይ ውለዋል። የመረጃ አሰባሰብ ስለቶቹም የክፍል ውስጥ ምልከታ፥ ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ፥ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅና በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና ናቸው።

በተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች፡- በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት የተማሪዎችና የመምህራን ተሳትፎ፥ የመምህራኑ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አጠቃቀም፥ ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች (ሬዲዮ፥ ኤሌክትሪክ ወይም የባሪ ድነጋይ፤ ጥቁር ሰሌዳ የመማርያ ክፍሉ ሁኔታ ወዘተ) አቅርቦት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ተሞክሯል። ለተማሪዎች በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ አማካይነትም ከተለያየ አቅጣጫ ተማሪዎች ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ያላቸውን አመለካከት ለመገንዘብ ተሞክሯል።

ለ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም በቀረበው ቃለመጠይቅ አማካይነት፡- ትምህርት ቤቶች(ርዕሳነ መምህራን) ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ስለሚሰጡት ትኩረት፥ ለትምህር በሬዲዮው ፕሮግራም ስለሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች አቅርቦት፥ ስለ 7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምና መደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት አቀራረብ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምና መደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት አቀራረብ ቅንጅት፥ ስለ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምርያ (የክፍል መምህራንን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ስላለው) ብቃት፥ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ስላላቸው ፍላጎትና የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት ስለሚችለው አስተዋጽኦ ዙርያ መምህራኑ ያላቸውን አስተያየት ለማወቅ ነው።

በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ንድፍና የመምህሩ መምሪያ ላይ በተደረገ የይዘት ትንተናም፦ በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምና ለክፍል ደረጃው በዘጋጁት የመማርያ/ማስተማሪያ መጻህፍት መካከል ያለው የይዘት ግንኙነት ምን እንደሚመስል፥ በተግባር ላይ የዋሉት የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶች አይነትና የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የክፍል መምህሩን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ያለው ብቃት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ተሞክሯል።

ከዚህ አኳያ እነዚህን የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች በመጠቀም በተገኙ መረጃዎች መሠረት፦

1. ተማሪዎች ለትምህርት በሬዲዮ ፍላጎት እንዳላቸውና
2. የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘትም ለክፍሉ ደረጃ ከተዘጋጁት የመማርያ/ማስተማሪያ መጻህፍት ይዘት ጋር ተመሳሳይ እንደሆኑ ተመልክቷል።

በሌላ በኩል የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም፦

1. በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪዎችንና የክፍል መምህራንን የማሳተፍ ድክመት እንዳለበት
2. ከመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት ፕሮግራም ጋር የአቀርቦት ቅንጅት ችግር እንዳለበት፥
3. በአቀራረቡ ከተማሪው ደረጃ በታች እንደሆነ
4. የተወሰኑ የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ስልቶችን ብቻ የሚጠቀምና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የማዳበር ብቃት የሌለው እነደሆነ፥

5. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ የክፍል መምህሩን አስቀድሞ ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ያለው ብቃት ዝቅተኛ እንደሆነ፥

6. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ በተፈለገ ጊዜና መጠን ለመምህራን የማይዳረስበት ሁኔታ እንዳለ፥

7. በትምህርት በሬዲዮ የስርጭት ወቅት ለተማሪዎችና ለክፍል መምህራን ተሳትፎ የሚሰጠው የጊዜ ፋታ በቂ እንዳልሆነ፥

8. የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ተማሪው የተማራቸውን የትምህርት ይዘቶች በልምምድ እንዲያዳብራቸው የሚረዱት የመልመጃ ጥያቄዎች እጥረት እንደሚታዩበት፥

9. አብዛኞቹ መምህራን ስለ ትምህርት በሬዲዮ ዓላማና አጠቃቀም ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ እንደሆነ፥

10. አንዳንድ ትምህርት ቤቶች (ርዕሳነ-መምህራን) ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረትና የሚያደርጉት ክትትል ዝቅተኛ እንደሆነና በእነዚህ ከዚህ በላይ ከ1-10 በተዘረዘሩ ጉልህ ችግሮች የተነሳም የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክርት የሚችለው አስተዋፅኦ ዝቅተኛ እንደሆነ ከጥናቱ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ድክመቶችን አስወግዶ ወይም ቀንሶ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱት የመፍትሄ ሀሳቦች አወንታዊ አስተዋፅኦ ሊኖራቸው እንደሚችል የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል።

1. የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻህፍት አዘጋጆችና የትምህርት በሬዲዮ ንድፍ አዘጋጆች ተቀናጅተው በመስራት የትኞቹ የትምህርት ይዘቶች በክፍል መምህራን፥ መቅረብ እንዳለባቸውና የትኞቹ የትምህርት ይዘቶች በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቅረብ እንዳለባቸው ቀደም ብሎ ቢወስን ቅንጅታዊ የትምህርት አቅርቦቱን

የሰመረ ያደርገዋል፤ አስፈላጊ ያልሆኑ የትምህርት ይዘት ድግግሞሽን፥ የክፍለ ጊዜ ብክነትንና የመማር/ማስተማሩን ሂደት አሰልቺነት ሊቀንስው ይቻላል።

2. የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ በትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም እንዲቀርቡ የተወሰኑ ዝርዝር ይዘቶችን፥ በትምህርት በሬዲዮ ቅድመ ስርጭት፥ በስርጭት ጊዜና ከስርጭት በኋላ በተማሪዎችና በክፍል መምህራን መከናን የሚገባቸውን ተግባራት በግልፅና በዝርዝር የሚያመለክት፥ በትምህርት በሬዲዮው መምህር በተማሪዎችና በክፍል መምህራን መካከል ትምህርታዊ መስተጋብር እንዲኖር የሚረዳ፥ ለአዳዲስ ቃላት ሀረጎችና አባባሎች ፍችና ማብራሪያ ለመስጠት የሚሞክርና ተማሪው የተማራቸውን የቋንቋ ክሂሎች በልምምድ እንዲያዳብራቸው የሚረዱ በቂ መልመጃዎችን እንዲይዝ ተደርጎ ቢዘጋጅ ፕሮግራሙ የተማሪውን የመማር ፍላጎት የበለጠ ያዳብራል፤ የታሰበለትንም ውጤት እንዲያስገኝ ሊረዳ ይቻላል።

3. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ስርጭት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ለመምህራት እንዲዳረስ ቢደረግ የክፍል መምህሩን ስለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘትና አቀራረብ አስቀድሞ እንዲያውቅና እንዲዘጋጅ ሊረዳው ይቻላል።

4. አብዛኞቹ መምህራን ስለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዓላማና አጠቃቀም ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል። የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በክፍል መምህራት እየታገዘ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ተገቢውን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችል ዘንድ በሙያው ተሰማርተው የሚገኙ መምህራን በክረምት በሚዘጋጅ ኮርስ፥ በተዘማጅ ጥናታዊ ስብሰባዎችና የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞች፥ እጩ መምህራንም በስልጣናቸው ወቅት ስለትምህርት በሬዲዮ ዓላማና አጠቃቀም ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ትምህርት እንዲያገኙ ጥረት ቢደረግ የፕሮግራሙን ውጤት አዎንታዊ ሊያደርገው ይቻላል። የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራንም እንዲሁ ስለትምህርት በሬዲዮው ፕሮገራም ዓላማ ግንዛቤውን መጨበጥ የሚችሉበት መንገድ/ስልት ቢቀየስ ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም አጠቃቀም ምቹ ሁኔታዎችን ሊፈጥር ይቻላል።

5. የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም በሳምንት ለአንድ ቀን ብቻ መተላለፉ በተለያየ ምክንያት ወይም ችግር አንድ ቀን ፕሮግራሙን መጠቀም ያልቻሉ ትምህርት ቤቶች በሌላ ቀን ፕሮግራማቸውን አስተካክለው የመጠቀም እድላቸውን ይገታዋል:: ይህም ሁኔታ በሳምንቱም ሆነ በሰነ ትምህርቱ የትምህርት መርሀ ግብር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል እንደሚችል ይገመታል:: ስለዚህ አንድ የትምህርት ፕሮግራም በሳምንት የትምህርት ቀናት ውስጥ ከአንድ ቀን በላይ መተላለፍ የሚችልበት ሁኔታ ቢመቻች በተጠቀሱት አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ለሚችሉ ችህሮች መፍትሄ ሊሆን ይቸላል::

## ዋቢ ምንጮች (Bibliography)


አዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ:: (1991):: አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ሰባተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት::

________:: (1990):: አማርኛ ማስተማሪያ መጽሀፍ ሰባተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

________:: (1991):: "ሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ንድፍ::" አዲስ አበባ፤ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ቡድን የተዘጋጀ:: (ያልታተመ)

________:: (1991) "ሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ፤ አንደኛ መንፈቀ አመት::" አዲስ አበባ፤ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ቡድን የተዘጋጀ:: /ያልታተመ/

________:: (1991):: "ሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ÷ ሁለተኛ መንፈቀ አመት::" አዲስ አበባ፤ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ቡድን የተዘጋጀ:: /ያልታተመ/

ትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት::/1991):: "በትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ቅንጅታዊ አጠቃቀምና የወደፊት አቅጣጫ አውደ ጥናት ለውይይት የቀረቡ ጽሁፎች::" አዲስ አበባ፤ ከህዳር 1-3 /1991:: /ያልታተመ/

Asres Kebede. (1988). Radio for Education and Development: A Case Study of Ethiopia. Manchester: Manchester University.

Almaze Bein. (1989). "Application and Effectiveness of the Methodology of English by Radio Programm for the Elementary Schools in Ethiopia." Thesis presented to the School of Graduate Studies. AAU, Addis Ababa.

Awol Endris. (1987). "Content and Effectiveness of Instructional Radio Programes for the Teaching of English in Ethiopian Elementary Schools: A Descriptive and Expermental Case Study." Addis Ababa. Thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa.

Bates, A. (1984). Broadcasting in Education: An Evaluation. London: Constable and Company.

____________. (1980). "Towards a Better Theoretical Framwork for Studying Learning Frome Educational Television." Instructional Science, Vol.9(3) pp. 393-415.

____________. (1995). Techonology, Open Learning and Distance Education. London: Routhledge.

Best, J.w., and James, V.K. (1993). Research in Education. (7th.ed.) NewDelhi: Prentic Hall.

Borg, ., and Gall, M. (1983). Educational Research: An Introduction. New York: Longman.

Breer, J., and Hunter, A. (1989). Multimethod Research: A Synthesis of Styles. London: Sage Publishers.

Brown, J. (1988). Understanding Research in Second Language Learning : A Teachers Guide to Statistics and Research Design. Cambridge: Cambridge University Press.

____________. et.al. (1977) (5th. ed.). An Instructional Technology: Media and Methods. New York: McGraw Hill Book Company.

(EDO. (1972) Development of Educational Mass Media in Ethiopia: A Report of the CEDO Survey Team. London: eihall.

Chancock, A. (1977). Planning for Educational Mass Media. London: Longman.

Clark, R. (1985). "Reconsider dering Research on Learning from Media and Technology." Review of Educational Research, 53(4), pp. 445-461.

Edgerton, D., and Sedlak, P. (1990). "The Second Language Factor in Interactive Radio: Report of the Radio Learning." Radio Learning, Vol. 7 (3), pp. 178-189.

Educational Massmedia Agency. (1995). Schools Radio Programs Utilization: An Evaluation Report. Addis Ababa: EMPDA.

_____________.(1991). "Schools Radio Programms Utilization Evaluation Report." (Unpublished).

Endale Kebede.(1986). "History of Educational Radio Programme in Ethiopia" Addis Ababa University in Parcial Fulfilment of the Requirments for the Degree of Bachlore of Arts in History. A.A.

Fekadu Mergia.(1989). "The Role of Educational Massmedia in Ethiopia." Addis Ababa: Yekatit 66 Institute of Poletical Education To the Department of Phylosophy (Unpublished).

Frankel, J., and Wallen N.E. (1990). How to Design and Evaluate Research in Education. New York: McGraw Hill Inc.

Fuller, N. (1965). Educational Television. New York: The Center for Applied Research in Education.

Hawkridg, D., and Robinson, J. (1982). Organizing Educational Broadcasting. Paris: UNESCO Press.

Head, S., (1994). Broadcasting in Africa: A Continental Survey of Radio and Television. Philadelphia: Temple University Press.

Jamisson, D.T., and McAnany, E.G. (1978). Radio for Education and Development. London: Sage Publishers.

Keith, R., and Peter, R. (1993). "Distance Learning in ELT." Review of English Language Teaching. Vol. 3(2), 79-86.

Keith, R., and Peter, R. (1993). "Distance Learning in ELT." Review of English Language Teaching. Vol. 3(2), 79-86.

Laflin, M. (1994). "Writing for Interactive Radio Instruction." Learning Technology. Washington D.C.: Educational Development Centntre.

Lindlof, T.R. (1995) Qualitative Communication Research Methods. London: Sage. Publihsers.

Moykur, P., and Morehouse, R. (1994). Beginning Qualitative Research: A Philosophic and Practical Guide. London: The Falmen Press.

Ministery of Education. (1987). "Evaluation of Primary School Radio Programs." Addis Ababa: (unpublished).

___________. (1973). Educational Media Organization and Operation. Addis Ababa: (unpublished).

___________.(1973). "A Plan of Operation for CEDO Report Recomendation: Educational Mass Medea Centre. Addis Ababa (unpublished).

Mohanty, J. (1994). Educational Broadcasting: Radio and Television in Education. (Revised ed.) New Delhi: Sterling Publishers Private Limited.

__________.(1984). Educational Broadcasting: Radio and Television in Education. New Delhi: Sterling Publihsers Private Limited.

Priest, S.H. (1966). Doing Media Research: An Introducltion. London. Sage Publishers.

Romiszoski, A.J. (1977) The Selection and Use of Instructional Meida. London: Kogan Page Limited.

Scramm, W. (1977). Big Media, Little Media: Tools and Technologies for Instruction. London: Sage Publishers.

Solomon, G., and Clark, R. (1977). "Reexamining The Methodology of Research On Media and Technology in Education." Review of Educational Research, 47(1), 99-120.

Solomon Melesse. (1999). "The Integration of Educational Media in the Current Ethiopian Educational System." Addis Ababa University. School of Graduatee Studies. In Parcial Fulfilment of the Requirment for the Degree of Masters of Arts in Curriculum and Instruction. Addis Ababa.

Tesfaye Simerta. (1990). "Methods of Teaching Formal Education Radio and Television Programs." (A Content Analysis) A Dessertation Submited in Parcial Fulfilment of the Requirments for the M.A. in Mass Communication. Leicester: University of Leicester.

Teshome Nekatibeb. (1998). Media Utilization and School Improvement: A Case Study of Primary Education Radio Support Programms in Ethiopia. Stockholm: Stockholm University Press.

Tilson, T.D. (1994). "Instructional Radio" Interactive Radio Instruction. Washington, D.C. published in the International Encyclopedia of Education Program Press.

Tomalin, B. (1991). Vidio, TV, and Radio in the English Class: An Introductory Guide. London: Macmillan Publishers.

Tuckman, B. (1985). Evaluating Instructional Programs. Boston: Allyn and Bacon Inc.

UNESCO. (1984). Media Education. Printed in France.

Ur, P. (1993). Teaching Listening Comprehension. Cambridge: Cambridge University Press.

_________. (1996). A Course in Language Teaching. Cambridge: Cambrdige University Press.

Wedell, G. (ed.). (1986). Making Broadcasting Usefull: The African Experience. Manchester: Manchester University Press.

Zirker, J.M. (1990) Interactive Radio Instruction: Confronting Crises in Basic Education. New ton: Massachustts.

# አባሪ 1

## በአዲስ አበባ መስተዳድር የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም÷ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ረገድ ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ

የክፍል ውስጥ ምልከታና ግምገማ መመሪያ ቅፅ

የትምህርት ቤቱ ስም________________

ክፍል____________ ሴክሽን________

ፈረቃ____________ ክፍለ ጊዜ________

የፕሮግራሙ ቁጥር______________

የትምህርቱ ርዕስ_____________

ቀን_____________

| ሀ | የመምህሩ ተግባር | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 1 | ቅደመ ትምህርት በሬዲዮ | | |
| 1.1. | ያለፈውን ትምህርት ይዘት ከልሷል (ሳለች) | | |
| 1.2. | የሚቀጥለውን ትምህርት ዓላማ ይዘት በአጭሩ ጠቁሟል(ለች) | | |
| 1.3. | አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችንና ቃላትን አስቀድሞ በሰሌዳ ላይ ጽፏል (ፋለች) | | |
| 1.4. | ትምህርቱን ለማዳመጥ እክል የሚፈጥሩ ነገሮችን አስቀድሞ ለማስወገድ ሞክሯል(ለች) | | |
| 1.5. | ሬዲዮኑን አስቀድሞ በማስተካከል ለተማሪዎች በሚሰማ ስፍራ አስቀምጧል(ለች) | | |
| 1.6. | ሬዲዮኑን በሰዓቱ ከፍቷል(ታለች) | | |
| 1.7 | ተማሪዎች ትምህርቱን በጥሞና እንዲከታተሉ አበረታቷል(ታለች) | | |
| 1.8 | ተማሪዎች ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ እንዲይዙ አበረታቷል(ታለች) | | |

| 2 | ትምህርቱ በሚተላለፍበት ጊዜ | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 2.1 | ክፍሉን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራል(ትቆጣጠራለች) | | |
| 2.2. | ከሬዲዮ መምህሩ የሚጠቀሙ ተግባራትን ተከታትሎ(ላ) ይፈጽማል(ትፈጽማለች) | | |

| 3 | ከትምህርት በሬዲዮ ሥርጭት በኋላ | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 3.1. | ዋና ዋና ነጥቦችን ከልሷል(ሳለች) | | |
| 3.2. | ተማሪዎ ትምህርቱን መከታተላቸውን ለማረጋገጥ ዋና ዋና ነጥቦችን በጥያቄ መልክ አቅርቧል(ባለች) | | |
| 3.3. | በትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተጠቀሱ ተግባራትን አከናውኗል(ናለች) | | |
| 3.4. | ትምህርቱን አጠቃሏል(ላለች) | | |
| 3.5. | የመልመጃ ጥያቄዎችን ሰጥቷል(ታለች) | | |

| ለ | የተማሪዎች ተግባር | ከፍተኛ ነው | ዝቅተኛ ነው |
|---|---|---|---|
| 1 | ለትምህርቱ የሚታይባቸው ፍላጎት | | |
| 2 | የክፍሉ ፀጥታ ለትምህርት በሬዲዮ የነበረው ምቹነት | | |
| 3 | የትምህርት በሬዲዮኑንም ሆነ የክፍል መምህሩን ገለጻና መመሪያ በማስታወሻ የመያዛቸው ሁኔታ | | |
| 4 | ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ያልገባቸውን በመጠየቅና የሚሰጣቸን ተግባር በማከናወን ይሳተፋሉ? | | |

| ጠ | የትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ | ከፍተኛ ነው | ዝቅተኛ ነው |
|---|---|---|---|
| 1 | አዝናኝ ሁኔታዎችን (ቀልዶችን) በየጣልቃው የመጠቀሙ ሁኔታ | | |
| 2 | ሬዲዮ መምህሩ የድምጽ ፍጠነት ተስማሚነት ደረጃ | | |
| 3 | የሬዲዮ መምህሩ(ሯ) ለተማሪዎች ተሳትፎ የሚሰጠው (የምትሰጠው) የጊዜ ፋታ ተስማሚነት ደረጃ | | |

| መ | የትምህርት ቤቱ ሁኔታ | ከፍተኛ ነው | ዝቅተኛ ነው |
|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፈሉ ለትምህርት በሬዲዮ ያለው ምቹነት | | |
| 2 | የትምህርቱ መቀበያ ሬዲዮ ጥራት | | |

# አባሪ 2

## በአዲስ አበባ መስተዳድር የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መደበኛውን የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት ለማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ

## በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዓላማ ለአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል በሬዲዮ የሚተላለፈው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መደበኛውን የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት በማሻሻል ረገድ ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ ደረጃ ለማወቅ ነው፡፡ በመሆኑም አንተም/ቺም/ በዚህ መጠይቅ ውስጥ ለቀረቡ ጥያቄዎች የምትሰጣቸው/ጪያቸው/ መልሶች ለጥናቱ ውጤት ትክክለኛነት የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

ስለሆነም እባክህን/ሽን/ ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በጥንቃቄና በእርጋታ መልስህን/ሽን/ በመስጠት እንድትባበረን/ሪን/ በትህትና እንጠይቃለን፡፡

ስለምታደርግልን/ጊልን/ ትብብርም በቅድሚ እናመሰግናለን፡፡

ማሳሰቢያ፡-

1. ለጠናቱ ውጤታማነት ብቻ ሲባል መጠይቁን ከጓደኛ ጋር እየተወያዩ መሙላት ክልክል ነው፥
2. በመጠይቁ ላይ ስምን መፃፍ አያስፈልግም
3. በዚህ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች ሁሉ የ7ኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ብቻ የሚመለከቱ ናቸው፡፡

1. ከዚህ ቀጥሎ ትምህርት ቤትህን/ሽን/ እና እራስህን/ሽን/ በተመለከተ ከ 1-5 ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጠባቸው/ጪባቸው/

1.1. የትምህርት ቤትህ/ሽ/ ስም ____________________

የትምህርት ቤትህ/ሽ/ አይነት ከምርጫህ/ሽ/ ቀጥሎ ባለው ሳጥን ውስጥ የ/ / ምልክት በማድረግ መልስህን/ሽን/ አመልክት/ቺ/፡፡

ሀ. የመንግስት /   /     ለ. ይህዝብ /   /

1.2. ትምህርት ቤትህ/ሽ/ የሚገኝበት፥

ዞን ______

ወረዳ ______

ቀበሌ ______

1.3. የምትማርበት/ሪበት/ ሴክሺን ____________________

1.4. ፆታህ/ሽ/   ሀ. ወንድ /   /     ጥ. ሴት /   /

/በሳጥን ውስጥ የ /   / ምልክት በማድረግ አመልክት/ቺ/

2. ከዚህ ቀጥሎ ከ 2.1-2.24 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከቀረቡት አምስት አማራጭ መልሶች ውስጥ ይበልጥ ትክክል ነው ብለህ/ሽ/ በምታምንበት/ኚበት/ አማራጭ መልስ ስር የ / / ምልክት በማድረግ ምርጫህን /ሽን/ አመልክት /ቺ/

| | | ሀ. በጣም ከፍተኛ ነው | ለ. ከፍተኛ ነው | ሐ. መካከለኛ ነው | መ. ዝቅተኛ ነው | ሠ. በጣም ከፍተኛ ነው |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1. | የትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም ስርጭትን በዕሞና እንድትከታተሉ በክፍል መምህራችሁ የሚደረግላችሁ ቅደመ ዝግጅት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.2. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ደረጃህን/ሽን/ የመመጠኑ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.3. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ከፍላጎትህ/ሽ/ ጋር የመጣጣሙ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.4. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ማራኪነት ደረጃ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.5. | በትምህርት በሬዲዮ ስርጭት ጊዜ የተማራችሁትን ትምህርት ስርጭት በኋላ በግልም ሆነ በቡድን መልመጃን በመስራት የመለማመዳችሁ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.6. | በክፍል መምህራችሁ የተማራችሁትን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ደግማችሁ የመማራችሁ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.7 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ክፍለ ጊዜያት ማብቂያ ላይ የሚቀርቡ የመልመጃ ጥያቀዎች ትምህርቱን በልምምድ እንድታዳብረው/ሪው/ በመርዳት የሚያደርጉልህ/ሽ/ አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.8 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ የማዳመጥ ትኩረትህን/ሽን/ የመሳብ/የመመሰጥ/ ደረጃው ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.9 | በሬዲዮ የተማራችሁትን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክፍል መምህራችሁ ደግማችሁ የመማራችሁ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.10 | በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም በተማራችኋቸው ይዘቶች ላይ መልመጃዎችን በግልም ሆነ በቡድን እንድትሰሩ በክፍል መምህራችሁ የሚደረግላችሁ እገዛ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.11 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ግልጽነት ደረጃ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.12 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መምህር/ራን/ ድምጽ አማካይ ፍጥነት ተስማሚነት ደረጃ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.13 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ስርጭት ወቅት ለተሳትፎ/መልስ ለመመለስ÷ ጥያቄ ለመጠየቅ÷ አስተያየት ለመስጠት የሚሰጣችሁ የጊዜ ሩታ ተስማሚነት ደረጃ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.14 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ተማሪዎችን የማሳተፍ ደረጃው ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.15 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ተማሪዎችን እያዝናና የማስተማር ብቃቱ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.16 | በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜያት በተማራችኋቸው ይዘቶች ላይ መልመጃዎችን ስተሰሩ በክፍል መምህራችሁ የሚደረግላችሁ ክትትልና የሚሰጣችሁ እርማት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.17 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ በውይይት ሲቀርብ የአንደኛው ተወያይ ድምፅ ከሌላኛው ተወያይ ድምፅ ተለይቶ የመታወቁ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.18 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መማሪያ የሚያገለግል ሬዲዮ በትምህርት ሬዲዮ ክፍለ ጊዜ ተሟልቶ የመገኘቱ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.19 | ከትምህርት በሬዲዮ መምህር ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች የምትሰጡትን መልስ በመቀበልና እናንተም የምታቀርቧቸውን ጥያቄዎችና አስተያየቶች በመቀበል የክፍል መምህራችሁ የሚያደርጉላችሁ እገዛ ምን ያህል ነ? | | | | | |
| 2.20 | አንተ/ቺ/ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ ሁሉ ተገኝተህ/ሽ/ ትምህርቱን የመከታተልህ/ሽ/ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.21 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መኖር ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርትህ/ሽ/ የፈተና ወጤት መሻሻል የሚያደርግልህ /ሽ/ አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.22 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መኖር የቋንቋ ችሎታህን/ሽን/ እንድታዳብር/ሪ/ እያደረገልህ/ሽ/ ያለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.23. | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ያለህ/ሽ/ ፍላጎት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2.24. | መደበኛው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፥ በትምህርት በሬዲዮ እየታገዘ መሰጠቱ፥ ለትምህርቱ ጥራት መሻሻል ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው? | | | | | |

3. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ለመደበኛው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊኖረ ስለሚችለው አስተዋጽኦ ያለህን(ሽን) አስተያየት በአጭሩ ብትገልጽልን/ጪልን/

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ስለትብብርህ/ሽ/ በድጋሚ እናመሰግናለን።

# አባሪ 3

## ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ከቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | ሀ | | ለ | | ጠ | | መ | | ሠ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የድግግሞሽ ብዛት | በመቶኛ | የድግግሞሽ ብዛት | በመቶኛ | የድግግሞሽ ብዛት | በመቶኛ | የድግግሞሽ ብዛት | በመቶኛ | የድግግሞሽ ብዛት | በመቶኛ | ጠቅላላ ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | 36 | 15.00 | 41 | 17.08 | 58 | 24.17 | 71 | 29.58 | 34 | 14.17 | 240 | 100 |
| 2 | 23 | 24.58 | 29 | 12.08 | 96 | 40.00 | 48 | 20.00 | 44 | 18.33 | 240 | 100 |
| 3 | 29 | 12.08 | 35 | 14.58 | 75 | 31.25 | 61 | 25.42 | 40 | 16.67 | 240 | 100 |
| 4 | 38 | 15.83 | 30 | 12.50 | 62 | 25.83 | 76 | 31.67 | 34 | 14.17 | 240 | 100 |
| 5 | 18 | 7.50 | 27 | 11.25 | 31 | 12.92 | 47 | 19.58 | 117 | 48.75 | 240 | 100 |
| 6 | 41 | 17.08 | 29 | 12.08 | 36 | 15.00 | 46 | 19.17 | 49 | 20.42 | 240 | 100 |
| 7 | 21 | 8.75 | 17 | 7.08 | 34 | 14.17 | 103 | 42.92 | 65 | 27.08 | 240 | 100 |
| 8 | 36 | 15.00 | 32 | 13.33 | 57 | 23.75 | 75 | 31.25 | 40 | 16.67 | 240 | 100 |
| 9 | 39 | 16.25 | 32 | 13.33 | 68 | 28.33 | 48 | 20 | 53 | 22.08 | 240 | 100 |
| 10 | 14 | 5.83 | 23 | 9.58 | 55 | 22.92 | 72 | 30 | 76 | 31.67 | 240 | 100 |
| 11 | 74 | 30.83 | 54 | 22.50 | 76 | 31.67 | 25 | 10.42 | 11 | 4.58 | 240 | 100 |
| 12 | 73 | 30.42 | 68 | 28.33 | 37 | 15.42 | 49 | 20.42 | 13 | 5.17 | 240 | 100 |
| 13 | 13 | 5.42 | 21 | 8.75 | 56 | 23.33 | 62 | 25.83 | 88 | 36.67 | 240 | 100 |
| 14 | 21 | 8.75 | 14 | 5.83 | 71 | 29.58 | 86 | 35.83 | 48 | 20 | 240 | 100 |
| 15 | 27 | 11.25 | 24 | 10 | 58 | 24.17 | 67 | 27.92 | 64 | 26.67 | 240 | 100 |
| 16 | 34 | 14.17 | 33 | 13.75 | 43 | 17.92 | 56 | 23.33 | 74 | 30.83 | 240 | 100 |
| 17 | 76 | 31.67 | 76 | 31.67 | 69 | 28.75 | 13 | 5.42 | 6 | 2.50 | 240 | 100 |
| 18 | 102 | 42.50 | 73 | 30.42 | 47 | 19.58 | 13 | 5.42 | 5 | 2.08 | 240 | 100 |
| 19 | 49 | 20.42 | 36 | 15 | 59 | 24.58 | 59 | 24.58 | 37 | 15.42 | 240 | 100 |
| 20 | 134 | 55.83 | 61 | 25.42 | 37 | 15.42 | 6 | 2.50 | 2 | 0.83 | 240 | 100 |
| 21 | 68 | 28.33 | 56 | 23.33 | 48 | 20 | 35 | 14.58 | 33 | 13.75 | 240 | 100 |
| 22 | 43 | 17.92 | 38 | 15.83 | 88 | 36.67 | 42 | 17.50 | 31 | 12.92 | 240 | 100 |
| 23 | 116 | 48.33 | 73 | 30.42 | 23 | 9.58 | 17 | 7.08 | 11 | 4.58 | 240 | 100 |
| 24 | 34 | 14.17 | 51 | 21.25 | 83 | 34.58 | 56 | 23.33 | 16 | 6.67 | 240 | 100 |

ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ. ከፍተኛ ጠ. መካከለኛ መ. ዝቅተኛ ሠ. በጣም ዝቅተኛ

# አባሪ 4

## ለ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ

1. የትምህርት ቤታችሁ ርዕሰ መምህር/ራን/ ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው?
2. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?
3. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለዚህ የክፍል ደረጃ ከተዘጋጁት የመማርያና የማስተማርያ መጽሀፍት ጋር ያለው የይዘት ግንኙነት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?
4. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎችም ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ሊገልፁልኝ ይችላሉ?
5. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ተማሪዎችንና የክፍል መምህሩን ለማሳተፍ ያለው ብቃት ምን ያህል ነው?
6. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርት ፕሮገራሙ ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ነው ቀድሞ የሚደርስው?
7. የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ እርስዎ ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም ቀደም ብለው እንዲዘጋጁ በመርዳት የሚያደርግልዎት አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው?
8. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ተሳትፈው ወይም እንዲሳተፉ ተጠይቀው ያውቃሉ?
9. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለቋንቋው ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው ይላሉ?

## አባሪ 5

### መምህራን ለቀረበላቸ ቃለ መጠይቅ የሰጡት መልስ

መጠይቅ 1

መምህር ጌትነት ስንሻው

ቀን 26/7/1992

ሰዓት ከ7:00 - 8:00

መምህር ጌትነት ስነሻው የዳግማዊ ብረሃን የመጀመሪያ ደረጃ የህዝብ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር ናቸው። ከመምህር ጌትነት ጋር ቃለመጠይቁን ያካሄድነው በትምህርት ቤቱ የመምህራን ማረፊያ ክፍል ውስጥ ነው። ከአቶ ጌትነት ጋር የተዋወቅነው በዚያኑ እለት ከሰዓት በፊት በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በአቶ አብዲሳ ጫላ አማካይነት ነበር። ለአቶ ጌትነት የመጣሁበትን ዓላማ ነግሬያቸው ለቃለ መጠይቁ መቼ እነደሚተባበሩኝ ስጠይቃቸው በዚያኑ እለት ከሰዓት በኋላ እንደሚመቻቸው ነግረውኝ ተለያየን። በተጠቀሰው ሰዓትና ቦታ ተገናኝተን ቃለመጠይቁን ቀጠልን፦

ጥ. የትምህርት ቤታችሁ ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው?

መ. ያሉት አንድ ርዕሰ መምህር ብቻ ናቸው እሳቸውም በቂ ትኩረት በመስጠት የትምህርት በሬዲዮውን ፕሮግራም እንድንጠቀም መምህራኑንም ተማሪዎችንም ያበረታታሉ።

ጥ. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. በሬዲዮ በኩል ምንም ችግር የለብንም። ያሉት ሬዲዮ ቴፖችም ጥራታቸው የተጠበቀ ነው።

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለዚህ ክፍል ደረጃ ከተዘጋጁት መርሃ ትምህርት፥ የመማርያ መጽሀፍና ማስተማሪያ መጽሀፍ፥ ጋር ያለው የይዘት ግነኙነት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. እኔ የተለያዩ የክፍል ደረጃዎች አስተምራለሁ፤ የሚተላለፈ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም ከእነዚህ መጽሀፍት ጋር በይዘት ይመሳሰላል። ሆኖም ግን በአቀራረቡ አብሮ አይሄድም መደጋገሙ ብዙ ክፋት ባይኖረውም እኔ በማስተማርያ መጽሀፉ እየተመራሁ አስተምሬ ካለፍኩ በኋላ ያው ርዕስ ዘግይቶ በሬዲዮ ደግሞ ይቀርባል። አቀራረቡም በመማርያ/ማስተማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ካለው ይዘት በጣም ጠባብና ቀላል በሆነ መንገድ ነው የሚቀርበው።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎችዎ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ሊገልፁልኝ ይችላሉ?

መ. ተማሪዎቹ በሬዲዮ መማሩን ይወዱታል፥ ግን የትምህርቱ ይዘት ስለሚደገምባቸውና ያንን ይዘት ተምረውትና ተፈትነትም ያለፉት ስለሚሆን ትምህርቱ አያጓጓቸውም። በዚያ ላይ የትምህርቱ አቀራረብ ቀላል ነው። እኔ ለምሳሌ አምስተኛ ክፍል አሁንም አስተምራለሁ። እነዚህን አሁን 7ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎጼችም እንዲሁ አምስተኛ ክፍል አስተምሬያቸዋለሁ። የአምስተኛው ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ከሰባተኛው ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጠጠር ያለና ደረጃውን የጠበቀ ይመስለኛል። አሁን የሚማሩት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮም ሆነ መደበኛው ትምህርት በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ የተሻለ መሆን ሲገባው መቅለሉ የተማሪውን የመማር ፍላጎት ይቀንሰዋል። በተማሪዎቻችን ላይ የሚታየውም ይኸው ነው? ተማሪዎቹ ደግሞ የማስተምራቸውን ትምህርት በሬዲዮም ሆነ መደበኛን ትምህርት በጉጉትና በንቃት ካልተከታተሎኝ የእኔንም የማስተማር ፍላጎት መቀነሱ አይቀርም።

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ተማሪውንና የክፍል መምህሩን ለማሳተፍ ያለው ብቃት ምን ያህል ነው?

መ. በቂ የመልመጃ ጥያቄና ለዚያም ሰፋ ያለ ጊዜ ሲኖር ነው። የተማሪዎችን ተሳትፎ ማቅ የሚቻለው። በዚህ የሬዲዮ ትምህርት አቀራረብ ግን የተወሰነ ነገር ያስተምራል ያንኑ ወዲያው ይጠይቃል ማንም ያዳመጠ ተማሪ በቀላሉ ይመልሰዋል። ይህ ተሳትፎ አይባልም። የክፍል መምህሩም ተማሪዎቹን እንዲያሰራ የሚጠይቀው ተግባር በጣም ውሱን ነው።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርቱ ፕሮግራም ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ቀድሞ ይደርሳችኋል?

መ. እየዘገየ አንዳንዴም ግማሽ አመት ላይ ይመጣል፤ አንዳንዴም ሳይመጣ የትምህርቱ አመት ያልቃል:: ዘንድሮም ቢሆን ስርጭቱ ተጀምሮ አለመምህሩ መምሪያ ሳስተምር ከርሜ ነው የመጣው:: የዘንድሮው የሁለተኛ ሰሚስተር ብቻ ነው በወቅቱ የደረሰው::

ጥ. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ እርስዎን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም ቀደም ብለው እንዲዘጋጁ በመርዳት የሚያደርግልዎት አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው?

መ. የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ አቀራረቡም ሆነ የያዘው መመርያ በጣም ውሱን እና ግልፅነትም የጎደለው ነው:: በዚያ ላይ በሬዲዮ የሚቀርበውን ትምህርት ይዘትና አቀራረብ በዝርዝር አውቆ ለመዘጋጀት የሚያስችል አይደለም::

ጥ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ተሳትፈ ወይም እንዲሳተፉ ተጠይቀው ያውቃሉ?

መ. አላውቅም

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለቋንቋው ትምህርት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው ይላሉ?

መ. የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘትና አቀራረብ ከዋናው ትምህርት ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ካልተደገረና የመምህሩ መምሪያም ዘርዝር ያሉ መመርያዎችን እንዲይዝ ተደርጎ ካልተዘጋጀ ትምህርቱን ለማገዝ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በጣም ትንሽ ይመስለኛል::

# ቃለ መጠይቅ 2 ሀ.

መምህር፡ ታዬ አየለ

ቀን፡ 26/7/1992

ሰዓት፡ 3፡00 -3፡55

መምህር ታዬ አየለ በዕድገት በኅብረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር ናቸው፡፡ ቃለ መጠይቁም የተካሄደው በትምህርት ቤቱ የትምህርት ማዕከል በር አካባቢ ባለው ደረጃ ላይ ተቀምጠን ነው፡፡ ከአቶ ታዬ አየለ ጋር የተዋወቅነው የካቲት 25 ቀን 1992 ዓ.ም. የትምህርት ቤቱ ዩኒት መሪ በሆኑት በአቶ ተስፋዬ አማካኝነት ነበር፡፡ ስለ መጠይቁ ዓላማና ይዘት ካስረዳኋቸው በኋላ ነበር ለተጠቀሰው ቀን ቀጠሮ ይዘን የተለያየነው፡፡ በቀጠሮው ቀንና ሰዓት ተገናኝተን ቃለ መጠይቁን ቀጠልን፡፡

ጥ. የትምህርት ቤታችሁ ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል እንደሆነ ቢገልፁልኝ?

መ. የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ትኩረት ሰጥቶ ሲከታተል አላየሁም፡፡ እኔ ለራሴ ፕሮግራሙን ተከታትዬ በሰዓቱ ፕሮግራሙን ካልተጠቀምኩ ሌላ አካል ሲጠይቅና ሲከታተል አላየሁም፡፡

ጥ. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. አልፎ አልፎ መብራት ሲቋረጥ ፕሮግራሙን ለመከታተል የባትሪ ድንጋይ እጥረት ከማጋጠሙ በቀር የሬዲዮ ችግር አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ ያሉት ሬዲዮኖች ጥራትም ቢሆን ምንም አይል፡፡

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለክፍሉ ደረጃ ከተዘጋጀው፥ የመማርያንና ማስተማሪያ መጽሀፍ ጋር ያለ የይዘት ግንኙነት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. የተማሪዎቹ የመማርያ መጽሃፍም በሬዲዮ የሚተላለፈው የአማርኛ ቋንቋን በተመለከተ ትምህርቱ ከመደበኛው ትምህርት ትዘትና አሰጣጥ ጋር ተዛማጅነት ይጎለዋል፡፡ በዚያ

ላይ ትምህርት በሬዲዮው በራሱም ሆነ ከመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት ጋር ተከታታይነት የለም። በመማርያ መጽሀፉም ሆነ በማስተማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያልቀረቡ ይዘቶችም በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚቀርቡበት ጊዜ አለ።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎችዎ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ቢገልፁልኝ?

መ. በሬዲዮ የሚተላለፈው ትምህርት ከተማሪዎች ደረጃና ችሎታ ጋር ሲነፃፀር በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ቀላልና ተራ በመሆኑ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት አይስብም። የትምህርቱ ይዘትም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብር ሳይሆን በቲዎሪ ላይ የተመሰረተ ነው። በአቀራረቡም ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን እንዲለማመዱ የሚያደርግ ስላልሆነ የተማሪውን የመማር ፍላጎት አይስብም። በዚያ ላይ አቀራረቡ ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ ስለሆነ እኔንም አይስበኝም ተማሪውንም አያነቃቃም።

ጥ. በርስዎ ግምት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ተማሪውንና የክፍል መምህሩን ምን ያህል ያሳትፋል?

መ. አቀራረቡ እራሱ የተማሪውን ተሳትፎ በትክክል ለመገመት የሚያስችል አይደለም። የተወሰነውን የትምህርት ይዘትም እራሱ የሬዲዮ መምህሩ ነው የሚያቀርበው መጨረሻ ላይ ሁለት ወይም ሶስት ጥያቄዎች ይቀርባሉ። ተማሪዎች ለእነዚያ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ የሚሰጠው ጊዜም አጭር ስለሆነ ከሁለት ተማሪ በላይ መሳተፍ አይችልም። የሚቀርቡ ጥያቄዎችም በጣም ቀላልና አጭር መልስ ብቻ የሚጠይቁ ናቸው። የክፍል መምህሩም ምንም የሚሳተፈው ነገር የለም። የተወሰኑ ቃላትን ሀረጎችን ወይም ስንኞችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ መፃፍና በጥያቄ ጊዜ ቢበዛ የሁለት የተማሪዎችን መልስ መቀበል ብቻ ነው።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርቱ ስርጭቱ ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ቅደሞ ይደርሳችኋል።

መ. ብዙውን ጊዜ ዘግይቶ ነው የሚደርሰው አንዳንድ ጊዜ ያለመምሪያ እያስተማርን አመቱ ያልቃል።

ጥ. የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ እርስዎን ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ቀደም ብለው እንዲዘጋጁ በመርዳት የሚያበረክትልዎት አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው?

መ. አንተ መጽሀፉን አላየኸውም እንጂ ስለ ትምህርቱ እኮ ይህ ነው የሚባል ነገር ለመምሩ የሚያሳየውና የሚመራው ነገር የለም:: የትምህርቱን ርዕስ ይዘት፥ ዓላማ የአቀራረብ ዘዴ ይህ ነው ካለ በኋላ ከትምህርት በሬዲዮ ስርጭት በፊት ጊዜና በኋላ ሥራ ወይም አድርግ ብሎ የሚያዛቸው መመሪያዎች ግልፅነት የላቸውም:: የትምህርቱን ዝርዝር ይዘትና አቀራረብ በግልፅና በዝርዝር ስለማይጠቁም አስቀድሞ ለመዘጋጀት አያበቃም::

ጥ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ተሳትፈው ወይም እንዲሳተፉ ተጠይቀ ያውቃሉ?

መ. አላውቅም

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም መኖር ለቋንቋው ትመህርት የሚያበረክተው አስተኦ ምን ያህል ነው ይላሉ?

መ. በእኔ አስተያየት አሁን ባለበት ሁኔታ ምንም አስተዋፅኦ የለውም:: ለወደፊት ካልተሻሻለ ቢቀር ይሻላል:: ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ትምህርቱ ከመደበኛው ትምህርት ጋር ተጣጥሞ አይሄድም፥ በይዘቱም ስህተት ይታይበታል፥ የተማሪውን ደረጃ አይመጥንም ቀላል ነው፥ የሬዲዮው ፕሮግራም ከመቅረቡ በፊት የትምህርቱን ይዘት፥ ቃላት ሀረጎችና ከስርጭቱ በኋላም የመለማመጃ ጥያቄን በመምህሩ መምሪያ ላይ ማቅረብ ሲኖርበት ይህን አያደርግም፤ ይህ የሚያመለክተው ፕሮግራሙ ብቃት ባላቸ ባለሙያዎች ተጠንቶ አለመዘጋጀቱን ነው:: ስለዚህ በሬዲዮ የሚተላለፈው ትምህርት ለአማርኛ ቋንቋው ትምህርት የተሻለ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በቂ ቋንቋ ትምህርትና ልምድ ባላቸው ሰዎች በጥንቃቄና በጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት አለበት::

# መጠይቅ 2-ለ

መምህር፡ ቸርነት መኮንን

የትምህርት ደረጃ፡

የአገልግሎት ዘመን፡

ቀን፡ 26/7/1992

ሰዓት፡ ከ4፡10 - 5፡15

መምህር ቸርነት መኮንን በእድገት በኅብረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር ናቸው፡፡ መጠይቁ የተካሄደው በትምህርት ቤታቸው ቅርጥ ግቢ ውስጥ፥ ከትምህርት ቤቱ የትምህርት ማዕከል ፊት ለፊት ባለው ቦታ ነው፡፡ ከአቶ ቸርነት መኮንን ጋር ያስተዋወቁኝ የትምህርት ቤቱ ዩኒት መሪ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ናቸው፡፡ የካቲት በተዋወቅንበት የካቲት 25 ቀን 1992 ዓ.ም. ለየካቲት 28 ቀን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡ በተቃጠርንበት ቀንና ሰዓት ተገናኝተን ቃለመጠይቁን ቀጠልን፡፡

ጥ. የትምህርት ቤታችሁ ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል እንደሆነ ቢገልፁልኝ?

መ. የአማርኛውንም ሆነ የሌላን ትምህርት በሬዲዮ የመጠቀም ግዴታ ያለ ይመስለኛል፡፡ እነሱም ይህንን ለማስፈፀም የትምህርት በሬዲዮንን ፕሮግራም በአግባቡና በሰዓቱ እንድንጠቀም በተለያየ አጋጣሚ ማሳሰቢያ ይሰጣሉ፡፡ ከዚያ ያለፈ ክትትልና ትኩረት ሲደረግለት ግን አላየሁም፡፡ ከላይ መመርያው ባይኖር የሚያስታውሰውም ያለ አይመስለኝም፡፡

ጥ. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ፡፡

መ. እኔ በበኩሌ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ የማስተምርበት ሬዲዮ ችግር ገጥሞኝ አያውቅም፡፡ ሌሎች መምህራንም በዚህ በኩል ሲያማርሩ አልሰማሁም፡፡

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት

ለዚህ ክፍል ደረጃ ከተዘጋጁት፥ የመማርያና ማስተማሪያ መጻህፍት ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. የሬዲዮው ትምህርቱ ከተማሪው መጻህፍትም ሆነ ከመምህሩ ማስተማሪያ መጽሀፍ ጋር አብሮ አይሄድም።

ጥ. አብሮ አይሄድም ሲሉ ቢያብራሩልኝ።

መ. አንደኛ ነገር በርዕሱም ቢሆን ተከታታይነት የለውም። እኛ ዋናውን የመምህር መምርያ ተከትለን አስተምረን ካለፍንና ሌላ ርዕስ እያስተማርን እያለን አስተምረን ያለፍነው ትምህርት ተደግሞ ጣልቃ ይገባል። አንዳንዴ እኛ ካስተማርነው የተለየ ነገር በማቅረብም በተማሪና በመምህር መካከል አለመግባባትንና ግጭትን ይፈጥራል። ይህ ሁሉ በሬዲዮው ትምህርትና በዋናው የመማርያ/ማስተማሪያ መፃፍት መካከል የይዘት ልዩነት መኖሩን የሚያመለክት ነው።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎችዎ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ቢገልፁልኝ?

መ. የትምህርቱ ይዘትም ሆነ አቀራረብ ብዙውን ጊዜ ከደረጃቸው በታች ስለሚሆንና ብዙ ጊዜም እኔ ያስተማርኳቸው ትምህርት በቀለለ ሁኔታ ስለሚቀርብላቸው የሚሰለቻቸው ይመስለኛል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ብዙ ጊዜ የማዳመጥ ትኩረታቸው ይቀንሳል። በበለጠ ደግሞ እነሱ ብትጠይቃቸው የሚሻል ይመስለኛል። በእኔ በኩል ግን ምንም ለውጥ የለውም። ማለትም የትምህርቱ ይዘትም ሆነ አቀራረብ ተማሪዎችን ምን ያህል አስተማራቸው ከማለት ካልሆነ በቀር ለእኔ የሚፈጥርብኝ የተለየ ስሜት የለም። እንዳልኩህ አልኩህ ትምህርቱ ሲደጋገምና ከደረጃቸው በታች ቀላል ሆኖ ሲቀርብ ደስ አይለኝም።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርቱ ፕሮገራም ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ቀድሞ ይደርሳችኋል?

መ. ብዙን ጊዜ በጣም ዘግይቶ ነው የሚመጣው። የዚህን ወሰነ ትምህርት መምሪያ ብቻ ነው ቀደም ብለን ያገኘነው

ጥ. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ እርስዎን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ቀደም ብለው እንዲዘጋጁ በመርዳት የሚያደርግሎት አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው? መ. ብዙም አስተዋፅኦ የለውም፡፡

ጥ. ምን ችግር አለበት?

መ. በሚቀርበው ይዘት ላይ ዝርዝር ያለ መመርያ ቢኖርና በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ምን ምን ነጥቦች እንደሚነሱ፥ ምን ምን ጥያቄዎች እንደሚቀርቡ አስቀድሞ ቢታወቅና ትክክለኛና ወጥ የሆነ መልሳቸውም ቢጠቆም መምህሩን በሚገባ እንዲዘጋጅ ይረዱታል ብዬ አምናለሁ፡፡ የመምህሩ መምርያ በዚህ መልኩ የተሟላ ሆኖ ቀደም ብሎ ቢደርስ ቅድም ያነሳውልህን የይዘት መደጋገም ለመቀነስና አንድን ይዘት በተለያየ መንገድ ላለማስተማር ይረዳል፡፡

ጥ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ተሳትፈው ወይም እንዲሳተፉ ተጠይቀው ያውቃሉ፡

መ. ተሳትፌም፥ ተጠይቄም አላውቅም፡፡

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለቋንቋው ትምህርት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው?

መ. አሁን ባለበት አቀራረብ ከሆነ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አለ ብዬ አላምንም፡፡ እንዲያም የተማሪውንና የመምህሩን ክፍለ ጊዜና የመንግስትንም ገንዘብ አለአግባብ ማባከኑ ነው የሚታየኝ፡፡ ነገር ግን ከመደበኛ ትምህርት ጋር በትክክል እየተገናዘበና የተማሪውን ደረጃ በሚጠብቅ መልክ እንዲቀርብ ከተደረገ ለትምህርቱ የሚኖረው እገዛ ከፍተኛ ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

## መጠይቅ 3

መምህር ተናኘ አላምረው

ቀን: 28/7/1992

ሰዓት: ከ4:10-5:00

ቃለ መጠይቁ የተካሄደው በፍሬህይት ቁጥር 2 ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው:: የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ጣዕመ አምባዬ መምህርቷን ቢሮአቸው ድረስ አስግርተው ካስተዋቁን በኋላ ለምፈልገው መረጃ እንዲተባበሩኝ ማሳሰቢያ ከሰጡልኝ በኋላ ከቢሮአቸው ወጥተን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ካለው መስክ ተቀምጠን ውይይታችንን ቀጠልን::

ጥ. የትምህርት ቤታችሁ ርዕሰ መምህር/ራን ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው?

መ. ብዙ ጊዜ ስበሰባ ሲኖር ሰዓቱን አክብረን ፕሮግራሙን እንድንጠቀም ማሳሰቢያ ይሰጣል፤ ለፕሮግራሙ መቅጃ የቴፕ ክር ስንጠይቅም ይሰጠናል ስለዚህ ምንም ችግር የለብንም::

ጥ. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. በትምህርት ቤቱ በጣም ብዙ ሬዲዮ ስላለ በዚህ በኩል ምንም ችግር የለም:: ከበቂ በላይ ሬዲዮ ስላለ የተሻለ ጥራት ያለውን ሬዲዮ መርጠን መጠቀም እንችላለን:: አስቀድሞ በታወቀ ምክንያት ለምሳሌ ብስብሰባ ወይም በሌላ ምክንያት ፕሮግራሙን መጠቀም እንደሚችል ከታወቀ፣ በትምህርት ቤቱ ሚኒ ሚዲያ አማካይነት ፕሮግራሙ በቴፕ ተቀድቶ እንዲቆየን እናደርግና ሌላ ጊዜ እናስተምርበታለን::

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለዚህ የክፍል ደረጃ ከተዘጋጁት፣ የመማርያና ማስተማርያ መፃህፍት ጋር ያለው የይዘት ግንኙነት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. ትምህርት በሬዲዮው ያው መማርያና ማስተማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያለውንና እኛ ያስተማርነውን ነው የሚያስተምረው አቀራረቡ ግን በጣም ቀላል ስለሆነ ተማሪዎቹ አንዳንድ ጊዜ እንደቀልድ ወይም ጫወታ ነው የሚያዩት::

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎችዎ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ሊገልፁልኝ ይቻላሉ?

መ. እኔ በበኩሌ ፕሮግራሙ ለመደበኛው ትምህርት የሚኖረው እገዛ ከፍተኛ ይመስለኛል፣ ተማሪዎችም ይወዱታል፣ ግን ቅድም እንዳልኩህ አቀራረቡ ከተማሪዎቹ ደረጃ ያነሰና እኛ ከምናስተምርበት አቀራረብም የቀለለ ስለሆነ ተማሪዎቹ እንደ ቀልድና መዝናኛ የሚቆጥሩት ይመስለኛል። በዚያ ላይ ቀደም ብለው በክፍል ውስጥ ከተማሩት የተለየ አዲስ ነገር ስለማያገኙበት የመስላቸትና የማዳመጥ ፍላጎታቸ የሚቀንስበት ሁኔታም አለ። ስለዚህ ደረጃቸውን የሚመጥን አዳዲስ ነገር ቢያቀርብ የበለጠ በተማሪዎች ተወዳጅ ሊሆን የሚችል ይመስለኛል። በተረፈ ተማሪዎችን ብትጠይቃቸው የበለጠ ከራሳቸው ትሰማለህ።

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ተማሪዎችና የክፍል መምህራንን ለማሳተፍ ያለው ብቃት ምን ያህል ነው?

መ. መምህሩ እነኳን ምን ይሳተፋል። ሁልጊዜም በትምህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ የሚሰራው ተግባር የታወቀ ነው። ሬዲዮኑን በሰዓቱ መክፈት፥ የክፍሉን ፀጥታ መቆጣጠር፥ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ፃፍ የተባለውን መፃፍና ለሚጠየቅ ጥያቄ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመቀበል ነው። ተማሪዎቹም ማዳመጥና ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ መስጠት ነው። ይህን በሚገባ ያከናውናሉ።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርቱ ፕሮገራም ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ነው ቀድሞ የሚደርሰው።

ሠ. ብዙ ጊዜ ዘግይቶ ነው የሚደርሰው። ዘንድሮም እንዲያውም ትንሽ ተሻሽሏል እንጂ ሳይደርሰን አመቱ የሚያልፍበት ጊዜም አለ። ዘንድሮ የአንደኛውና የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የመምህሩ መምሪያ ለየብቻ የተያይቶ ነው የተዘጋጀው። የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ትንሽ ዘግይቶ ትምህርቱ መተላለፍ ከጀመረ በኋላ ነው የደረሰው። የሁለኛው ወሰነ ትምህርት ግን ቀደም ብሎ ነው የደረሰው።

ጥ. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ እርስዎን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮገራም ቀደም ብለው እንዲዘጋጁ በመርዳት የሚያደርግሎት አስተዋፅኦ ምን ያህል

ነው?

መ: በሬዲዮ የሚቀርበውን ትምህርት እኔ አስቀድሜ ያስተማርኩትና የማውቀው ስለሆነ ምንም የሚረዳኝ ነገር የለም። በዚያ ላይ የሚያቀርበው ሰፋ ያለ ሀሳብና መልመጃ የለውም። እነዚህን ቃላት፥ ወይም ሀረጎች ወይም ሌላ የቋንቋ ክፍል በዚህ መልክ አስተምር ብሎ እንደመደበኛው የመምህር መምሪያ የሚመራው ነገር የለም።

ጥ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ዝግጅት ተሳትፈው ወይም እንዲሳተፉ ተጠይቀው ያውቃሉ?

መ. ተሳትፌም ተጠይቄም አላውቅም።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለቋንቋው ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው ይላሉ?

መ. መደበኛውን ትምህርት በማገዝና የትምህርቱንም ጥራት በማሻሻል ትምህርት በሬዲዮው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል። ታዲያ አቀራረቡ ቢሻሻል፥ የተማሪውን ደረጃ እንዲመጥን ቢደረግና የመምህር መምሪያውም ቢሻሻል የበለጠ አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል ብዬ አምናለሁ።

# ቃለመጠይቅ 4

መምህር: ተመስገን አለምነህ

ቀን: 6/8/1992

ሰዓት: ከ5:00 - 6:35

ቃለመጠይቁ የተካሄደው በእንጦጦ አምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ከትምህርት ቤቱ መምህራንና ሰራተኞች መዝናኛ ክበብ ፊት ለፊት ባለው መናፈሻ ውስጥ ነው:: ከአቶ ተመስገን ጋር የተዋወቅነው የካቲት 12 ቀን 1992 ዓ.ም/ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በአቶ ሀብቱ አምባዬ አማካይነት ነበር:: ከዚያም በኋላ የካቲት 15 ቀን በተላለፈው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ ክፍለ ጊዜ እሳቸው በክፍል መምህርነት እኔ በተመልካችነት አብረን ነበርን:: የቃለመጠይቁን ዓላማና ይዘትም በዚያው ቀን አስረድቻቸው÷ የሚመቻቸውን ቀንና ሰዓት እንዲወስኑልኝ ጠይቄያቸው ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት እንደሚመቻቸው ነግረውኝ ተለያየን:: ሁለታችንም በተወሰነው ቀንና ሰዓት ተገናኝተን ቃለ መጠይቁን ቀጠልን::

ጥ. የትምህርት ቤታችሁ ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል እንደሆነ ቢገልፁልኝ?

መ. የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራምን እንደመደበኛ ትምህርት ባለመቁጠር ይመስለኛል ትምህርቱን የምናስተምርበት የተመቻቸ የመማርያ ክፍል÷ ጥቁር ሰሌዳ መብራትና ሶኬት የለም:: በትምህርቱ ስርጭት ወቅት የሬዲዮ መምህሩ "እባክዎን መምህር በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው" ሲሉ የምንፅፍበትና ሌሎችንም ምሳሌዎች የምንሰጥበት ጥቁር ሰሌዳ የለም:: ችግሩን ደጋግመን ብናመለክትም የተሰጠ መፍትሄ የለም:: በዚህ ላይ አንተም እንዳየኸው በአንድ ጊዜ የሁለት ክፍል ተማሪዎችን በአንድ ክፍል ውስጥ ነው የምናስተምረው:: በክፍሉ ውስጥ ያለው ወንበር ትንሽ ነው:: በዚያ ላይ ክፍሉ አቧራ ነው:: ግማሹ ደብተሩ ላይ ግማሹም ድንጋይ ከውጭ እያመጣ ነው የሚቀመጠው:: አንዳንዴም መቀመጫ ሲያጣ ጥሎት ይሄዳል:: ታዲያ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለትምህርት በሬዲዮ ትኩረት የሚሰጥ ቢሆን ኖሮ

ችግሮቹን ቀስ በቀስም ቢሆን ለመቅረፍ መሞከር ይችል ነበር፡፡ ግን ምንም ጥረት ሲደረግ አናይም፡፡

ጥ. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ሊገልፁልኝ ይቸላሉ?

መ. በትምህርት ቤቱ ካሉት ስድስት ሬዲዮኖች ውስጥ ሁለቱ ብቻ ናቸው የሚሰሩት፡፡ የተቀሩት አራቱ በጭራሽ አይሰሩም፡፡ እነዚህኑ ነው እየተቀባበልንና እያዘዋወርን የምንጠቀመው፡፡

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለዚሁ ክፍል ደረጃ ከተዘጋጁት፥ የመማርያና የማስተማርያ መጻህፍት ጋር ያለው የይዘት ግንኙነት ምን ይመስላል?

የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ይዘት ከመማርያ/ማስተማሪያ መጻህፍት ይዘት ጋር መመሳሰል አለው፡፡ በዚህ በኩል ያለው ችግር የሬዲዮው ትምህርት ይዘቶች እኔ ከማስተምረው ትምህርት ጋር በተጣጣመና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልክ አይቀርብም፡፡ ብዙ ጊዜ አንድ ይዘት እኔ በክፍል ውስጥ አስተምሬ ተማሪዎቹምግንዛቤ ከጨበጡ በኋላ ይዘቱ በሬዲዮ ይቀርባል፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪው ይሰላቻል፡፡ ለምሳሌ ባለፈው አርብ ሲተላለፍ ያዳመጥከውን ግጥም እኛ በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት አስተምሬናቸዋል፡፡ ሌላው ችግር የቅደም ተከተል ችግር ነው፡፡ እኔ ሀሙስ አንድ ርዕስ ጀምሬ ሳልጨርስ አርብ በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አዲስ ይዘት ጣልቃ ይገባል፡፡ እንደገና ሰኞ፥ የጀመርኩትን ርዕስ ማስተማር እቀጥላለሁ፡፡ በዚህም ትምህርቱ ተከታታይነቱን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ሊገልፁልኝ ይቸላሉ?

መ. እኔ ስመለከተው ተማሪዎቹ ለትምህርት በሬዲዮ ፍላጎት ያላቸው ይመስለኛል፡፡ በተለይ በትምህርታቸው ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎች አዲስ እውቀት እናገኛለን የሚል ጉጉት ይታይባቸዋል፡፡ ይሄን የምለው በተለያየ ምክንያት በስብሰባ፥ ወይም በባትሪ ድንጋይ ችግር ምክንያት የትምህርት በሬዲዮውን ካልተከታተሉ ከትምህርት ፈረቃቸው ውጭ

በቤታቸው አዳምጠው ይነግሩኛል። ይህን የሚያደርጉት እንግዲህ ፍላጎት ቢኖራቸው ነው። በክፍል ውስጥም አብዛኞቹ ተማሪዎች የሚቀመጡበት አግዳሚ እንኳን ሳይኖር ተቀምጠው ማዳመጣቸውና መሳተፋቸው የፍላጎታቸው ምልክት ይመስለኛል።

በእኔ በኩል ግን ትምህርት በሬዲዮው ለትምህርቱ የሚያደርገው እገዛ ከፍተኛ እንደሆነ ባምንም በትምህርት ቤቱ ውስጥም ሆነ÷ በፕሮግራሙ አቀራረብ የሚታዩት ችግሮች ለፕሮግራሙ ያለኝን ፍላጎት ቀንሶብኛል።

ጥ. በርስዎ ግምት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ተማሪውንና የክፍል መምህሩን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ለማሳተፍ ያለው ብቃት ምን ያህል ነው?

መ. እኔ የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪውንም ሆነ መምህሩን በበቂ ሁኔታ ሲያሳትፍ አላየሁም። ለተማሪው የሚቀርቡ የተወሰኑ ጥያቄዎች ቢኖሩም ለተማሪዎች መልስ መስጫ የሚሰጠው ጊዜ በጣም አጭር ስለሆነ ከሁለት ተማሪ በላይ መልስ መስጠት አይችልም። መልሱንም ወዲያው እራሱ ስለሚመልሰው በዚያው ያበቃል። የክፍል መምህሩንም ቢሆን የተወሰኑ ቃላትን÷ሀረጎችን÷ ስንኞችንና አረፍተ ነገሮችን በሰሌዳው ላይ ፃፍ ከማለትና የተማሪዎችን መልስ ይቀበሉ ከማለት ሌላ ምንም የለም።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርቱ ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ቀድሞ ይደርሳችኋል?

መ. የዘንድሮ የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ፕሮግራም የመምህሩ መምሪያ እንኳን ቀደም ብሎ ነው የደረሰው ከዚያ በፊት ግን አንድ ጊዜም በሰዓቱ ቀደም ብሎ የደረሰበትን ጊዜ አላስታወስም። መምህሩም ተማሪውም በፕሮግራሙ ምን እንደሚተላለፍ ስናውቅ ሲተላለፍ ብቻ ነው የትምህርቱን ርዕስ ስናውቅ የነበረው። አንድ ጊዜ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አስመልክቶ ናዝሬት በተደረገ ሴሚናር ተሳትፎ በነበረበት ወቅት ያለመምህሩ መምሪያ ትምህርት በሬዲዮ ባይተላለፍ ይሻላል ተብለን የመምሪያውን አስፈላጊነት አጥብቀው ነበር የነገሩን። ይህ እንዳይሆንም የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ስርጭት ከመጀመሩ አንድ ወር ገደማ ቀደም ብሎ እንዲደርሳችሁ ይደረጋልም ተብለን ነበር። በተግባር የታየው ግን አሁን በዚህ ሴሚስተር ብቻ ነው።

ጥ. የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ የክፍል መምህሩን ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለማዘጋጀት ያለው ብቃት ምን ያህል ነው ይላሉ?

መ. የትምህርት በሬዲዮ የመመህሩ መምሪያ ብዙ ነገሮች ይጎሉታል:: በዕለቱ የሚቀርበውን የትምህርት ዓላማና ይዘት ከመጠቆም አልፎ÷ መምህሩ ተማሪዎችን ምን ማሰራት እንዳለበት አያመለክትም÷ የቃላትንና የሀረጎችን ፍቺ እንኳን በበቂ ሁኔታ አይሰጥም:: መልመጃዎችም የሉትም:: በመሆኑም በእኔ ግምት መምርያው ቁንፅል ነው::

ጥ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ተሳትፈው ወይም እንዲሳተፉ ተጠይቀው ያውቃሉ?

መ. ቅድም እንደነገርኩህ የትምህርት በሬዲዮን ፕሮግራም አስመልክቶ ናዝሬት ለአምስት ቀናት ከተሳተፍኩ ሴሚናር በቀር ሌላ ምንም ተሳትፌ አላውቅም:: አሁን አንተ የምትለውን አይነት ዝግጅት ውስጥ የተሳተፉ መምህር መኖሩንም ሰምቼ አላውቅም:: ይልቅ አሁን አንተ እንደምታደርገው የትምህርቱን ይዘትና አቀራረብ አስመልክቶ ከመምህራኑ ሀሳብና አስተያየት በመሰብሰብ እንዲሻሻል ቢደረግ የተሻለ ውጤት ማስገኘት የሚቻል ይመስለኛል::

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ መኖር ለቋንቋው ትምህርት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ አለ?

መ. በጣም እንጂ:: ታዲያ የሬዲዮ ትምህርቱ አስተዋፅኦ ከፍ እንዲል ከመደበኛው የክፍል ትምህርት ጋር እንዳይዘበራረቅ ይዘቱ ቅደም ተከተሉም መጠበቅና መቀናጀት አለበት:: የትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያም ተሟልቶና የተለያዩ መልመጥያቄዎችን መያዝ አለበት:: የትምህርት ማጣቀሻ መጻህፍትም ቢጠቆሙ ጥሩ ነው:: ይህ ካልሆነና አሁን ባለበት ሁኔታ ከቀጠለ ብዙም አስተዋፅኦ የሚኖረው አይመስለኝም::

## መጠይቅ 5

መምህር፡ አለሙ መተኪያ

ትምህርት ቤት፡ አፍሪካ አንድነት ቁጥር 1

ቀን፡ 6/8/1992

ሰዓት፡ 9፡45 - 10፡20

ከአቶ አለሙ መተኪያ ጋር ቃለ መጠይቁን ከማካሄዳችን በፊት ለሶስት ክፈለ ጊዜያት የትምህርት በሬዲዮው ክፍለ ጊዜ ሲተላለፍ እሳቸው በክፍል መምህርነት እኔ በተመልካችነት አብረን በማሳለፍ ቆይተናል፡፡ ቀደም ብሎ ከሶስት ሳምንት በፊት ከአቶ አለሙ ጋር ያስተዋወቁኝ የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕስ መምህር አቶ አበራ አታክልት ናቸው፡፡ ቃለመጠይቁንም ያካሄድነው በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመምህራን ማረፍያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡

ጥ. የትምህርት ቤታችሁ ርዕስ መምህር/ራን/ ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው?

መ. የትምህርት ቤቱ ርዕስ መምህር አቶ ኃይሉ ውበሸት ወደዚህ ትመህርት ቤት ተዛውረው የመጡት በቅርብ ጊዜ ነው ስለሆነም ስለእሳቸው ብዙ የምለው ነገር የለም፡፡ የተምህርት ጉዳዮችን በቅርብ የሚከታተሉት ምክትል ርዕስ መመህሩ አቶ አበራ አታክልት ግን በዚህ ቦታና ኃላፊነት በሰሩባቸው አመታት ለመደበኛውም ሆነ ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮገራም በከፍተኛ ትኩረት ክትትል ያደርጋሉ፡፡

ጥ. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. በዚህ በኩል አንተም እንዳየኸው ምንም ችግር የለብንም፡፡ በተለያዩ የጥዋቱ የትመህርት በሬዲዮው ስርጭት ከእኛ የትምህርት ጊዜ ስሌዳ ጋር አብሮ ስለማይሄድ ፕሮግራሙን በቴፕ ቀድተን ነው በክፍለ ጊዜያችን የምናስተምረው፡፡ በአንድ ካሴት አራት ፕሮግራም እንቀዳበታለን፡፡ ካሉን አምስት ምድቦች ከሰዓት በኋላ በቀጥታ የተመለከተው ፕሮግራም የሚማሩት በዚህ አንተ በተመለከትከው ክፍል ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡

ሌሎቹ ግን በቴፕ ክር የተቀዳውን ነው የሚማሩት።

ጥ. ማነው የሚቀዳላችሁ?

መ. እራሳችን ነን።

ጥ. የእናንተ ቅጅ ጥራቱን አይቀንሰውም?

መ. በጥንቃቄና ጥራት ባለው መቅጃ ስለሚቀዳ ምንም ለውጥ የለውም።

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለዚህ የክፍል ደረጃ ከተዘጋጁት፥ የመማርያና ማስተማሪያ መጻህፍት ጋር ያለው የይዘት ግንኙነት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ።

መ. ከመማርያ ማስተማሪያ መጽሀፉ ጋር የትምህርት በሬዲዮው ይዘት ተመሳሳይ ነው።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎችዎ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ሊገልፁልኝ ይቻላሉ?

መ. ተማሪዎቹን እንዳየሁቸው በፍላጎት ነው የሚከታተሉትና የሚሳተፉት። ይዘቱም ሆነ አቀራረቡ ግን ከደረጃቸው በታች ስለሆነ አዲስ ነገር የሚያገኙበት አይመስለኝም። በእኔ በኩል ግን ፕሮግራሙ ብዙ ነገሮች የሚጎሉት ይመስለኛል። እኔ የማታም ጭምር አራተኛ ክፍልም አስተምራለሁ፥ የአምስተኛና የስድስተኛ ክፍልን የመማርያ መጽሀፍን አይቻለሁ። የ7ኛ ክፍል መጽሀፍም ሆነ የትምህርት በሬዲዮው ከእነዚህ ከታች ካሉ ክፍሎች ያነሰና የቀለለ አቀራረብ ነው ያለው። ይህ ደግሞ ትምህርቱ ለተማሪዎቹ በጣም እንዲቀላቸው ስለደረገ ብዙም እንዳያስቡና በትጋት እንዳይከታተሉ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል። ይህ ነው እንጂ ችግሩ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም መኖር ጠቃሚ ነበር።

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ አቀራረብ ተማሪዎችንና የክፍል መምህራንን ለማሳተፍ ያለው ብቃት ምን ያህል ነው ይላሉ?

መ. እንዳየሁት ነው። ተማሪዎቹ ትምህርቱ ሲለሚቀላቸው የተጠየቀውን ጥያቄ ቀድመው ለመመለስ ይሻማሉ። ለዚያውም የተወሰኑ ጥያቄዎች ናቸው የሚቀርቡት። ስለዚህ ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያለው ብቃት ውሱን ነው የሚመስለኝ። የክፍል መምህራንን ለማሳተፍ ያለው ድርሻ ደግሞ አይታየኝም። በእኔ በኩል በሬዲዮው የሚቀርበውን

ትምህርት ቀደም ብዬ ያስተማርኩትና ፈተናም የወሰዱበት ስለሚሆን አዲስ የምሰራው ነገር የለም፡፡

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ ትምህርት ፕሮገራሙ ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ነው ቀድሞ የሚደርሰው?

መ. ቀድሞ የደረሰበት ጊዜ ትዝ አይለኝም፡፡ አሁን ብቻ የዚህ ሴሚስተር ለብቻው ተዘጋጅቶ በወቅቱ ደርሷል፡፡

ጥ. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ እርስዎን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ቀደም ብለው እንዲዘጋጁ በመርዳት የሚያደርግልዎት አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው?

መ. ቅድም እንደነገርኩህ ትምህርቱን እኔ ቀደም ብዬ ተዘጋጅቼ ያስተማርኩት ስለሆነ ምን የሚያዘጋጀኝ ነገር አለ? በዚያ ላይ አይተኸው እንደሆነ ምንም ግልፅ አድርጎ የሚያሳየው ነገር የለም፡፡ በፕሮግራሙ ለቀረቡት ቃላት እንኳን ፍቺ አይሰጥም፥ ሀሳቦችን አያብራራም ጭፍን ነው፡፡

ጥ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ተሳትፈው ወይም እንዲሳተፉ ተጋብዘው ያውቃሉ?

መ. አላውቅውም፡፡

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለቋንቋው ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው?

መ. በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ተሻሽሎና የተማሪውን ደረጃ እንዲመጥን ተደርጎ ቢቀርብ ጥሩ አስተዋፅኦ ሊያበረክት የሚችል ይመስለኛል፡፡ በዚህ በአሁኑ ይዞታው ከቀጠለ ግን አስተዋጽኦው አይታየኝም፡፡

## መጠይቅ 6

መምህር: ዳኛቸው ግዮን

ቀን: 25/7/92

ትምህርት ቤት: ገላን ቁጥር 1

ሰዓት: ከ3:20 - 4:25

ከመምህር ዮናስ ብርሃኑ ጋር ቃለ መጠይቁ የተካሄደው በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኘው መስክ ላይ ነው:: የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የሆኑት አቶ ታደሰ ምትኩ ከመምህር ዮናስ ብርሃኑ ጋር ካስተዋወቁኝና መጠይቅ የሚሞሉ ተማሪዎችን ስመርጥ የሚያስፈልጉኝን እርዳታ እንዲያደርጉልኝና ከሳቸውም የምፈልገው መረጃ ካለ እንዲተባበሩኝ አሳስበውልኝ እሳቸው ወደ ስራቸው ተመልሰዋል:: በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ተማሪዎችን መጠይቅ ካስሞላው በኋላ በተጠቀሰው ሰዓትና ቦታ ተገናኝተን ቃለ መጠይቁን አካሂደናል::

ጥ. የትምህርት ቤታችሁ ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል እንደሆነ ቢገልፁልኝ?

መ. አልፎ አልፎ በማሳሰቢያ መልክ የትምህርት በሬዲዮኑን ፕሮግራም እንድንጠቀምበት ከሚነግሩን በስተቀር የተለየ ትኩረት ሰጥተውት ለትምህርት በሬዲዮው የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሲያሟሉ አይታዩም:: የሁለት ክፍል ተማሪዎች መቀመጫ ወንበርም ሆነ ማስደገፊያ የሚሆን ጠረጴዛ በሌለበት ባዶ ክፍል ውስጥ ነው እንዲማሩ የሚደረገው:: የመማሪያ ክፍሉም ቅድም አንተ ተማሪዎችን መጠይቅ ያስሞላህበትን ክፍል ነው፤ እንዳየኸው ባዶ ነው በዚያ ላይ ወለሉ አፈርና አቧራማ ነው:: ለትምህርት በሬዲዮው ትኩረት የሚሰጥ አካል ቢኖር ኖሮ ከሞላ ጎደል እንኳን ቢሆን ቀስ በቀስ ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ሲደረግ ይታይ ነበር:: ግን ምንም የለም::

ጥ. በትምህርት ቤታችሁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መቀበያ ሬዲዮ አቅርቦት በብዛትም ሆነ በጥራት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. ሬዲዮኖች መኖሩን አሉ፥ ግን አንደኛ አሮጌዎች ስለሆኑ የጥራት ጉድለት

ይታየባቸዋል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ክፍል ውስጥ ሶኬት ስለሌለ የባትሪ ድንጋይ እጥረት ያጋጥማል፡፡ ባትሪው ሲደክም የድምፁ ጥራት እንደሚቀንስ ይታወቃል፡፡

ጥ. በርስዎ አስተያየት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይዘት ለክፍሉ ደረጃ ከተዘጋጁት መርህ ትምህርት የመማርያና ማስተማርያ መጻህፍት ጋር ያለው የይዘት ግንኙነት ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?

መ. በሬዲዮው የሚተላለፉት ይዘቶች በመማርያ ሆነ በማስተማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ መማርያና ማስተማሪያ መፃህፍቱ ደግሞ አንድ አይነት ናቸው፡፡

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትመህርት በሬዲዮ አቀራረብ ከርስዎም ሆነ ከተማሪዎችዎ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣም ቢገልፁልኝ?

መ. ይቅርታ አድርግልንና እኔ በበኩሌ አይጥመኝም፡፡ እንዲያውም አርብ ሲመጣ ያስጠላኛል፡፡ የመንግስት መመርያ ስለሆነ ነው እንጂ ከእሱ ይልቅ እራሴ ባስተምር ይሻለኛል፡፡

ጥ. ለምን

መ. የሁለት ክፍል ተማሪ በእንደዚያ አይነት ክፍል ውስጥ በዚያ ላይ መቀመጫ የለ፥ ያሁሉ ተማሪ ከውጭ መስኮት ላይ ግማሹ ክፍል ውስጥ ቆሞ፥ ማስታወሻ መፃፍ አይችል ታዲያ ይህን ምን ማስተማር ትለዋለህ? በዚያ ላይ የሬዲዮ መምህሩ ይህን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ፃፉላቸው ይላሉ፥ የታዘዝከውን ስትፅፍ ሌላ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ሁሉ ሰው ደግሞ ሲፅፍ እኩል ፍጥነት የለው፡፡ ብቻ በበኩሌ ብዙው ነገሩ አይስበኝም፡፡ የተማሪዎቼን ፍላጎት በተመለከተ ግን እነሱኑ ጠይቀሀቸው ከሆነ ከዚያ ትረዳለህ፡፡ ያም ሆኖ ግን እነደመዝናኛም ስለሚቆጥሩት ነው መሰለኝ ሲያማርሩና ጥለው ሲሄዱ ብዙም አላይ፡፡

ጥ. በርስዎ ግምት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም አቀራረብ ተማሪውንና የክፍል መምህሩን ለማሳተፍ ያለው ብቃት ምን ያህል ነው ይላሉ?

መ. ይህን በጥቁር ሰሌዳው ላይ የፃፉላቸው፥ ከተማሪዎች መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው፥ እንዲህ አይነት ተግባር አሰሯቸው በማለት የክፍል መምህሩን ለማሳተፍ ይሞክራል፡፡ ግን አቀራረቡ ቀላልና ተማሪዎችም ትምህርቱን ቀደም ብለው የተማሩት ስለሚሆን እራሳቸው መምህሩ ሳይጠብቁ ይመልሳሉ፡፡ የተማሪውን ተሳትፎም በተመለከተ ያው

እንደቆመ ለተጠየቀው ጥያቄ በቃሉ መልስ በመስጠት የተወሰነ ነው።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የመምህሩ መምሪያ የትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ምን ያህል ጊዜ ቀደሞ ይደርሳል?

መ. እኔ እስከማውቀው እንኳን ቀድሞ የደረሰበት ጊዜ ይለም። ወይ የተጀመረ አካባቢ ወይ ከተጀመረ በኋላ ነው የማመጣው። ሌላ ክፍልማ እስካሁን ሳይደርስ ይኸው አመቱ ሊያልቅ ነው።

ጥ. የትምህርት በሬዲዮው የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ የክፍል መምህሩን አስቀድሞ ለትምህርት በሬዲዮው ፕሮግራም ለማዘጋጀት ያለው ብቃት ምን ያህል እንደሆነ ቢገልፁልኝ?

መ. ምንም ማዘጋጀት አይችልም?

ጥ. ምንድ ነው? ችግሩ?

መ. በቃ ምን ተዘጋጀለህ ተማሪውም አስተማሪውም አስቀድሞ የሚያውቀውን ነገር ነው የሚያቀርበው። ወይም መልመጃዎች ሰጥቶ እነዚህን እንደዚህ አሰራቸው መልሳቸውም ይሄ ነው? የሚለው ነገር የለው? ከእሱ ይልቅ የአሁኑ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ የመምህሩ መምሪያ በጥሩ ሁኔታ ተሻሽሎ ቀርቧል።

ጥ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ተሳትፈው ወይም እንዲሳተፉ ተጠይቀው ያውቃሉ?

መ. ተሳትፌም ተጠይቄም አላውቅም።

ጥ. የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም መኖር ለቋንቋው ትምህርት ጥራት መሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው ይላሉ?

መ. በዚህ በእኛ ትምህርት ቤት ሁኔታ ሳይሆን፥ የተመቻቸ የመማርያ ክፍል፥ ጥራት ያለው ሬዲዮ፥ የኤሌትሪክ ሶኬት፥ የተማረው መቀመጫና ማስደገፊያ ዲስክ ከተሟላና ትምህርት በሬዲዮውም በአቀራረቡ ተሻሽሎ ከተዘጋጀ የሚያደርገው ድጋፍና አስተዋፅኦም ከፍተኛ ነው የሚሆነው። የተማሪውንም ሆነ የመምህሩን የመማርና የማስተማር ፍላጎት ያነሳሳል። አሁን ባለበት ሁኔታ ግን ትርፍ ያለው አይመስለኝም። ጊዜና ገንዘብከማባከን በቀር።

ድምጽ

አቅራቢ

መለያ ቁጥር

እንደምን አሉ መምህር

እንደምን አላችሁ ተማሪዎች

ተማሪዎች በዛሬው በ18 ሣምንት የአማርኛ የሬዲዮ ትም ህርት ግጥም በዋና ርዕስ የተዘጋጀ ነው ። ግጥም ማለት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ አይደል ። እስቲ አንዱ ግጥም ለመምህራችሁ የሚነገር ተማሪ?

መምህር ግጥም የሚነገር ተማሪ ካለ ከአንዱ ሁለቱ ይቀ በሏቸው?

20 ሰከንድ

እሺ ግጥሞችን ለመምህራችሁ እንደነገራችሁ ተከሩ አደር ጋለሁ፣
እኔ ደግሞ አንድ ግጥም እነግራችኋለሁ ። መምህር እባ ክዎን የጥቁር ሠሌዳ ላይ ይጻፉት ።

/ ማስጻፍ እንዲቻል ተደርጎ ይነበብ /

ከቶ ምን ያደርጋል የሆዱን ሕመም፣
ማጭድ አይገባበት በሹ አይታረም ።

የመዘይታችሁን በጥሞና አዳምጡ
ይህ የጥቁር ሠሌዳው ላይ የተጻፈው አሁን ያዳመጣችሁት
ግጥም ስንት ስንኝ ያለው ግጥም ነው?

10 ሰከንድ

ግጥሙ ባለሁለት ስንኝ ግጥም ነው አላችሁ?
የሚቀጥለው ጥያቄ....ቤት መምቻው ፊደል ምንድነው?

10ሰከንድ

ቤት መምቻው ፊደል" ምን ነው ካላችሁ ጎበዞች ናችሁ ።

እስቲ ደግሞ በግጥሙ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በቅደም ክፍፍላቸውን ። የመጀመሪያው ስንኝ መነሻ ረቂ ቅሬን አለው ። ስለዚህ የመጀመሪያው ስንኝ መነሻ ረቂ ቅሬን ምን ተብሎ ነው?

10 ሰከንድ

የመጀመሪያው ... መድረክ ሠሪ ... ...

የሚል ነው ካላችሁ? የሚቀጥለውን ተከታተሉ፣ የሁለ
ተኛው ስንኝ መድረሻ ሐረግ ምንድነው?

10 ሰከንድ

« በእጅ አይታረም» የሚለው እንደሆነ ከነገራችሁ
ጥሩ ነው፣

ድምፅ

መሸጋገሪያ

ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባለው የግጥም ትምህርታችሁ
ደገም ቤት መምቻ ስንኝና ቤት መድረሻ ስንኝ፣ስለግ
ጥም በቂም ስራን ሃሳብ በተሟላ ሁኔታ የሚገልጽ መሆ
ኑን ማለትም በሰዱ ገበበ ቢቀርብ በበራ ሁኔታ የሚ
በረሪው ሃሳብ በተሟላ ሁኔታ መገለጽ የሚችል መሆኑን
ትማራላችሁ ።

ይህን ግጥም ተከታተሉ ። መምህር ጥቁር ሠሌዳ ላይ
ይጽፉላችኋል ።

/ ለማስጸፍ እንዲቻል ሬጋ ተበሎ ይነበብ /

የወኪናው መንገዱ ይሰበር ይሰነጠር
በገሬ ዥዎ ቢሆን አደርሰበት ነበር

ይህ ግጥም ስንት ስንኝ አለው?

10 ሰከንድ

ግጥሙ ሁለት ስንኝ አለው ካላችሁ ጥሩ ነው ።

የመጀመሪያው ስንኝ የወኪናው መንገዱ ይሰበር ይሰነጠር
የሚለው ነው ፣ ይህ ስንኝ ቤት መምቻ ስንኝ ይባ
ላል ። የመጀመሪያው ስንኝ ቤት መምቻ ከተባለ የመ
ጠረሻው ስንኝ የትኛውን ሃሳብ የሚያጠቃልለው፣ ግጥ
ሙ መልዕክት የሚያስተላልፍ እንደሆነ የሚያደርገውና
ቤቱን መትቶ የሚጨርሰው ደገም ቤት መድረሻ ይባላል ።

ስለዚህ ቤት መድረሻ የሚባለው ስንኝ
« በገሬ ዥዎ ቢሆን አደርሰበት ነበር የሚለው ነው

ማለት ነው፤

ተማሪዎች እንዳስተዋላችሁት ግጥም ዜማዊ የሆነ አቀራ
ረብ አለው ቢያደምጡት ለጆሮ ይጥማል፤ በቃል ለመያ
ዝም ያመቻል ።
ግጥም ግጥም ለመባል ቢያንስ ሁለት ስንኝ ሊኖረው
ይገባል ። ግጥም ውብ ዜማዊ አቀራረብ ያለው ከመሆኑ
ሌላ በጣም ብሬ የሆነን ሃሣብ በጥም ቀቺት በሆቅ
ቃላት የሚተላለፍን ግጥም ከታች
መምህር አበበ ያን ጥቁር ሠሌዳው ላይ ይጻፋት
ለማስረጃ እንዲሆኑ ረጋ ብለው ይነበቡ ።

ሃሣብና ሃሣብ ይጋጩ ይሩጡ፤
በውል በቀ ነገር በጋራ እስኪደርሱ ።

የሚለውን ግጥም ስንመለከተው በዙ ሃሣብ ውስጥ የያዘ
መሆኑ አይታያችሁም፤ እስቲ የምትረዱትን ለመምህራችሁ
ንገሩ?

20 ቡጥቆ

ሃሣብና ሃሣብ ይጋጩ ይሩጡ፤
በውል በቀ ነገር በጋራ እስኪደርሱ ። የሚለው ግጥም
በጣም ብሬ ሃሣብ የያዘ ነው ። የሃሣቡ ብሬ መሆ
ን ደሀል እንደሆነና በስፉ ነበበ ቢያና በበዙ
ቃላት መበረራት ያለበት መሆኑን አነገራችኋለሁ ።
የተለያዩ ሰዎች ሃሣባቸው ለመጋጠት በውይይት ላይ
መሆን ይኖርባቸዋል ። አንደኛው አንዱ ሃሣብ ያራል
ቃል፤ ሌላው ሌላ ሃሣብ ያራልያል፤ ሌላኛው አንደ
ዚሁ ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የተለየ ሃሣብ
በቻ ማቀረብ ሣይሆን የሚቃወም ሃሣብም ይቀርባል ።
በዙ አይነት የተለያዩ ሃሣቦችና የሚቃረኑ ሃሣቦች
ከቀረቡ በኋላ የሚሆነውን የሚገበው ሃሣብ ላይ
በመጨረሻ ከስምምነት ይደረስና ደንን አዲስ የተስማ
ሙበትን ሃሣብ እንዲጠቀሙበት በውል መሙሬያ አጩር
ገው ስበበበው ይጸባል የሚል ሃሣብ የያዘ ግጥም ነው ፡
በጣም በዙ ቃላት ወስደ የተገለፀ ነው ። ግጥሚ ግን

ቅልበጥ በላ በሁለት ስንኝ ውስጥ በሚገኙ በስምንት ቃላት ብቻ ነው የተጨናቀቀው ። እንመልከተው

ሃሣብና ሃሣብ ይጋጩ ይፋጩ፣
በቃል በቁምነገር በጋራ እስኪደቁ ።

ተማሪዎች በአሁን ቀጥሎ ጥያቄዎች አቀርብላችኋለሁ በጥሞና እየተከታተላችሁ ለመመለስ ሞክሩ

መምህር ቀጥሎ ያለውን ግጥም ጥቁር ሠሌዳ ላይ ይጻፉት ።
ማስጃፍ አንጌቻል ተደርጎ ይነበብ

ካልተሳፈረበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ
ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ / ይደገም /

እሺ የዚህ ግጥም ሃሣብ ምንድነው? ምን መልዕክት አንደሚያስተላልፍ ለመምህራችሁ ንገሩ ።

20 ደቂቃ

ካልተሳፈረበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ፣
ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ ። በሚለው ግጥም መረዳት የሚቻለው ሃሣብ / ታክሲ በአጠገብህ ሲያልፍ ቆሞ እንዲወስድህ በትዕግሥት እስከምትደርስበት ድረስ ይጠብቅሀል ። ጊዜ ግን የዚህ አይነት ፀባይ የለውም ። ይመጣል፣ ይሄዳል ቆሞ አይጠብቅም ። ጊዜ የሚያልፍ ስለሆነ መስራት ያለብህ ነገር ካለ ጊዜ ሣያልፍብህ፣ ጊዜን ሳታባክን መሥራት ያለብትን ነገር በወቅቱ መሥራት የሚያስፈልግ መሆኑን የሚያስገነዝብ ግጥም ነው የሚል አይነት መልስ ሰጥታችሁ ከሆነ ልክ ናችሁ ።

እሺ ቀጣዩን ጥያቄ ደግሞ ተከታተሉ ።
ቤት መድፊያ ስንኝ የሚባለው የትኛው ነው?

20 ደቂቃ

ቤት መዉረጃ የሚገለው ስገኝ

ጊዜ ቃክቢ አይደለም አይወበትም ቆም የሚ
ለው ነው ።

እንግዲህ ተማሪዎች ለእንግም እንደመነሻ ሊሆን የሚ
ችል ዕውቀት እንደጠበቃችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።
በሬዲዮ ትምህርት ወቅት ተርበው የነበራችን አይነት
መለማመጃዎችንና በዚሁ በተጨማሪ አንደኛችሁ አንዱ
ስገኝ ትናገራችሁ ሊሳናችሁ ደገም ሁለተኛውን ስገኝ
በመናበር ተለማመዱ ታዲያ ዘም በሉ ቤት ማስመታት
ብቻ አይደለም ። መሉ ትርጉም ናርኩኸው መልዕክት
ሊያስተላልፍ የሚችል መሆኑን እርግጠኛ መሆን ይኖር
ባችኋል ። በተረፈ ለዛሬ ያዘጋጀነውን በዚሁ አጠና
ቀናለን በሌላ ፕሮግራም እስክንገናኝ ደህና ሁኑ ።

ሙዚቃ — የመገናኛ መዝሙር

አንባቢ — እንደምን አሉ መምህር
እንደምን አላችሁ ተማሪዎች

ተማሪዎች ባለፈው [illegible] ሳምንት ትምህርታችሁ
የጽዳት [illegible]
ርት ተምራችኋል ::

ተማሪዎች አንድ የተጠበቀ ጤና መሠረት ካለበት በቀ
ደም ተከተል መከናወን ያለባቸው ነገሮች ይኖራሉ ::
ስራ በተገቢው ቅደም ተከተል ከተሰራ የሚጠበቀው
መጨረሻ ላይ ይገኛል ጥሩ የሚታየው ውጤት ይገኛል ::
ቅደም ተከተሉ ካልተጠበቀ ግን ሊሆን የሚገባው ወይም
የሚጠበቀው ውጤት አይገኝም ማለት ነው ::

ለምሳሌ ያህል ቀላልና ሁላችሁ በአከባቢያችሁ የምታ
ዩትን ነገር እንደምሳሌ እንውሰድ ::
ልብስ አጠባ ወይም ልብስ ለማጠብ ተፈለገ እንበል ::
ልብስ ለማጠብ መጀመሪያ መታጠብ ያለበት ልብሱ
ይሰበሰባል፤ የሚታጠብበት ቦታ ይዘጋጃል፤
ማጠቢያው ውስጥ ያለው ልብስ ላይ ውሀ ይጨመራል፤
ሳሙና ይቀባል፤ ይታሻል፤ በውሀ ይለቀቃል፤ ይጨ
መቃል፤ ይሰጣል ከደረቀ በኋላ ወደቤት ይገባል፤ የሚ
ተኮስ ከሆነ ይተኮሳል፤ ይለበሳል የሚለው ቅደም ተ
ከተል እንደሰናው የጽዳት ቅደም ተከል ነው :: ይህ
ንን የጽዳት ቅደም ተከተል ያለ ተከተል ከሆነ ተገቢ
አይሆንም ::

ስለዚህ የታጠበ ልብስ ለመልበስ በዚህ ቅደም ብሎ
በተዘረዘረው ቅደም ተከተል መሠረት መከናወን አለ
በት ማለት ነው ::

አይደለም እንዴ ተማሪዎች? ሁላችሁም ወላጆቻችሁን
ከማጠብ በፊት ማስቀደም ይቻላል አይደል?

10 ሰከንድ

ታጥቦ እንዳበቃ ወዲያው ከተለቀለቀ በኋላ ወደቤት ማስ ገባት ይቻላል እንዴ?

10 ስዕል

ለሁሉም ጥያቄ መልስ እንደሰጣችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ለመጀመሪያው ልብስ ካልታጠበ ለምን ይበጣል ። መስ ፋት ያለበት መጨረሻ ላይ ነው ።

ታጥቦ በንፁህ ውሀ ከተለቀለቀ በኋላም ወደቤት ማስ ገባት አይቻልም ። ካልደረቀ በሚቀመጥበት ቦታ ላይ ያለውን አቧራ እያነሳ እንደገና ይቆሽሻልና አይሆ ንም ።

ብቻ በቀጣሪው በአንዱ መሆን ባለበት ሂደት ውስጥ በውርጌት ቅደም ተከተል ያልተከናወነውን ሥራ ውጤት የሚጠበቀውን ያህል አይሆንም ።

ተማሪዎች በመቀጠል ሁለት የገኙ ክፍል የሬዲዮ ተማ ሪዎች በዚህ በውርጌት ቅደም ተከተል ላይ የተለያዩ የውርጌቶች ሂደት እንዲያበባበቡ በመምህራቸው በተነ ገሬቸው መሠረት ያዘጋጁትን በመደምደም ተከታተሉ ። መምህር የሬዲዮ ተማሪዎች የሚነጋገሩበትን የውርጌት ቅደም ተከተሎች ጥቁር ሠሌዳ ላይ ይጽፋሉ ።

ድምፅ — መሸጋገሪያ

ተማሪ 1 — ከእንቅልፌ ቶሎስኬ አልጋዬን እያነጠፍኩ ዛሬ ከእናቴ ጋር የምንበረው ነገ እለኝና እዚያው ሆኜ እንዱ የው ርጌት ቅደም ተከተል የሚጠይቅ ሥራ አገኘሁ ። ምን መሰለሽ ከአልጋሽ ስትነሺ አልጋሽን ለማንጠፍ ምንድነው መጀመሪያ ማድረግ ያለብሽ የሚለው ነበር ። የውርጌት ቅደም ተከተል አለው ።

ተማሪ 2 — ይገርመኛል እኔ ለብ እንዳንቺው አስታውሸ ነበር አልጋሽን ለማንጠፍ መጀመሪያ አልጋው ላይ ያሉትን ልብሶች አንስቶ በደሌብሰባ ታገኛለሽ በዚያ የልብ

ታራግፊያለሽ፣ ከዚያ ደግሞ አንሶላዎችን ከደረገናሽ በቀሬ በቀሬ ታነጥፊያለሽ፣ ከዚያ በርጩማውን ታነ ጥፊያለሽ፣ በመቀመጫ ዙሪያውን ትሸከሚያለሽ ከትራስጌ በኩል አጠፍ አድርገሽ ትሸከሚያለሽ ከዚያ በኋላ የአ ለጋ ለበስ ካለ በላዩ ላይ ታነጥፊያለሽ ፡፡ ይኸው ነው አይበቃም፣ ሌላ አይደለም እንዴ?

ተማሪ 1 ሌላ ነው ፍራሹ ላይ መሸመሪያ በርጩማውን አነጥፌ ለሁ በትይ ናፒ ሌላ አይሆንም ነበር ፡፡

ከሆነ ደግሞ የመደቡሽ ደብዳቤ መጻፍ በጓሉጌ ምን- ምን ማድረግ አለብሽ ፡፡ ቤቱ ውስጥ የሙታደርገውን አይደለም መጻፍ ከመሸመርሽ በፊት የሚገረውን ዘገዞት ማለቴ ነው ፡፡

ተማሪ 2 የሚጻፍበት በው አለ ፡፡ ለቡ የሚገረውን ሆሣብ ማው ልኝና ማወረቅ ከሁሉም ይቀድማል ፡፡ ቀጥሎ የሚጻፍበት ወረቀት ይዘጋጃል ፡፡ የደብዳቤ መጻፊያ ወረቀት ቢሆን ይመረጣል ፡፡ ከዚያ መጻፊያ እስክሪፕቶ ይዘጋጃል ፡፡ ፖስታ ከጻፍሽ በኋላም ቢሆን ፖስታ ቤት ለማስገባት ስትሄጅ መገዛት ይቻላል ፡፡ ከገዛሁ በኋላ የኔ አድራሻ ከግራ በኩል አናቱ ላይ የሚያከለትን በው አድራሻ ደግሞ ከቀኝ በኩል ከታች እጽፋለሁ ከዚያ ቴምብር ገዝቼ በመለጠፍ የፖስታ ማስረቀሚያ ሳጥን ውስጥ እከተዋለሁ ፡፡ በቃ ይኸው ነው ፡፡

ተማሪ 1 ሌላ ነው ይኸው ነው ፡፡ አንቺ ደግሞ ወደኛ ከብዱ ሥራ እንዲሆን በጆ ቀላል የሆነ ወደኛ ፡፡

ተማሪ 2 አሺ ቀላል ነው ፡፡ አንዱ የክፍሉ መምህር ወደቶ ሊያ ስ ትምር ክፍል ውስጥ ሲገባ የሚያደርጋቸውን ነገሮች በቅደም ተከተል ንገሪኝ ፡፡

ተማሪ 1 ተማሪዎች ክፍል ገብተው ቀጥ ብለው አንበሉ ።
መምህሩ የክፍል መገባደጃ ሰዓት ሲደርስ ይመጣል፣
በረን አንኳኩተው ይገባል፣ ተማሪዎች ይነሳሉ፣ እን
ደምን አደራችሁ ይላል፣ የተማሪዎችን የስሞታ መልስ
ከተቀበሉ በኋላ ተቀመጡ ይሏቸዋል ። ስሙ ይጠራሉ፣
የቤት ሥራ ካለ ደገን ደርሟሉ፣ ቀሪው ባለፈው ቀን
እስከሚረው የነበረውን አርዕስት አስታውሰው ማስተማር
ይጀምራሉ ። አይበቃም ።

ተማሪ 2 ይበቃል ።

ተማሪ 1 ይሸውልሽ አሁን ደግሞ ለዓት ያለ ተያዩ ለመይቸሽ
የአንዱን ነገር የዶርጊት ቀደም ክፍለ አዘበራርቁ
ነገርሽልሁ፣ እንደ ደገን የዘበራረቀውን አያስቸግ
በልሽ ትነግሬኛለሽ ።

ተማሪ 2 እሺ ተራ በይ ንገሪኝ ።

ተማሪ 1 ዛሬ ክለሽ ማስደን ትፈልጊያለሽ ለዚያ የሚሠረው
የዶርጊት ቀደም ክፍለ የመክሊያ ጉድጓድ መፍረር፣
ችግኝ ማፍላትና ችግኝ መትከል፣ የተተከለውን ችግኝ ውሀ
ማጠጣት ይሸውልሽ ከዚህ ላይ እያየሽ በሬ /የወረቀት
መገለጫ ይበማል/

ተማሪ 2 እሺ ለዚህ መሆን ያለበት ቀደም ክፍለ የመጀመሪያ
የሚሆነው ችግኝ ማፍላት ነው ። ቀጥሎ የመትከያ ጉድ
ጓድ ማዘጋጀትና ችግኝ መትከል የተተከለውን ችግኝ
ውሀ ማጠጣት ነው መሆን ያለበት ።

ተማሪ 1 ልክ ነሽ እንደ ደገሞ ዘይቸ የሠው አይነት አቧዘ
ጋሽሽ ከሆነ አኔ አስይዋለሁ ።

ተማሪ 2 ኸሬ እሰቸ አዘጋጅቻለሁ ። አንዱ አሷሬ ለመኸኝት
ግዜ ማዶሬን ያስረሪጋል፣ ለዚያ የሚያስፈልገውን

የድርጊት ቅደም ተከተል አዘበራርቄ ነው የማቀርበ፣
ለሽ አንቺ ደግን ወሆን ባለበት ቅደም ተከተል ታስ
ተካክዪ የለሽ ።

ወንበኛትን ለግዢ የሚያስፈልገውን ነገር ማዘጋጀትን
የሚጠበቀባትን ቦታ ማወቅን ወደዚያ በንበኛት ቦታ የሚ
በሏትን ሥነስ ማዘጋጀት ይበቃል ይህን እስተካክዪ
ይበው እዚህ ላይ እደየሽ አደርገው/ የወረቀት ወገ
ቢሏት

ተማሪ 1 ቀረ ነው እኔ ሀገር ወንበኛት ስለመወደ በደንብ ነው
ቅደም ተከተሉን የማስተካክለው ወገ ከመን ወቅደም
እንዳለበት አውቃለሁ ።

የመጀመሪያው የሚሆነው ለንበኛት የሚሄዱበትን ቦታ
ማወቅ ነው ። ከዚያ አንደ አየር ዐበቀ ሁኔታ ለግዢ
የሚያስፈልገውን ነገሮ ~~ማዘጋጀትን~~ በንበኛት
ቦታ የሚበሏትን ሥነስ ማዘጋጀትን ወደዚያ ከዚያም
ወንበኛት በወወበት ሁኔታ ወደ ቤት መመለስ ነው የሚ
ሆነው ።

ተማሪ 2 ትክክል ነው ገን እንዱ ነገር እኔ ያልወደድኩትን
ቅደም ተከተል ውስጥ አስገብተሻል በሆነም በትክክ
ለኛው ቦታ ስለሆነ ተቀበያለሁ ። ወደ ቤት መመለስ
የሚለው ነው ።

እሺ አሁን እኔ አንዱ ቀደቁ የተለየ ቀደቁ አወዩ
ሽና ለዚሬ ይበቃናል ። ወየት ወደት ብት በመምቢያሽ
በሬት እና ሽን ለማግዝ ወን ታደርጊያለሽ?

ተማሪ 1 ከእንቅልፌ ከተነሳሁ በኋላ አፌን እና ፊቴን ከታጠብኩ
በኋላ ቁርስ ወምሬት እንዘጋለሁ፣ ትንንሽ ወንድሞቼ
ንና እህቶቼ ወታጠበና ወልበስ እረዳቸዋለሁ፣ ቁርስ

ተራን ይዞ ወደ ት/ቤት እሄዳለሁ ።

ተማሪ 2 — እንደ እናት ነው የምትከሪው ደግሞ በዚያ ላይ ገዝዝ ለጅነሽ

ተማሪ 1 — ሁሌም በምርዐት ስለመጠቀመበት እና ቶን በሥራ ረዳቴ አስደስቻት ተና ቶን በሚገባ ስለማጠና ነው ። በይ እሁን የማገዛት ነገር ካለ ለጊዜው በይ ደህና ሁኚ ።

ተማሪ 2 — ደህና ሁኚ / በር ዘግቶ ይዘጋል /

ድምፅ — የመሸጋገሪያ ሙዚቃ

አቅራቢ — ተማሪዎች የራሴ ተማሪዎች..........ና..........
ይደረጉትን ውይይት አዳመጣችሁ አስቲ እናንተ ደግሞ
ትምሮ ያልሆነ የድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክሉ
በቅድሚያ መሆር ? ትር ሠሌዳ ላይ ይጻፋላችኋል ከዚያ
ላይ እያያችሁ ማስተካከል ነው ።

ደመና በሰማይ ተቋጥሮ አስመሰለው
በጣቅ አስገመገመ
ዝናብ ጣለ
ወረቀ ጠቀቀ
ተደግሞ ይነበበ / ማስከኛ እንደሚቻል ተደርጎ ይነበበ /

20 ሰከንድ

ቅደም በላችሁ እንዳቀሰበት ለማድረግ ነው ጊዜ እን
ደሚያገባችሁ ይገመታል በሆነም መልስ

ደመና በሰማይ ተቋጥሮ አስመሰለው
በጣቅ አስገመገመ
ዝናብ ጣለ
ወረቀ ጠቀቀ የሚለው ከከለኛ ቅደም ተከተል
ነው ።
ትምሮ ያለውን ደግሞ አዳምጡ በት ለመሥራት የሬለን

በሙ ማድረግ ያለበት መንገድነው? ትዕዛዝ ክፍሉን አስ ካበሉኝ

መሬት ማግኘት

ለቤቶ መሥሪያ እቃዎች ማሰባሰብ

የቤት መሥሪያ ገንዘብ ማዘጋጀት

ቤት መሥራት

20 ሰዓት

የመጀመሪያው የቤት መሥሪያ ገንዘብ ማዘጋጀትና ቀጥሎ የቤት መሥሪያ መሬት ማግኘት የቤት መሥሪያ ዕቃ ማሰ ባሰብ፤ ቤት መሥራት ቢሆኑ ልክ ናቸው ።

እንግዲህ ተማሪዎች ለዚሁ ያዘጋጀነው ትምህርት በሙ ሉው ወቅትት የሚገባቸውን የክንውን ቅርጊት ትዕዛዝ ክፍሉ ማወቅ የሚገባ በመሆኑ ባለማወቃቸው ቀደም ለሆኑ ወሰሉ የቅርጊት ትዕዛዝ ክፍሎችን በማገናኘት ከጓደኞቻቸው ጋር ተወያይተው ። / ለዚሁ ያዘጋጀነውን በዚህ እናያለን ። ስለዚህ ፕሮግራሙ እስከነገ ድረስ ይሆና ቆቁ ።

| | |
|---|---|
| ድምጽ | የመግቢያ ሙዚቃ |
| አቀራቢ | እንደምን አሉ መምህር<br>እንደምን አላችሁ ተማሪዎች |

ተማሪዎች በዛሬው በሰባተኛው ሳምንት ትምህርታችሁ የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ትምህርት እናቀርብላችኋለሁ ።
የዚህ ትምህርት ዓላማ ማንኛውም ድርጊት ወይም ሁኔታ መንስኤ እንዳለውና በመንስኤው ምክንያት በሚደረግ እንቅስቃሴ ከአንድ ከታለመ ውጤት ላይ እንደሚደርስ ለማስገንዘብ ነው ። ከዚህ በተጨማሪም ውጤት ተብሎ የተወሰደው እንደ መንስኤ ሆኖ ሌላ ውጤት የሚያስገኝ በመሆኑ መንስኤና ውጤት አንድነት ያላቸው አንዱ መነሻ አንዱ መድረሻ ወይም ውጤት በመሆኑ ደግሞ ልዩነት ያላቸው መሆኑን የምትማሩበት ይሆናል ።

አንድ ልጅ እድሜው ለትምህርት ቢደርስ መማር ይኖርበታል ። ይህ የማንኛውም ልጅ መብት ነው ። መብት በመሆኑ መማር አለበት ። ስለዚህ ይህ የመማር መብት መንስኤ ሆኖ ልጁ ት/ቤት ይገባል ። ምንድነው ውጤት የሚሆነው?

10 ሰከንድ

መማር መብት ሆኖ ልጁ ት/ቤት ቢገባ የሚኖረው ውጤት መማር ማወቅ ነው አላችሁ? ጥሩ ከዚያም አልፎ ሀገሩን ወገኑን የሚጠቅም ዜጋ ማፍራት፣ እራሱ የሚረዳ መሆን የሚገባ የመማር ውጤት ነው ።
አሁን እዚህ ላይ የማንኛውም ልጅ የመማር መብት መንስኤ ሲሆን ትምር ማወቁና መረዳቱ እራሱንና ወገኖቹን የሚረዳበት ደረጃ ላይ መድረሱ የመማሩ ውጤት ነው ።
በሌላ በኩል ደግሞ መማርና ማወቅ ለሌላ ለከባድ ምርምርና ጥናት ስለጋበዘው ተመራማሪ ሣይንቲስት ሆነ እንበል ። የተማረ ሁሉ ሣይንቲስት ተመራማሪ

የነበረው ኩሮ የማወቅ ሁኔታ ወይም ማወቅ እንደገና መነሻ ሆኖ ተመራማሪ ሣይንቲስት በመሆን ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሚሆን የፈጠራ ሥራ የመስራት ደረጃ በመድረሱ ሌላ ውጤት እንዲኖረው ሆነ ማለት ነው ።

እሺ አሁን አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ ክረምት ገባ ደመናው ተንሰስ መስፈልፌ ዝናብ መዘነብ ጀምሯል ይህን እንደመነሻ በመውሰድ ውጤት ሊሆን የሚችል ነገር ለመምህራችሁ ንገሩ መምህር የሚሰጡትን መልስ ይቀበሏቸው ።

20 ሰከንድ

ሌላ ሌሎች ተማሪዎች ከተናገሩት የተለየ ውጤት ሊሆን የሚችል ነገር የሚነገር ተማሪ አለ ቴ የሚሞክር ማነው?

20 ሰከንድ

የተለያየ ውጤት መስጠት ይቻላል ። የተወሰኑ እኔ ልንገራችሁ፣

— በሰፈራችን በየቦታው ውስጥ የተጠራቀመውን ቆሻሻ አጥቦ አጽርጉ ይወስዱልናል ።

— ወቅቱን ጠብቆ የመጣ ስለሆነ የዘር ሥራዎችን በተለመደው ጊዜ መጀመር እንችላለን ።

— ከአጀማመሩ ጥሩ ስለሆነ በዘንድሮው መከር የሚገኘው ሰብል ከዚቶ አያልቅም የሚል እይነት በጥቃቸሁ ከሆነ በጣም ጥሩ ነው ።

እሺ ተማሪዎች የክረምት ዝናብ ኃይለኛ ነበር ሀይለኛ በመሆኑ ምክንያት በዝናቡ መነሻ የተለያዩ አደገኛ ሁኔታዎችም መከሰት ይችላሉ ። እስቲ በከባድ ዝናብ ምክንያት የተፈጠሩ ሁኔታዎች ውጤቶች ደግሞ ለመምህራችሁ ንገሩ ።

20 ሰከንድ

ሌላስ አለን ከተነገረው የተለየ ውጤት ሊሆን የሚችል ነገር የሚነገር? መምህር ይቀበሏቸው ።1



20 ሰከንድ

— ወደ ት/ቤት የምንሄድበት መንገድ ላይ ያለው ዱል ዱይ በጎርፍ ተወሰደ ።

— ወንዝ ሞልቶ ሰው ወሰደ

— በወንዝ ዳርቻ የሚገኙ ቤቶችን ወሰደ የሚሉና ሌሎች ውጤቶችን ማቅረብ ችላችሁ ከሆነ ጎበዞች ናችሁ ።

አሁንም ሌላ ጥያቄ አጠይቃችኋለሁ ። ተዘጋጅታችኋል፣ አንድ የነጋበት ጅብ ማለትም ሌሊት ተመልሶ ወደ ዋሻ መሄድ ሲገባው አንድ የገጠር አጥር ስር የበቀለ ቁጥ ቋጦ ውስጥ ተደብቆ ነበር ። በአጠገቡ መኪና ሲያልፍ ደምበር በመውጣት በቀን በሰፈር ውስጥ ሲሮጥ የነበር ይህንን መነሻ አድርጋችሁ ጅቡ ቀን በሰፈር ውስጥ በአካባቢው በመታየቱ ሊፈጠሩ የሚችሉ ነገሮችን ለመም ሀራችሁ ንገሩ ።

20 ሰኮንድ

ተማሪዎች ጅቡ በሰፈሩ ውስጥ በመታየቱ መንስኤነት እናንተ ብዙ ተናገራችሁ ይሆናል ። እኔ ደግሞ የተ ወሰነ ሊሆን የሚችሉ ሁኔታዎችን ልንገራችሁ ።

— የሰፈሩ ሰው በሙሉ ይጯጯህ ነበር ።

— በመንገድ ላይ ያገኘውን አህያ ነከሰ ።

— እናቶች ልጆቻቸውን ለማምጣት ጅቡ ወደነበረበት ቦታ ባይፈሩ ይሮጡ ነበር፣

— ለማምለጥ ሲሮጥ አንድ ክፍት ቤት ውስጥ ገብቶ ሊጥ ደፋ ። የሚልና ሌላም ማለት ይቻላል አይደል?

በጅቡ በቀን በሰፈር ውስጥ መግባት ምክንያት ብዙ ነገሮች ሆኑ ማለት ነው ።

አንድ ሌላ ሁኔታ ከዚሁጋር አያይዘን እንመልከት ። ጅቡ በፈር ውስጥ ሲገባ የሰፈሩ ውሾች በሙሉ ተከትለው ያባርሩት ነበር፣ አንድ ጠመንጃ ያለው ሰውዬ ሁለት ጥይት ተኩሶ በአንደኛው ጥይት ጅቡን ገደሉት ።

[illegible]
የገደለው ። በዚህ ጊዜ ባለውለታና የዘመቱት ሰውዬ ተባሉ ።

የትምህርቱ ዓይነት፡— ......አማርኛ

ክፍል፡— ......7ኛ

የኘሮግራም ቁጥር፡— .....20

1. **የትምህርቱ ርዕስ፡—** የድርጊት ቅደም ተከተል ማወቅ

2. **የትምህርቱ ዓላማ፡—** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች
   - አያንዳንዱ ድርጊት በቅደም ተከተል የሚከናወን መሆኑን ያውቃሉ፤
   - የትኛው ድርጊት ቀደም እንደሚፈጸም የቱ ደግሞ እንደሚከተል ይናገራሉ፤
   - ቅደም ተከተል የሌለው ድርጊት እንደሌለ ይገነዘባሉ

3. **የትምህርቱ ይዘት፡—**
   - ድርጊት ቅደም ተከተል እንዳለው
   - አንዱ ከሌላው የቀጥሎ እንደሚመጣ
   - በቅደም ተከተል መሥራት ያለውን ጥቅም

4. **የሬዲዮ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ፡—**

   4.1. በሬዲዮ መምህሩ የድርጊት ቅደም ተከተል ማለት ምን እንደሆነ ማብራሪያ ይሰጠል፤
   - የድርጊት ምሣሌ በመስጠት እንዲገነዘቡ ያደርጋሉ
   - ሁለት የሬዲዮ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በድርጊት ቅደም ተከተል ላይ ሲጠያየቁ ይቀርባሉ፤
   - ስለድርጊት ቅደም ተከተል በተማሩት ላይ በሬዲዮ መምህሩ ጥያቄ ይቀርባል ፡፡

   4.2. **ከሬዲዮ ትምህርት በፊት፤**
   - የዕለቱ የትምህርት ርዕስ ምን እንደሆነ ያሰውቋቸው፤
   - ትምህርቱን በጥሞና እንዲከታተሉ ያሰስቧቸው
   - በሬዲዮ ትምህርት ወቅት በሬዲዮ መምህሩ ከሚነገራቸው ነገር በቀር ሌላ ሥራ እንዳይሰሩ ይንገሯቸው ፡፡